# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነ-ፅሑፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሃ-ግብር

# "ሰዋሰውን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋሰው ዕውቀት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና" በሊሙ ገነት አንደኛ ደረጃ ትምህርት በ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፡፡

በ

ታረቀኝ አብርሃም

አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነ-ዘዴ ለሁለተኛ ዲግሪ (ማስተርስ) ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፡፡

ጥቅምት. 2017

ጅማ ኢትዮጵያ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነ-ፅሑፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ

መርሃ-ግብር

"ሰዋሰውን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋሰው ዕውቀት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና" በሊሙ ገነት አንደኛ ደረጃ ትምህርት በ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፡፡

በ

ታረቀኝ አብርሃም

አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነ-ዘዴ ለሁለተኛ ዲግሪ (ማስተርስ) ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፡፡

አማካሪ :- ለማ ንጋቱ (ዶ/ር)

ረዳት አማካሪ :- ምህረት ሰዳሞ (ዶ/ር)

ጥቅምት. 2017

ጅማ ኢትዮጵያ

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

### የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነ-ፅሑፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሃ-ግብር

እንደ ጥናታዊ ፅሑፍ አቀራረብ ገምጋሚ ቦርዶች "ሰዋሰውን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋሰው ዕውቀት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና" በሊሙ ገነት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት በተማሪ ታረቀኝ አብረሃም ለሁለተኛ ዲግሪ (ማስተርስ) ማሟያ የቀረበው ጥናት በአማካሪና በፈታኞች ተገምግሞ የዩኒቨርሲቲውን መስፈርት ያሟላ ስለሆነ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

የፈታኞች ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

የአማካሪ ስም________________________________ ፊርማ__________ ቀን________

የውስጥ ፈታኝ ስም___________________________ ፊርማ__________ ቀን________

የውጭ ፈታኝ ስም____________________________ ፊርማ__________ ቀን________

## ምስጋና

በመጀመሪያ ሁሉን ነገር በቸርነቱ አስጀምሮ ለሚያስፈፅም ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በመቀጠልም ጥናቱን ስጀምር የጀመርኩትን ርዕስ በማስተካከል እና መስመር በማስያዝ ከትልመ ጥናቱ አንስቶ እስከ አሁኑ ሰዓት ድረስ ያለ ምንም መሰልቸት በኢሜል ግብረመልስ በመስጠት እና በአካልም የቸገረኝን ሳማክራቸው  በጎ ምላሽ በመስጠት የጎበጠውን እያቃኑ የራቀውን እያቀረቡ የረቀቀውን እያጎሉ እዚህ ላደረሱኝ አማካሪዎቼ ለዶ/ር ለማ ንጋቱ እና ለዶ/ር ምህረት ሰዳሞ እንዲሁም ሁሌም ለሚያበረታቱኝ ለዶ/ር ጥበቡ ሽቴ እና ለዶ/ር ማንያለው አባተ ለዶ/ር ጌታቸው አንተነህ ለመምህራኖቼ በሙሉ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡ በመቀጠልም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ፈተናዎችን በማረም፣ መረጃን በመስጠት ቀና ትብብር ላደረጉልኝ ለሊሙገነት 1ኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡ በመጨረሻም የፅሑፉን ረቂቅ በኮምፒውተር በመፃፍ እና ኤዲት በማድረግ ለተባበሩኝ ሁሉ ታላቅ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

# አህፅሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኢንዳክቲቭ ዘዴ ሰዋሰውን ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋሰው ዕውቀት በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና መመርመር ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በጂማ ዞን በሊሙ ኮሳ ወረዳ በሊሙ ገነት ከተማ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ትምህርት በመከታተል ላይ የሚገኙት ተማሪዎች 210 ተማሪዎች በአራት ክፍልች ውስጥ ሲሆን ለጥናቱ የተመረጡት ደግሞ ከጠቅላላው አራት ክፍሎች በዕድል ሰጪ የንሞና ስልት የ8ኛ (A) እና የ8ኛ(B) ክፍሎች ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከዚህም በኋላ የተመረጡት ክፍሎች በ8 B(የሙከራ ቡድን) 8A(የቁጥጥር ቡድን) እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡ ከእነሱም በፈተና እና በፅሁፍ መጠይቅ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል የተሰበሰቡት መረጃዎችም መጠይቅ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎ ተሰብስበዋል የተሰበሰቡት መጃዎችም በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተተንትነዋል፡፡ በውጤት ትንተናው መሰረት በኢንዳክቲቭ ዘዴና በተለመደው አቀራረብ ምክንያት ሰዋሰውን ማስተማር በተማሪዎች የሰዋሰው ዕውቀት ላይ የታየው ለውጥ ልዩነት መኖሩን በኢንዳክቲቭ ዘዴና በተለመደው አቀራረብ ፈተና አማካይ ውጤት መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት ($p<0.05$) ታይቷል፡፡ ይህም በኢንዳክቲቭ ዘዴ የተማሩት በተለመደው አቀራረብ ከተማሩት በላይ የሰዋሰው ዕውቀታቸው መሻሻሉን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ኢንዲሁም በኢንዳክቲቭ እና በተለመደው አቀራረብ ምክንያት በተማሪዎች ሰዋሰው የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ የሚታየው ለውጥ ልዩነት መኖሩን በኢንዳክቲቭ ዘዴና በተለመደው አቀራረብ በቅድመ እና ድህረ ፍላጎት የፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት መካከልም በስታቲስቲክ ጉልህ ልዩነት ($p<0.05$) ታይቷል፡፡ በዚህም ኢንዳክቲቭ ዘዴ ከተለመደው አቀራረብ በተሻለ መልኩ ሰዋሰውን የመማር ፍላጎት ላይ ለውጥ እንዳመጣ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ በጥናቱ ውጤት መሰረትም በኢንዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋሰው ዕውቀትና የመማር ፍላጎት ለማሳደግ ጠቃሚ ሚና እንዳለው ለመረዳት ትችሏል፡፡ ይህም በመሆኑ ይህ የኢንዳክቲቭ ዘዴ ለአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች በተሻለ መፍትሔነት ተቀምጧል፡፡

# ማውጫ

ይዘት ገጽ

ምስጋና ........ i
አህፅሮተ ጥናት ........ ii
የሰንጠረዥ ማውጫ ........ v
ምዕራፍ አንድ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 4
1.3 የጥናቱ ጥያቄዎች ........ 5
1.4 የጥናቱ ዓላማ ........ 5
1.4.1 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ........ 5
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 5
1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 6
1.7 የጥናቱ ውስንነት ........ 7
1.8 የቁልፍ ቃላት ፅንሰ ሃሳቦች አጠቃቀም ብያኔ ........ 7
ምዕራፍ ሁለት ........ 8
2 ክለሳ ድርሳናት እና የተዛማጅ ፅሑፎች ቅኝት ........ 8
2.1 የሰዋሰው ምንነት ........ 8
2.1.1 የሰዋሰው ትምህርት አስፈላጊነት ........ 9
2.1.2 የሰዋሰው ትምህርት አቀራረቦች ........ 11
2.1.3 ኢንዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት ዘዴ ........ 12
2.1.4 በኢንዳክቲቭ ዘዴ ሰዋሰው ማስተማር ላይ ምሁራን ያላቸው ዕይታ ........ 13
2.1.5 ዲዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት ዘዴ ........ 15
2.1.6 በዲዳክቲቭ ሰዋሰው ማስተማር ላይ ምሁራን ያላቸው ዕይታ ........ 15
2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 17
2.3 የጥናቱ ጽንሰ ሃሳብና ማዕቀፍ ........ **Error! Bookmark not defined.**
ምዕራፍ ሶስት ........ 22
3 የአጠናን ዘዴ ........ 22
3.1 የጥናቱ ተሳታፊዎችና የንሞና ዘዴ ........ 22
3.1.1 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ........ 23
3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 23
3.2.1 ፈተና ........ 23

3.2.2 የፅሑፍ መጠይቅ ..... 25
3.3 የጥናቱ ሂደት ..... 26
3.4 የማስተማሪያ ቴክስት አዘገጃጀት ..... 27
3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ ..... 29
ምዕራፍ አራት ..... 30
4 የጥናቱ ውጤት ትንተና ማብራሪያ ..... 30
4.1 የጥናቱ ውጤት ትንተና ..... 30
4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ..... 38
ምዕራፍ አምስት ..... 40
5 ማጠቃለያ ፣ መደምደሚያና የመፍትሔ ሃሳብ ..... 40
5.1 ማጠቃለያ ..... 40
5.2 መደምደሚያ ..... 42
5.3 የመፍትሔ ሃሳቦች ..... 43
ዋቢ መፃህፍት ..... 44
አባሪዎች ..... 47

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 4.1 የሙከራ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ፈተና የሰዋሰው ፈተና ችሎታ ንፅፅር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት........................................................................36

ሰንጠረዥ 4.2 በሙከራ ቡድንነና በቁጥጥር ቡድን ድህረ ፈተና የሰዋሰው ፈተና ችሎታ ንፅፅር በባዕድ ንፅፅር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ............................................................37

ሰንጠረዥ 4.3 የቡድኖቹ የቅድመና የድህረ ልምምድ የሰዋሰው ፈተና ችሎታ ተናጠላዊ ንፅፅር በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት.....................................................................38

ሰንጠረዥ 4.4 በኢንዳክቲቭ ዘዴ እና በተለመደው አቀራረብ ቅድመ የመማር ፍላጎት በማጎልበት ላይ የሚታየውን ንፅፅር (በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት).....................................40

ሰንጠረዥ 4.5 በኢንዳክቲቭ ዘዴና በተለመደው አቀራረብ ድህረ የመማር ፍላጎት በማጎልበት ላይ የሚታየው ንፅፅር (በባዕድ ናሙና) ቲ-ቴስት).........................................................41

ሰንጠረዥ 4.6 የቡድኖቹ የቀድመና የድህረ የሰዋሰው የመማር ፍላጎት የፅሁፍ መጠይቅ ተናጠላዊ ንፅፅር (በዳግም ልኬት ናሙና) ቲ-ቴስት.......................................................43

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ቋንቋ ፈርጀ ብዙ ጥቅሞች ያሉት እና የሰው ልጆችን በማግባባት በማህበራዊ ሕይወት ውስጥ እጅግ የጠበቀ ትስስር እንዲኖራቸው በማድረግ የሚጫወተው ሚና የላቀ ነው፡፡ ያለቋንቋ የሰውን ልጆች በማህበራዊ፣ በፖለቲካዊ እና በኢኮኖሚያዊ ማስተሳሰር አይቻልም፡፡ ስለዚህ የሰው ልጅ ያለ ቋንቋ ሕይወት ምንም ትርጉም የሌለው ይሆናል፡፡ ቋንቋን ለተማሪዎች ማስተማር ዋነኛ ዓላማው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብ እና የመፃፍ ክሂላቸው እንዲዳብር እና ተማሪዎች ከሰዋሰው ትምህርት ጋር ጥልቅ ቁርኝት ኖሯቸው የመናገር ችሎታቸው እንዲጎለብት ብሎም የሥነፅሑፍ ዕውቀት ኖሯቸው ጥሩ የቋንቋ ተመራማሪና ፀሐፊ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው፡፡

ቋንቋ ጥበብም ሳይንስም ነው፡፡ ጥበብነቱ መምህሩ በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች ትምህርቱን ውብ እና ማራኪ በሆነ ሁኔታ ለማቅረብ የሚጠቀምበትን የራሱ ዘዴ የሚያ መለክት ሲሆን፡፡ ሳይንሳዊነቱ ደግሞ መምህሩ በቋንቋ ላይ ያለውን ስነልሳናዊ ግንዛቤ ነው፡፡ ቋንቋን ማስተማር የተጀመረበት ጊዜ ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ ቢሆንም የሰዋሰው ትምህርት ግን ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተካቷል፡፡ ከዚህ አገላለፅ ለመረዳት እንደሚቻለው ቋንቋን ማስተማር የተጀመረው እጅግ ቀደም ባሉት ዘመናት ሲሆን ስነልሳን ግን ራሱን ችሎ መጠናት የተጀመረው በ20ኛው ክፍለ ዘመን ተቀባይነት እያገኘ እንደመጣ (stem 1986;126) አክለው ይገልፃሉ፡፡

Ur (1999) እንደሚገልፁት የማንኛውም ቋንቋ ተናጋሪ በቋንቋ ሃሳቡን በንግግርም ሆነ በፅሁፍ ለመግለፅ እንዲሁም የሌላውን ሰው መልዕክት በትክክል ለመረዳት የሰዋሰው ዕውቀት ያስፈልገዋል፡፡ ሲሉ Brown (1994) ደግሞ የቋንቋ ትምህርት ክሂል ከማዳበር ባሻገር የቋንቋው ተማሪ ሊገነዘበው የሚገባውን ዕውቀት ማካተት ይኖርበታል፡፡ ይህም ዕውቀት የቋንቋ ስርዓት ወይም ሰዋሰው ነው ይላሉ፡፡ በዚሁ መሰረት አፍ መፍቻም ሆነ ሁለተኛ ቋንቋን ከተግባቦታዊ አገልግሎት በተጨማሪ ሰዋሰዋዊ ሥርዓቱን መማርም ሆነ ማስተማር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ የቋንቋ ዕውቀትና ችሎታ የሚለካው ተግባቦታዊ አገልግሎቱን ከነሥርዓቱ አቀናጅቶ መገንዘብ በመሆኑ ሰዋሰውን መማርም ሆነ ማስተማር በጣም አስፈላጊ እና የግድ ነው፡፡ ምክንያቱም ያለሰዋሰው ዕውቀት የቋንቋ ባህር ውስጥ ለመዋኘት የማይታሰብ ስለሆነ ነው፡፡

Larsen (1997, 18-19) ገለፃ "በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሰዋሰው አስፈላጊ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም ምክንያቱም ቋንቋን በትምህርትነት ከማቅረችን በፊት የቋንቋን ተፈጥሮ አሰራርና ባህሪያት ማወቅ ይጠበቅብናል፡፡ ከቋንቋ ባህሪያት ውስጥ ደግሞ አንዱ ስርዓቱ ነው፡፡ ስርዓቱ የሚጠናው ደግሞ በሰዋሰው ትምህርት ነው"በማለት የሰዋሰው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አስፈላጊ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ከላይ ከጠቀስናቸው ሃሳቦች መገንዘብ የምንችለው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሰዋሰውን ማስተማር የግድ መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ የቋንቋ ተማሪ ቋንቋውን ችሏል የሚባለው ከአራቱ ክሂሎች በተጨማሪ የቋንቋውን ሰዋሰው ጠንቅቆ ሲያውቅ መሆኑንና ሰዋሰው በቋንቋ ማስተማር ውስጥ በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ጉዳዮች ውስጥ የሚመደብ እንደሆነና ያለሰዋሰው ዕውቀት ቋንቋን በትክክል ለመረዳትና ለማወቅ እንደማይቻልም ያስረዳሉ፡፡

ከ1840-1940ዎቹ ዓመታት ጎልቶ የታየው ሰዋሰው ወትርጉም የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ (grammar Translation Method) ተማሪዎች ሰዋሰዋዊ ህግጋትን እንዲያውቁ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጥ ነበር ፡፡ ይሁን እንጂ በ1970ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ሰዋሰው ወትርጉም ዘዴ በእዝን ወአፋዊና በሁኔታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ (situational Language teaching Method) ሲተካና ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ተቀባይነት እያገኘ ሲመጣ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ለሰዋሰው ትምህርት ሲሰጠው የነበረው ትኩረት እየቀነሰ መጥቷል፡፡ (Ruther ford 1987)::

ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ባለሙያዎች እንደሚገልፁት የቋንቋ መዋቅር ከመግለፅ ይልቅ በቋንቋው መግባባት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን በማመላከት ላይ የሚያተኩር ዘዴ ነው፡፡ (Light bown and spade (2006) እንደሚያስረዱት መዋቅሮችን ተራበተራ ማቅረብ ቋንቋን በሚገባ ለመለማመድ አያስችልም፡፡ በቋንቋ ትምህርት ሂደትም በመጀመሪያ በሚገባ መግባባት ለመቻል (fluency) ትኩረት ሰጥቶ ተማሪዎችን ማለማመድ ተገቢ ነው፡፡ ይህንን ልምድ ተከትሎም ትክክለኛነትን (accuracy) ለማምጣት መስራት ይገባል፡፡ እንደ spada እና Light bown "አገላለፅ ተማሪዎች በተግባቦታዊ ዘዴ ሲማሩ በቋንቋው እውነተኛ (authentic) አጠቃቀምን ያዳብራሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም በርካታ የመስኩ ባለሙያዎች (krashen (1985) እና Terrel (1977) በቋንቋ ትምህርት ሂደት ለቋንቋ ቅርፅ የሚሰጠውን ትኩረት ጥያቄ ውስጥ አስገብተውታል፡፡

የተግባራዊ የቋንቋ መማር ንድፈ ሃሳብ (function Language Theorist) አራማጆች እንደሚገልፁት ቋንቋ ተግባቦት መፍጠሪያ እንጂ የቋንቋው መዋቅር አይደለም (Halliday (2004)):: እንደዚህ ባለሙያ አገላለፅ የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ተግባቦት እንዲፈጥር ማስቻል ነው፡፡ የሰዋሰው ትምህርት ይህን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ በሚያስችል ስልት

መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ሰዋሰውም በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ ካለው ግልጋሎት አንፃር ሊፈተሽ ይገባል፡፡

የሰዋሰው ትምህርት በኢንደክቲቭ ዘዴ እና በዲዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር እንደሚቻል የተለያዩ ባለሙያዎች ይገልፃሉ፡፡ እነዚህን የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብን የተለያዩ ባለሙያዎች እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

የሰዋሰውን ትምህርት በክፍል ውስጥ ለማቅረብ ከሚያስችሉ ስልቶች አንዱ ኢንዳክቲቭ (ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ) የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ነው፡፡ ኢንዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ የቋንቋውን መዋቅር በቀጥታ ከመግለፅ ይልቅ በተዘዋዋሪ መንገድ ተማሪዎች ህግጋቱን ፈልገው እንዲደርሱባቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ (Nunan (1999); Krashen (1982))::

ማረው (2003:42) እንደሚያስረዱት ሰዋሰውን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር በታወቀ ነገር አማካይነት ወይም ከታወቀ ነገር በመነሳት ያልታወቀ ሰዋሰዋዊ ህግጋትን ማስተማር ሲሆን አቀራረቡም ለተማሪዎች አንድ ዐረፍተነገር በምሳሌነት በማቅረብ ከዚያ ዐረፍተ ነገር በመነሳት የሰዋሰው ህጎችን እንዲያወጡ ለማድረግ ያገለግላል፡፡ ሌላው የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ በዲዳክቲቭ አቀራረብ ማስተማር (ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ወይም ቀጥተኛ በሆነ መንገድ) ሲሆን መምህር ተኮር እና በእያንዳንዱ መዋቅር የቅርፅ ልዩነት ላይ ግልፅ ትንተና በማድረግ የሚሰራ ሆኖ ተማሪዎች የቋንቋን መዋቅር እንዲተነትኑ የሚደረግበት ስልት ነው፡፡ Ur (1996) እንደሚገልፁት ተማሪዎች የትኛውን የሰዋስው ህግ እንደሚፍልጉ ካላወቁ ተማሪዎቹ እንዲያውቁ ሚፈለገውን ነገር መገመት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ይህ በትክክል ተለይቶ ካልታወቀ እንዲሁ ዝም ብሎ ጊዜን ማባከን ይሆናል፡፡

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ መረዳት የሚቻለው የተለያዩ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ መኖራቸውንና ከአቀራረቡም ውስጥ አንዱ ዲዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ሲሆን አቀራረቡም መምህር ተኮር ሆኖ ተማሪዎች የቋንቋን መዋቅር እንዲተነትኑ የሚደረግበት ስልት ነው፡፡ ሌላው የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ኢንዳክቲቭ አቀራረብ እንደሆነና አቀራረቡም ተማሪዎች ለበርካታ ምሳሌዎች እንዲጋለጡ በማድረግ ለትምህርትነት የቀረበውን ሰዋሰዋዊ ህግ እንዲያውቁ የሚደረግበት ትምህርት አቀራረብ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ከላይ በጥቂቱ ለመዳሰስ እንደተሞከረው የሰዋሰው ትምህርት በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ያለው ሚና ከፍተኛ ቢሆንም አቀራረብን በተመለከተ ሁሉንም ባለሙያዎች የሚያስማማ አንድወጥ አቋም የለም ምክንያቱም በየጊዜው የሚወጡ የተለያዩ ባለሙያዎች

በጥናታናታቸው የራሳቸውን ጥናት ብቻ አጉልተው ስለሚሄዱ እና አቀራረብ ላይ ሁሉም የራሱን ዘዴ ብቻ ይዞ ስለሚጓዝ ነው፡፡

በአጠቃላይ ቋንቋ መምህሩ በይዘትነት የመረጠውን ትምህርት ወደ ክፍል ይዞ ሲገባ ትምህርቱን በትክክል ተማሪዎች ዘንድ ያደርስልኛል ብሎ የሚያስበውን ማቅረቢያ ዘዴ መምረጥ ይኖርበታል፡፡ ለትምህርት የተዘጋጀውን የሰዋሰው ይዘት ለማቅረብ የትኛው የማቅረቢያ ዘዴ ውጤታማ ነው? የሚለው ሃሳብ በጥናት ሊፈተሽ ይገባል፡፡ ይህ ጥናትም ኢንዳክቲቭ ዘዴ የተማሪዎችን የሰዋሰው ዕውቀት በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ይመረምራል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚው በዚህ ርዕስ ላይ ለጥናት እንዲነሳሳ ካደረገው የመጀመሪያው ዐቢይ ጉዳይ ከመምህራን ጋር መደበኛ ያልሆነ ውይይት ሲያደርግ መምህራን አብዛኛውን ጊዜ የዲዳክቲቭ ዘዴ ላይ ብቻ ተመርኩዘው ሰዋሰውን ማስተማራቸውና መምህሩ ብቻ ቅርፁን እና ህግጋቱን ተናጋሪ መሆኑ (መምህር ተኮር መሆኑ) እና የተማሪዎቹ ተሳትፎ አናሳ መሆን በተማሪዎች የሰዋሰው ዕውቀት ላይ ክፍተት መኖሩን ተገንዝቧል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በሰዋሰው ትምህርት ላይ ያላቸው ተሳትፎ አናሳ መሆን እና በትምህርቱ ላይ ፍላጎት ማጣት በመመማር ማስተማር የሥራ ላይ ግምገማ ተገንዝቧል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች ሰዋሰው ከተማሩ በኋላ በሰዋሰው ፈተና የሚያመጡት ውጤት ዝቅተኛ እንደሆነ በተለያዩ ጊዜያት አጥኚው ከሥራ ልምዱ መገንዘብ ችሏል፡፡

ማረው (2003፡40) "የሰዋሰው ዋና ዓላማ ተማሪዎቹ ቋንቋውን በአግባቡ እንዲጠቀሙበት ከማስቻል ውጪ አይሆንም፡፡ ይሁን እንጂ በርካታ መምህራን በየማስተማሪያ ክፍሉ አብዛኛውን የትምህርት ጊዜ የሚያጠፉት ሰዋሰዋዊ ህግጋትን እና መደበኛ መዋቅሮችን በማለማመድ ነው"በማለት የመምህራንን የሰዋሰው ትምህርት አተገባበር ይገልፃሉ፡፡

በመሆኑም በኢትዮጵያ የቋንቋ ትምህርት ሰዋሰውን አስመልክቶ በርካታ ጥናቶች የተካሄዱ ቢሆንም እነዚህ ጥናቶች ለኢንዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ብዙም ትኩረት አልሰጡም፡፡ በሌላም በኩል የሰዋሰውን ትምህርት በኢንዳክቲቭ ዘዴ በተለይም በ1ኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ቢፈተሽ ተማሪዎቹ ውጤታማ ይሆኑ ይሆን? የሚል ጥያቄ በውስጡ ተመላልሷል፡፡ ስለሆነም ሰዋሰውን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር የተማሪዎቹን የሰዋሰው ዕውቀት በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና መፈተሽ ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡

## 1.3 የጥናቱ ጥያቄዎች

1- በክፍል ውስጥ የሰዋሰው ትምህርትን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር በተማሪዎቹ የሰዋሰው ትምህርት ዕውቀት ላይ ምን ዓይነት ለውጥ ይኖረው ይሆን?

2- የሰዋሰው ትምህርትን በኢንዳክቲቭ ዘዴ በክፍል ውስጥ ሲማሩ ያላቸው የሰዋሰው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ምን ያህል ይሆን?

3- በኢንዳክቲቭ እና በተለመደው አቀራረብ ሰዋሰውን ማስተማር በተማሪዎች ሰዋሰው የመማር ፍላጎት ላይ ልዩነት ይኖረው ይሆን?

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ኢንዳክቲቭ ዘዴን ተጠቅሞ ሰዋሰውን ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋሰው ዕውቀት በማጎልበት ረገድ የሚኖራቸውን ሚና መፈተሽ ነው፡፡

### 1.4.1 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች፡፡

ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

- የሰዋሰውን ትምህርት በኢንዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር በተማሪዎች የሰዋሰው ዕውቀት ላይ የሚኖረውን ለውጥ መመርመር፡፡
- የሰዋሰውን ትምህርት በኢንዳክቲቭ ዘዴ ሲማሩ ያላቸውን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መፈተሽ፡፡
- በኢንዳክቲቭ እና በተለመደው አቀራረብ ሰዋሰውን ማስተማር የተማሪዎችን ሰዋሰው የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ልዩነት መመርመር፡፡

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

- ለቋንቋ መምህራን፡- ኢንዳክቲቭ ዘዴን ተጠቅሞ ሰዋሰውን ማስተማር የተማሪዎች የቋንቋ ዕውቀት እንዲዳብርና ቋንቋውንም በጥሩ ሁኔታ ለማስተማር የሚያስችለውን ዕውቀት እንዲያገኙ ይረዳቸዋል፡፡
- ኢንዳክቲቭ ዘዴን ተጠቅሞ ሰዋሰውን ማስተማር የተማሪዎች ሰዋሰው የመማር ፍላጎት ለማጎልበት ያለውን ጥቅም መምህራን እንዲረዱ ያስችላል፡፡
- ለተማሪዎች፡- በኢንዳክቲቭ ዘዴ መማር የሰዋሰው ዕውቀታቸውን እንዲያሳድጉ ያግዛል፡፡

- ለአጥኚዎች፡- ወደፊት ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያለው ጥናት ለሚያጠኑ ተመራማሪዎች ሰዋሰውን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር ያለውን ጠቀሜታ ተረድተው ከፍ ያለ ጥናት እንዲያካሂዱ እንደ መረጃ ምንጭነት ያገለግላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የተካሄደው በኦሮሚያ ክልል በጂማ ዞን ሊሙ ኮሣ ወረዳ በሊሙ ገነት ከተማ (01) አንደኛ ደረጃ ት/ቤት በ2015 ዓ.ም የ8ኛ ክፍል ተማሪዎችን ኢንዳክቲቭ ዘዴን ተጠቅሞ ሰዋሰውን ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋሰው ዕውቀት የማጎልበቱን ሚና ከመፈተሽ ውጪ ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን አላካተተም በትምህርት ቤቱ አራት የስምንተኛ ክፍሎች ማለትም (A, B, C, D) ሲሆኑ፡ ከእነዚህ ውስጥ የአማርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች የሚማሩት በሁለት ክፍሎች ማለትም (A እና B ሲሆን ሌሎቹ ተማሪዎች (C እና D) አማርኛ ቋንቋ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑት በጥናቱ አልተካተቱም የአፍ-ፈት ተማሪዎች ላይ ጥናቱ የተካሄደ ሲሆን ቁጥራቸውም ሰማንያ (80) ነው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በቀላል እጣ አወሳሰድ 8A (40) 8B (40) ተማሪዎች የተወሰዱ ሲሆን፤ 8A (40) የቁጥጥር ቡድን እንዲሁም 8B (40) የሙከራ ቡድን በማድረግ ተወስደዋል፡፡

ጌታሁን (1989) እንደሚያስረዱት "ሰዋሰው" የሚለው ቃል ሁለት አሻሚ ፍቺዎን ይዞ ይገኛል፡፡ አንደኛው ፍቺ የሰው ልጅ የሚጠቀምበትን ቋንቋ ዕውቀት የሚጠቁመውና በሰው ልጅ አዕምሮ ውስጥ ያለውን ችሎታ የሚመለከት ነው፡፡ የሰው ልጅ ቋንቋውን ሊያውቅና ሊጠቀምበት የሚችለው ይህ ችሎታ ስላለው ነው፡፡ ሁለተኛው ፍቺ ደግሞ የቋንቋ ተመራማሪዎች ስለ ቋንቋ ስርዓትና መዋቅር የሚያደርጉትን ገለፃ የሚጠቁመው ነው፡፡ ይህ ጥናትም ሰዋሰው የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ተማሪዎችን እውቀታቸውን በኢንዳክቲቭ ዘዴ በክፍል ውስጥ ከማሻሻል አንጻር ከመጀመሪያው ፍቺ ጋር ብቻ አያይዞ የሚመለከት ነው፡፡

ጥናቱ ከሰዋሰው አቀራረቦች ውስጥ ኢንዳክቲቭ የሰዋሰው ዘዴን በሰፊው ለማየት ሞክሯል ፡፡ በጥናቱ ውስጥም ሁለት የቋንቋ መምህራንን ተሳታፊ አድርጓል፡፡ ጥናቱ የሚያተኩረው በኢንዳክቲቭ ዘዴ ሰዋሰውን ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋሰው ዕውቀት በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ማሳየት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በሊሙ ገነት 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ነው፡፡ ጥናቱ በአንድ ትምህርት ቤት ላይ ብቻ ማተኮሩ ውስንነት ይታይበታል፡፡ ምክንያቱም ጥናቱ በሙከራ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ከጊዜ እና ከአቅም አንፃር ሌሎች ትምህርት ቤቶችን ማካተት አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም ሰዋሰውን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን ዕውቀት ማጎልበቱን ከመፈተሽ ውጪ ሁሉንም የሰዋሰው ትምህርት አቀራረቦች በጥናቱ ውስጥ ስላላከተተ ጥናቱ ውስንነት ይታይበታል፡፡

## 1.8 የቁልፍ ቃላት ፅንሰ ሃሳቦች አጠቃቀም ብያኔ

ከጥናቱ ተላውጦች (Variables) ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ፅንሰ ሃሳቦች እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

- ኢንዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት ዘዴ፡፡ ሰዋሰዋዊ ህግጋትን በቀጥታ ሳይሆን ተዘዋዋሪ በሆነ መንገድ ተማሪዎች ለበርካታ ምሳሌዎችና ምልልሶች እንዲጋለጡ በማድረግ በትምህርትነት የሚቀርበውን ሰዋሰዋዊ ህግ እንዲያዉቁ የሚያደርግ የሰዋሰው ትምህርት ዘዴ ነው፡፡
- የሰዋሰው ዕውቀት፡- ተማሪዎች የቀረበላቸውን የሰዋሰው ትምህርት ይዘት ምን ያህል ተገንዝበውታል የሚለውን ለመመዘንና የሚቀርብላቸውን የሰዋሰው ትምህርት ላይ የሚያሳዩትን ለውጥ ይመለከታል፡፡
- ዲዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት ዘዴ፡- ዲዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት ዘዴ ከአንድ የቋንቋ ህግ በመነሳት (ከሰዋሰዋዊ ህጉ) ህጉን ተንትኖ በማረጋገጥ ወደ ህጉ ተመልሰው የሚደርሱበት ዘዴ ነው፡፡
- ሰዋሰው የመማር ፍላጎት፡- ተማሪዎች የቀረበላቸውን የሰዋሰው ትምህርት ሲማሩ በማስተማር ስልቱ ላይ ያላቸውን ቅድሚያ ተነሳሽነት ያመለክታል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2ክለሳ ድርሳናት እና የተዛማጅ ፅሑፎች ቅኝት

### 2.1 የሰዋሰው ምንነት

ባዬ (2000) ሰዋሰው የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ሲያብራሩ "ሰዋሰው" የሚለው ቃል በግዕዝ "መሰላል" ማለት ነው፡፡ መሰላል ከአንድ አነስተኛ ደረጃ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ቀስ በቀስ ለመውጣትና ለመውረድ የሚያስችል መሳሪያ ነው፡፡ የአማርኛ ሰዋሰው ሲባልም የአማርኛን የድምፆች ዓይነት አፈጣጠር አቀነጃጀት የአማርኛን ቃላት አይነት፡ አመሰራረትና አቀነጃጀት እንዲሁም የሀረጋቱን አይነትና የአወቃቀር ስርዓት ደረጃ በደረጃ የሚያሳይ የዕውቀት ዘርፍ ነው፡፡ ድምፅ ከድምፅ ጋር ተቀናጅቶ ቃልን ቃል ከቃል ጋር ተቀናጅቶ ሀረግን፣ እንዲሁም ሀረግ ከሀረግ ጋር ተዋቅሮ ዓረፍተ ነገርን ደረጃ በደረጃ የሚፈጥርበትን ሥርዓት የሚመለከት ጥበብ ነው፡፡" ከዚህ ብያኔ መረዳት የሚቻለው ሰዋሰው በቋንቋ ውስጥ የሚገኙት ድምፆች በተለያዩ ሁኔታዎች ተሰባጥረው ቃላትን፣ ቃላትም በተራቸው ሥርዓት ባለው መንገድ ተቀናጅተው ሐረጋትን፤ ሐረጋትም ተቀናጅተው ዐረፍተነገር የሚመሰረትበትን ሁኔታ የሚመረምር ሳይንስ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ መለሰ (2008) በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር የታተመውን የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993) ዋቢ በማድረግ እንደሚያስረዱት ሰዋሰው የቃላት አመሰራረትና የዐረፍተነገር አሰካክ ስርዓት ወይም ሕግ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር Ur (1988) የሰዋሰውን ምንነት እንደሚያስረዱት ሰዋሰው በደምሳሳው ቃላት ወይም ጥቂት ቃላት ረዘምያለ ትርጉም ሰጪ አሐዶችን የሚመሰርቱበት መንገድ ነው፡፡ይህ አመለካከት ከላይ ከተጠቀሱ አመለካከቶች የሚለየው ለሰዋስው የሚሰጠውን ብያኔ ከዐረፍተ ነገር አመሰራረት ጋር ብቻ ያስተሳሰረ መሆኑን ነው፡፡

የእንግሊዝኛው ኮንተምፖራሪ መዝገበ ቃላት (2001) ሰዋሰው ምንነት ሲገለፅ ቃላት ቅርፃቸውን በመቀያየር ዐረፍተነገር የሚመሰርቱበት ህግ ወይም ይህን ህግ ለመጠቀም የምናጠናበት ነው ይለዋል፡፡ Povjakalova (2012) Skirivner (2003) ን በመጥቀስ ሰዋሰው ማለት ደረቅ የእውነቶች ዝርዝር ሳይሆን በአዕምሮአችን ያለና ህይወት ያለው ሌሎች ሰዎች የሚናገሩትን ወይም የሚፅፉልንን የምንረዳበትና የምንግባባበትን ችሎታ የሚሰጠን ነገር ነው በማለት ያቀርበዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ሙሉ መልዕክት ለማስተላለፉም ሆነ ለመቀበል የግድ ዐረፍተነገር መገንባት አለበት፡፡ ይህ ደግሞ የቋንቋው ህግ ሆኖ እንደሚያገለግል ያስረዳል፡፡

Harmer (1987) ሰዋሰው በአንድ ቋንቋ ውስጥ የቃላት ወደተለያየ ቅርፅ መለዋወጥና ቃላትም በሥርዓት ተቀናጅተው ዐረፍተነገርን የሚመሰርቱበትን ህግ የሚያጠና ሳይንስ ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡

Jinyayun (2009) ሰዋሰውን የሚከተሉት ዝርዝር ነጥቦችን በማቅረብ ለመግለፅ ይሞክራሉ፡፡ ሰዋሰው ዐረፍተ ነገር የሚመሰረትበት ማሽን ነው፡፡ ሰዋሰው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ልክ አንድ ነገር በሂደት እንደሚሰራ በትምህርት ውስጥም ሰዎች ቃላትና ሀረጋትን እያስታወሱ እንዲያስቡ ያደርጋል፡፡ ሰዋሰውን ማስተማር የሕግ መመሪያ (ትዕዛዝ) ነው፡፡ ሰዋሰው ሊማሩት የሚችሉት ሕግ ነው፡፡ ይህም የመማር ማስተማር ገፅታ ራሱ የሚታወቅና ተሻጋጋሪ መሆኑን ያሳያል፡፡ ከዚህ የምንረዳው እንደ ቋንቋው ህግ ቃላትና ሀረጋት አልፎም ዐረፍተነገር የሚመሰረትበት ሂደት ነው፡፡ አስቀድሞም በቋንቋ ተናጋሪው ዘንድ የተደራጀና የተዘጋጀ በመሆኑ በእውነተኛ ተግባቦት ውስጥ ውስን ቢሆንም በመደበኛ ትምህርት ማግኘት እንደሚቻልና በትምህርት ሂደት በዕውቀትና በድርጊት ታግዞ ወደ ሌሎች ማሻጋገሪር የሚቻል የቋንቋ ህግ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

በካምብሪጅ ኢንተርናሽናል የእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት (1995) ውስጥ ሰዋሰው ቃላት ቅርፃቸውን የሚለውጡበትንና ከሌሎች ቃላት ጋር ተቀናጅተው ዓረፍተነገርን እንዴት እንደሚመሰርቱ የምናጠናበት ወይም የምንጠቀምበት ህግ እንደሆነ ነው፡፡ ማንኛውም ማህበራዊ ሕግ ደግሞ ሰው ማድረግ የሚገባውንና የማይገባውን የሚነግር ደንብ ወይም ስርዓት ነው፡፡ የቋንቋም ሰዋሰው ወይም ህግ ተናጋሪው ህብረተሰብ በመደበኛነት የሚጠቀመውን አጠቃቀም መሰረት አድርጎ "እንዲህ ይባላል" እንዲህ አይባልም" ብሎ የሚነግረን ነው፡፡ በአጠቃላይ የሰው ልጅ በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ የሚተዳደርበት ሕግ እንለዳው ሁሉ ሰዋሰውም ቋንቋን የሚገዛበት ህግ ሆኖ ከቋንቋ ድምፅ አወቃቀር እስከ ዐረፍተ ነገር አመሰራረት ያለውን ሥርዓት የሚገዛበት ሕግ ሆኖ እንደሚያገለግል መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.1.1 የሰዋሰው ትምህርት አስፈላጊነት

Jinyanyun (2009) ስለ ሰዋሰው ትምህርት አስፈላጊነት ሲገልፁ የሚከተሉትን ዝርዝር ጉዳዮችን ያቀርባሉ፡፡ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሰዋሰው መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም የመግባባት ብቃትን ለማግኘት የቋንቋው ሰዋሰዋዊ ዕውቀት መሰረት ስለሆነ ነው፡፡ የመግባባት ብቃትን ለማሳደግ ሰዋሰውንና ቃላትን እንዴት መጠቀም እንዳለብን ትክክለኛውን ማህበራዊ አቅጣጫ ያሳየናል፡፡ እንደ "Jinyanyun አባባል ከሆነ በማህበራዊ ህይወታችን ውስጥ ለምናደርገው ተግባቦት የቋንቋው የሰዋሰው ዕውቀት ሊኖረን እንደሚገባና ብቃቱን ለማሳደግ ሰዋሰው ጠቀሜታ እንዳለው ነው፡፡"

Borg (1999) መደበኛ የሰዋሰው ትምህርት በቀጥታ የተማሪዎችን የተግባቦት ችሎታ ለማዳበር ባይውልም በመለማመድ ተግባራዊ ማድረጉ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡ በተለይ መጀመሪያ ስለሚማሩት ነገር ያውቃሉ፡፡ የሰዋሰው ትምህርት ከተማሪዎች ስህተት ጋር ግንኙነት ስላለው በስህተታቸው ላይ የተመሰረተ የሰዋሰው ትምህርት ስለሆነ የመምህሩን የተለያዩ አካሄዶችን ሊወሰን ስለሚችል እንዲሁም ተማሪዎች ለራሳቸው ስህተታቸውን እንዲያውቁ ስለሚያደርግ ነው ይላሉ፡፡

ከዚህ አገላለፅ በሰዋሰው ትምህርት ወቅት ተማሪውንም ሆነ መምህሩን የሚያግዝ መሆኑን ያሳያል፡፡ መምህሩ አካሄዱን እንዲወሰን ሲያደርገው ተማሪዎች ስለሚማሩት ነገር እንዲያውቁ ስህተታቸው የት እንገሆነ የሚጠቁምና ስህተታቸውንም በተማሩት መሰረት ራሳቸው እንዲለዩት እና እንዲያስተካክሉ ስለሚያደርጋቸው ጠቃሚነቱ የጎላ መሆኑን ያሳያል፡፡

ጌታሁን (1989) ስለሰዋሰው ትምህርት አስፈላጊነት የሰጡትን ትንታኔ እንደሚከተለው ማየት ይቻላል፡፡ አንድ የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ትክክለኛ የሆነ ዕረፍተ ነገርን ትክክል ካልሆነው ለይቶ ሊናገር ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ትክክለኛ ዐረፍተ ነገር ነው ያለውን ትክክል ለመሆኑ ስህተት ነው ያለውን ስህተት የሆነበትን ምክንያት ሊናገር አይችልም፡፡ ምክንያቱም ሊናገር የሚችለው ቋንቋውን አቀላጥፎ መናገር የሚችለው ሳይሆን የቋንቋውን ሥርዓት የሚያውቀው ባለሙያ ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ነው ቋንቋን መናገር መቻልና ስለቋንቋ ማወቅ የተለያዩ ናቸው የሚባለው፡፡ ስለቋንቋው ለማወቅ የሚያበቃው ደግሞ ሥርዓት (የሰዋሰው) ትምህርት ነው፡፡ ስለዚህ አንድ የቋንቋ መምህር ተማሪው የክህሎትም የሥርዓትም ችሎታውን እንዲያዳብር ማድረግ ይጠበቅበታል ይህንንም ለማድረግ መምህሩ ራሱ ለክህሎት ብቻ ሳይሆን ለዘመናዊ ሥርዓት ትምህርትም መጋለጥ አለበት፡፡ ከዚህ የመንረዳው አንድ ቋንቋ ተናጋሪ ትክክለኛ የቋንቋውን ሥርዓት የበለጠ ሊያውቅ የሚችለው በዘመናዊ ትምህርት ሲያዳብረው እንደሆነና መምህሩም ቢሆን የክህሎትም ሆነ የሥርዓት ችሎታውን ከዘመናዊ ትምህርት ማግኘት እንደሚችል ነው፡፡

ባዬ (1987) ላይ የሚከተለውን ሃሳብ ያቀርባሉ የቋንቋውን አጠቃቀም ከነሥርዓቱ የሚያውቅ ሰው መኪና አነዳድን እና የመኪና አካላትን አሰራር እንደሚያውቅ መካኒክ ሾፌር የሚቆጠር ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሾፌር ደግሞ የትራፊክን ህግ ጠብቆ እንዲያሽከረክር ከሰለጠነ ሾፌር የበለጠ የመኪናን አነዳድ ማለትም ያጠቃቀም ዕውቀት ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ ከተራ አሽከርካሪ ጋር አይመደብም፡፡ ከዚህ ልንረዳ የሚገባን ዓቢይ ቁም ነገር ቋንቋን ተምሮ ለማስተማር ለተዘጋጀ ሰው የሰዋሰው ትምህርት ያለውን ጠቀሜታ ነው፡፡ ይህ ከሆነ አቀራረቡንም ማወቅ የሚገባን እንደሆነ ያስረዳናል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች የሰዋሰው ዕውቀት በአግባቡ ያገኙ

ዘንድ የመማሪያ መፅሐፋቸው ተማሪ አሳታፊነቱ ተጠብቆ መዘጋጀት እንዳለበትና አዘጋጆቹም ሆኑ በተግባር ላይ የሚያውሉት መምህራን በቋንቋ መጠቀም ብቻ ሳይሆን ስርዓቱን ጠንቅቆ ማወቅ እንደሚገባቸው ነው፡፡ ለተማሪዎቻቸውም አስፈላጊውን ትምህርት ከመስጠት ባሻገር በቋንቋው መግባባት የሚያስችላቸው ደረጃ ሊያደርሳቸው እንዲችል አድርገው ማቅረብ ይገባቸዋል፡፡ ስለዚህ የሰዋሰው ትምህርት አንድን ቋንቋ የመግባባት ችሎታን ለማዳበርና ለማሻሻል የሚያስችል ዕውቀትና ችሎታ ሊያጎናፅፍ እንደሚችልና ተማሪዎች በትምህርት ቤትም ሆነ በማህበራዊ ሕይወታቸው ውስጥ ለመግባባት የመሳሰሉት ጠቀሜታዎች እንዳለው መረዳት እንችላለን፡፡ በተጨማሪም ማረው (2003፡40) የሰዋሰውን አስፈላጊነት አክለው ሲገልፁ የሰዋሰው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለውን ሚና አንድ እግርኳስ ተጫዋች ህግጋቱን ተከትሎ የሚጫወት ተጫዋች እና ህግጋቱን ሳያውቅ የሚጫወት ተጫዋች ጋር በማነፃፀር ይገልፃሉ ከዚህ ሃሳብ የምንረዳው ማንኛውም የቋንቋ ተማሪ የተሟላ የቋንቋ ዕውቀት ሊያገኝ የሚችለው ክህሎቱን ብቻ ሳይሆን ስርዓቱን ማለትም የቋንቋውን ሳይንስ ጭምር ሲገነዘብ መሆኑን ነው፡፡

Larsen (1997:18-19) እንደሚገልፁት "በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሰዋሰው አስፈላጊ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ቋንቋን በትምህርትነት ከማቅረባችን በፊት የቋንቋውን ተፈጥሮ አሰራርና ባህሪያት ማወቅ ይጠበቅብናል፡፡ ከቋንቋ ባህሪያት ውስጥ ደግሞ አንዱ ሥርዓቱ ነው፡፡ ስርዓቱ የሚጠናው ደግሞ በሰዋሰው ትምህርት ነው፡፡" በማለት የሰዋሰው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በተገለፁት ምሁራን ጥናት ቋንቋን በመማር ውስጥ ሰዋሰውን በጥልቀት ማወቅ ወሳኝ እንደሆነ ምሁራኑ ይስማማሉ፡፡

## 2.1.2 የሰዋሰው ትምህርት አቀራረቦች

የተለያዩ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች እንዳሉ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ ማረው (2003) እንደሚያስረዱት የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ዘዴን አስመልክቶ አንድ አይነት አቋም እንዳልተያዘ ያስረዳሉ፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ሁሉንም ሰዋሰዋዊ ህግጋት በተገቢው መልኩ ለማስተማር የሚያስችል አንድ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ባለመኖሩ ነው፡፡ በመሆኑም አንድን የቋንቋ ሰዋሰው ለማስተማር የተለያዩ አቀራረብ አማራጮች አሉ፡፡ እነዚህ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎችም፡- ዲዳክቲቭ የሰዋሰው አቀራረብ ዘዴ ኢንዳክቲቭ የሰዋሰው አቀራረብ ዘዴ፣ እና ውህዳዊ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ናቸው፡፡

### 2.1.3 ኢንዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት ዘዴ

Mohammed and Etal (2008): Mouton 2004)ን በመጥቀስ እንደሚያስረዱት ኢንዳክቲቭ ዘዴ የቋንቋውን አገባብ መሰረት በማድረግ የተተኳሪውን ቋንቋ ህግ በተግባር የተደገፉ ምሳሌዎችን በመገልገል ማቅረብ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ የዚህ ዘዴ ሂደት ሁኔታዎችን በማመቻቸትና ምሳሌዎችን በማመንጨት ከምሳሌዎቹም በመነሳት ተማሪዎች ወደ አጠቃላይ ሕግ በራሳቸው መንገድ እንዲሄዱ የሚያግዝና የመምህሩ እገዛም ወደ ህጉ ለመድረስ አስተዋፅኦ የሚያደርግ መሆኑ ነው፡፡

ማረው (2003፡42) "ኢንዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት ዘዴ ከበርካታ ተጨባጭ ምሳሌዎች በመነሳት ወደህጉ መድረስ ወይም ምሳሌዎቹን መሰረት በማድረግ ህግ ማውጣት የሰዋሰው ትምህርት ዘዴ ነው፡፡" ሲሉ Thornosbury (1999) ፣ እና Ellis (1993) ዲዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት ዘዴ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ህግጋትና ቅርፆች ለቋንቋ ተማሪዎች በቀጥታ አያቀርቡም፡፡ ከዚህ ይልቅ ለተማሪዎች እንዲቀርቡ የተፈለጉ ሰዋሰዋዊ ቅርፆች በምንባብ ወይም በምልልስ ውስጥ ተካተው ይቀርባሉ፡፡ ተማሪዎችም ከምንባቦች ወይም ከምልልሶች ውስጥ ሰዋሰዋዊ ህግጋትን ፈልገው ያወጣሉ፡፡ በመሆኑም በትምህርቱ መጀመሪያ ላይ ተማሪዎች በሚቀርብላቸው ምልልስ ወይም ምንባብ ውስጥ በተካተቱ ሰዋሰዋዊ ጉዳዩች ከሚያተኩሩ ይልቅ ሊተላለፉ በተፈለገው መልዕክት ላይ እንዲያተኩሩ ይደረጋል፡፡ በማለት ያስረዳሉ፡፡

Krashen (1982) እንደሚያሳዩት ቋንቋ ለተግባቦት ዓላማ መዋል አለበት የሚለው እንቅስቃሴ አራማጆች (ለምሳሌ Brunfit እና Jonson 1979) በውጭ /በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ከመደበኛው የሰዋሰው ትምህርትና ስህተትን ከማረም ይልቅ መልዕክት ተኮር ለሆነው የሰዋሰው ትምህርት ዘዴ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል የሚል አመለካከት አራምደዋል፡፡ በተመሳሳይ Dafti እና Williams 1998 እንደሚያስረዱት ሰዋሰው በራሱ ግብ ሳይሆን ወደ ግብ የሚያደርስ ስልት በመሆኑ አንድምታዊ በሆነ ስልት መቅረብ ይኖርበታል፡፡

Parichant (2009) Krashen (2002)ን ጠቅሰው ሲያስረዱ የኢንዳክቲቭ ዘዴ ችግሮችን የሚፈታው በሚከተሉት ምክንያቶች እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የቋንቋውን አገባብ መሰረት በማድረግ የዐረፍተ ነገር መዋቅሮችን በተግባር ስለሚማሩ ከሚተገብሩት ነገር እውነተኛውን ህግ ያመነጫሉ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የኢንዳክቲቭ ዘዴ ከሁለተኛ ቋንቋ ለመዳና መማር ጋር ይመሳሰላል፡፡ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ ንድፈ ሃሳብ ተማሪዎች ቋንቋን የሚማሩትና የቋንቋውን ሰዋሰው በተከተለ መልኩ ዐረፍተነገሮችን መመሰረት የሚችሉት

ህፃናት የመጀመሪያ ቋንቋቸውን በንቃት አልባ በሚለምዱበት ሂደት ነው፡፡ በዚህ ሂደት መሰረት ትኩረት የሚያደርገው በቃላት ቅንብር ላይ ብቻ ሳይሆን በተላሚው ቋንቋ መጠቀም መቻል ላይ ነው፡፡ ይህ በመሆኑ በተማሪዎች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግና የቋንቋውን ሰዋሰው ህግጋት በገሃዳዊ አቀራረብ ዘዴ ማስተማር አይተኮርባቸውም፡፡ Parichart (2009)

Alghazali, 2006) Varkeyin (1995)ን ዋቢ አድርገው እንደሚገልፁት በኢንዳክቲቭ አቀራረብ ዘዴ ሂደት ከታወቀ ነገር በመነሳት ያልታወቁ ሰዋሰዋዊ ህግጋትን መፈለግ ሲሆን ከታወቀ ነገር በመነሳት ያልታወቁ ሰዋሰዋዊ ህግጋትን በመፈለግ ነው የሚቀርበው፤፤ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

1- ተማሪዎች አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡
2- ተማሪዎች በራስ መተማመናቸው እንዲጨምር ያደርጋል፡፡
3- ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው እንዲሰሩና ሁሉንም ነገር ከመምህሮቻቸው እንዳይጠብቁ ያደርጋቸዋል፡፡
4- ይህ አቀራረብ ተማሪዎች ከተለያዩ ምሳሌዎች ሰዋሰዋዊ ህግጋትን ፈልገው የማውጣት ጥረት እንዲያደርጉ ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ለራሳቸው ፈልገው የሚያገኙት ሰዋሰዋዊ ህግ ሁሌም በውስጣቸው ተቀርፆ ይኖራል፡፡
5- የመማሪያ ክፍሎች አስደሳችና በተለያዩ ተግባራት የተሞሉ እንዲሆኑ ያስችላል፡፡

### 2.1.4 በኢንዳክቲቭ ዘዴ ሰዋሰው ማስተማር ላይ ምሁራን ያላቸው ዕይታ

Mohammed and Etal (2008) Wong (2012)ን በመጥቀስ እንደሚያስረዱት የኢንዳክቲቭ ዘዴየሚያመለክተው የተተኳሪውን ቋንቋ ህጎች ከሚቀርብላቸው ምሳሌና አገባብ በመነሳት በራሳቸው የቋንቋውን ህግ እንዲፈለጉ የሚያስተዋውቅ ነው፡፡ በተጨማሪም በዚህ ዘዴ ውስጥ ከሁኔታዎች በመነሳትና ምሳሌዎችን በመጥቀስ በራሳቸው ወደ ማጠቃለያ የሚደርሱበት ወይም በመምህር እገዛ ህጎችን ለማጠቃለል የሚያስችላቸው ዘዴ ነው፡፡

በታይዋን በተደረገው በሙከራ ላይ የተመሰረተ ጥናት እንደሚያመለክተው ኢንዳክቲቭ ዘዴ ለተማሪዎች የበለጠ ውጤታማ እንደሚያደርጋቸው ተገልጧል፡፡ ለምሳሌ Heron እና Tomaselo, (1992) የፈረንሳይኛ ሰዋሰዋዊ መዋቅር በመማር ላይ የሚገኙ በአሜሪካ ኮሌጅ ውስጥ በሚማሩ ሃያስድስት የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች ላይ ኢንዳክቲቭና ዲዳክቲቭ ዘዴዎችን ተጠቅሞ በማስተማር ጥናት አካሂደዋል፡፡ በኢንዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር ሂደት ላይ ተማሪዎች ቃላዊ በሆነ መልኩ መዋቅሮችን እንዲለማመዱ ተደረገ፡፡ ከዚያም በጥቁር ሰሌዳ ላይ ዐረፍተነገሮችን በመመስረት ፅፈው አመልክተዋል፡፡ በዚህም የተነሳ ተማሪዎች

ተተኳሪውን መዋቅር በተመለከተ ዓላማቸው ከግብ መድረሱን በራሳቸው እንዲለዩ አስችሏቸዋል፡፡ በሌላ መንገድ በዲዳክቲቭ ማስተማር ዘዴ ሂደት መምህሩ በፅሁፍ ተተኳሪውን ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ህጎች በማብራራት ለተማሪዎች አቀረቡ፡፡ በተደረገው ድህረ ትምህርት ፈተናም በኢንዳክቲቭ ዘዴ የተማሩት የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ በሌላ በኩል Wang (2012) በታይዋን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ሰማንያ አንድ ተማሪዎችን ያሳተፈ ጥናት አካሂደዋል ጥናታቸውም ትኩረት ያደረገው በጅምሩ የቀሩ ቃላትን አብረዋቸው በሚሄዱ ቃላት በማሟላት (collection patterns) መማር ላይ ነው፡፡ በጥናቱ እንደ ተመለከተው በኢንዳክቲቭ ዘዴ የተማሩት ተማሪዎች በዲዳክቲቭ ዘዴ ከተማሩት ተማሪዎች የበለጠ ውጤታማነት ታይቶባቸዋል፡፡ በተለይ ዝርው ድርሰት በመፃፍ ሂደት በኢንዳክቲቭ ዘዴ የተማሩት የቋንቋውን ሰዋሰው ጠብቆ በመፃፍ ረገድ ተሽለው ተገኝተዋል፡፡ ከባድ በሆኑ ልምምዶች ላይ ግን በሁለቱ ቡድኖች መካከል ምንም ልዩነት አልታየም፡፡

Wang (2012) የተለያዩ ባለሙያዎችን በመጥቀስ እንደሚያስረዱት የተወሰኑ የዲዳክቲቭ ዘዴ ደጋፊዎች የኢንዳክቲቭ ዘዴ በትምህርታቸው ደከም ለሚሉ ተማሪዎች ከባድ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ Iyusubel (1974): karol (1964) በሌላ መንገድ shafer (1989) እንደሚያስረዱት ኢንዳክቲቭ ዘዴ ተጠቅሞ በማስተማር በእስፓንኛ ቋንቋትምህርት ክፍለ ጊዜበታየው ውጤት ዘዴው በሁሉም ተማሪዎች ዘንድ እኩል ነው፡፡ በ" shafer " ጥናት አራት የዐረፍተ ነገር መዋቅሮችን ለስፖንኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ አዘጋጅተው ተማሪዎቹን በዲዳክቲቭና ኢንዳክቲቭ ዘዴ ሶስት መቶ አሥራ ዘጠኝ ተማሪዎች ከተለያዩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመምረጥ እንዲማሩ ተደረገ የጥናታቸው ውጤት እንደሚያመለክተው ከሆነ በኢንዳክቲቭ ዘዴ የተማሩት በሁሉም ደረጃ ያሉ ተማሪዎች በዲዳክቲቭ ዘዴ ከተማሩ ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ ሆኖም በሁለተኛ ደረጃ (በትምህርታቸው ደከም የሚሉ እና ጠንካራ ተማሪዎች) መካከል ምንም የጎላ ልዩነት አልታየም፡፡ እንዲያውም በትምህርታቸው ደከም የሚሉ ተማሪዎች በኢንዳክቲቭ ዘዴ ሲማሩ የበለጠ ተጠቃሚነታቸው ጎልቶ ታይቷል፡፡ wang (1989) በአጠቃላይ ከላይ wang (2012) የተለያዩ ባለሙያዎችን በመጥቀስ (shafer 1989 Tomaselo, 1992) ለመግለፅ እንደቻለው ኢንዳክቲቭ ዘዴን ተጠቅሞ ሰዋሰው ትምህርት ማስተማር ይበልጥ ውጤታማ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ ነገርግን ዘዴውን አስቀድሞ በመጠቀሙ ሂደት ወጥ የሆነ አቋም የያዙ አይመስሉም፡፡ ይህ ጥናትም በኢንዳክቲቭ ዘዴ ሰዋሰውን ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋሰው ዕውቀት በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ይመረምራል፡፡

### 2.1.5 ዲዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት ዘዴ

Mohammed and Etal (2008) wang (2012)ን በመጥቀስ እንደሚያስረዱት በዲዳክቲቭ ዘዴ ሰዋሰው ማስተማር ሂደት መጀመሪያ የቋንቋውን ህግ ለተማሪዎች በማስተዋወቅ የሚያቀርቡበት ስልት ነው፡፡ ከዚያም በተማሪዎች ህጉ እንዲተገበር በሙከራ /Expermental study/ ላይ የተመሰረቱ ጥናቶች በዲዳክቲቭ ዘዴ ሰዋሰው ማስተማር ለተማሪዎች ውጤታማነት መሰረት የሚጥል መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ ማረው (2003፡42) "ዲዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ከአንድ የቋንቋ ሕግ በመነሳት ህጉን ተንትኖ በማረጋገጥ ወይ ህጉ ተመልሶ መድረስ ነው፡፡" ሲሉ፤ Fortune (1992) ዲዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ስለ ቋንቋ ህጎች ገለፃና ማብራሪያ የሚቀርብበት ነው፤ ይላል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ Harmer (1987) ዲዳክቲቭ የሰዋሰው ትህርት አቀራረብ መምህሩ ሰዋሰዋዊ ህጎችን እና ማብራሪያዎችን በግልፅ ያቀርባል፡፡ ይህ በመሆኑም ተማሪዎች ከሚማሩት ቋንቋ ህጋጋት ጋር ፊት ለፊት ይገናኛሉ በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከላይ ከተለያዩ መምህራን ከቀረበው ሃሳብ ለመረዳት የሚቻለው በዲዳክቲቭ ዘዴ ሰዋሰው ማስተማር ማለት በመጀመሪያ የተተኳሪውን ቋንቋ ሰዋሰው ህግ በመምህሩ አማካይነት ማስተዋወቅና ህጉን ተንትኖ በማረጋገጥ ወደ ህጉ ተመልሶ መድረስ ከዚያም በተማሪዎች በተግባር እንዲውል የማድረግ ዘዴን ያመለክታል፡፡ በሌላ አነጋገር ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የማቅረብ ዘዴ እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል፡፡

### 2.1.6 በዲዳክቲቭ ሰዋሰው ማስተማር ላይ ምሁራን ያላቸው ዕይታ

Ellis (1993) እና Azer (1989) እንደሚገልፁት ዲዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት ዘዴ የቋንቋ ተማሪዎችን በቋንቋ ለመዳ ሂደት ወሳኝ የሆነውን መሰረታዊ የሰዋሰው ዕውቀት እንዲያገኙ የሚያስችል የአቀራረብ ዘዴ ነው፡፡ እነዚህ ምሁራን ይህ የሆነበትን ምክንያት ሲያስረዱ "አንድ የቋንቋ ተማሪ መሰረታዊ የሆነውን ሰዋሰዋዊ ዕውቀት ካላገኘ በስተቀር ቃላትን አቀናጅቶ ውጤታማ ተግባቦት ለመመስረት ይቸገራል፡፡" ይላሉ፡፡ ይህን ተከትሎም፡ Fotos (1994) እንድምታዊ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ መዋቅሮች እንዲለምዱና በተግባቦት ሂደት ትክክለኛ (Accuracy) እንዲሆኑ ከማስቻሉም ባሻገር መልዕክት ተኮር ለሆነ አንብቦ የመረዳት ሂደት (Meaning focused Comprehension)

እና የታላሚውን ሰዋሰው ለማፍለቅ ምቹ ሁኔታዎችን እንደሚፈጥር ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም አንድምታዊ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ቋንቋን በመቆጣጠር ሂደት አዎንታዊ ሚና አለው፡፡ Krashen (1982) እንደሚያስረዱት አንደምታዊ የሰዋሰው ዕውቀት የተወሰኑ የቋንቋ ችሎታዎችን ይቆጣጠራል፡፡ በማለት አመልክተዋል፡፡ በሌላ በኩል ገሃዳዊ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ውስንነቶች አሉት፡፡ የቋንቋውን ሰዋሰው በግልፅ የሚያቀርበው ስልት መምህር መራሽ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲስፋፋ ያበረታታል፡፡ ይህ በመሆኑም የመምህሩ የንግግር ጊዜ በተማሪው ንግግር ከሚሸፈነው ጊዜ የሰፋ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ይህም የተሳለጠ ትምህርት እንዳይኖርና ተማሪዎች በተለያዩ ተግባቦታዊ ተግባራት እንዳይሳተፉ እንቅፋት ይሆናል፡፡ (Thombury 1999) በማለት ያስረዳሉ፡፡

Akinbote (2010) ዲዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት ዘዴ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ላይ የሚኖረውን ሚና ለመፈተሽ ሁለት መቶ አሥራ ዘጠኝ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን የጥናቱ ተሳታፊ አድርጓል፡፡ በተገኘውም ውጤት በዲዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የተማሩ ተማሪዎች በቅደመ ሙከራና በድህረ ሙከራ ፈተናዎች ከፍተኛ አማካይ ውጤት (26.30) አስመዝግበዋል፡፡ ጥብቅ ቡድኑ ያስመዘገበው አማካይ ውጤት ዝቅተኛ (16.82) ሆኗል፡፡ ይህ ውጤትም ዲዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ የሚሻሻል መሆኑን ያሳያል፡፡

Lin (2007) በታይዋን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ላይ ባካሄዱት ጥናት ውስጥ ስድሳ አራት ተማሪዎች በናሙናነት ተመርጠው እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በዲዳክቲቭና በኢንዳክቲቭ ዘዴዎች ለአሥራ ሁለት ሳምንታት የእንግሊዝኛ የአንቀፅ ጊዜያትን ተምረዋል፡፡ በኢንዳክቲቭ ዘዴ መምህሩ ለተማሪዎች ህጎችን በገሃድ አልገለፁላቸውም፡፡ በዚህ ፋንታ ከተሰጣቸው የመማሪያ ቁሳቁስ ሰዋሰዋዊ ዐረፍተ ነገሮች ተተኳሪውን ህግ እንዲገነዘቡ አድርጓል፡፡ ለዲዳክቲቭ ዘዴ ቡድን በመምህሩ ለተማሪዎች የተተኳሪውን ህግ እንዲገልፁላቸው ተደረገ ለተማሪዎቹ የቀረበላቸውን የሰዋሰው ህግ መሰረት ያደረገ ጥያቄም ቀርቦላቸዋል፡፡ የሁለቱ ዘዴዎች የድህረ ፈተና ውጤት እንደሚያመለክተው ከሆነ የዲዳክቲቭ ዘዴ ከኢንዳክቲቭ ዘዴ በበለጠ መልኩ የሰዋሰው ህጎችን እንደተገነዘቡ ያመላክታል፡፡ በሌላ በኩል ዲዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ውስንነቶች አሉት የቋንቋውን ሰዋሰው በግልፅ የሚያቀርበው ስልት መምህር መራሽ የመማር ሂደት እንዲስፋፋ ያበረታታል፡፡ ይህ በመሆኑም የመምህሩ የንግግር ጊዜ በተማሪው ንግግር ከሚሸፈነው ጊዜ የሰፋ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ይህም ተማሪዎች በተለያዩ ተግባቦታዊ ተግባራት እንዳይሳተፉ

እንቅፋት ይሆናል Thomsbury (1999):: በተጨማሪም ማረው (2003) እንደሚያስረዱት የሰዋሰው ትምህርት ዋና ዓላማ ተማሪዎቹ ቋንቋውን በአግባቡ እንዲጠቀሙበት ከማስቻል ውጪ አይሆንም፡፡ ይሁን እንጂ በርካታ መምህራን በየማስተማሪያ ክፍሉ አብዛኛውን ጊዜ የሚያጠፉት ሰዋሰዋዊ ህግጋትና መደበኛ መዋቅሮችን በማለማመድ ነው፡፡ በመሰረቱ የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ተማሪዎቹ በራስ የመተማመን ችሎታቸውን አሳድገው በሚማሩበት ቋንቋ ማዘዝ እንዲችሉ የሚያደርጋቸው መሆን አለበት ሰዋሰዋዊ ህግጋትን ገለፃና የመደበኛ መዋቅሮች ልምምድ ግን ይህን ዓይነቱን ችሎታ አያመጣም፡፡

በአጠቃላይ ጌታሁን (1995) በመፅሐፉ መግቢያ ላይ እንደሚያስረዱት ሰዋሰው አንዳንድ ጊዜ ይህንን በል ይህንን አትበል ከሚልና በቃል ከሚጠና የህግጋት ጥርቅም ጋር ሲዛመድ ይታያል፡፡ ይህ የጥንታዊ የቋንቋ ትምህርት ዘዴ ተፅእኖ ውጤት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ አሰራር በዘመናዊ ሰዋሰው ጥናት ተቀባይነት የለውም፡፡

## 2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት እና ግንኙነት ያላቸው ጥናቶች ሲቃኙ ከሀገር ውስጥ ሃይለማሪያም (2011)፣ ቲጃኒ (2007) እና መለሰ (2008) በሰፊው ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ሃይለማሪያም (2011) "Investigating Teachers' Application of the Inductive Approach to Grammar Teaching" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ ዓላማ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ዘዴን በተመለከተ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራንን በሰዋሰው ትምህርት ሂደት የኢንዳክቲቭ ዘዴ አተገባበር መመርመር ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በደቡብ ጎንደር ዞን በአዲስ ዘመን መሰናዶ ት/ቤት የሚገኙ የ11ኛ ክፍል መምህራንና ተማሪዎች ናቸው፡፡ በሃይለማሪያም ጥናት ከተማሪዎችና ከመምህራን በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያመለክተው አብዛኛውን ጊዜ መምህራን በሰዋሰው ትምህርት ውስጥ የሚጠቀሙት መምህር ተኮር የሆነው ዲዳክቲቭ ዘዴ መሆኑን ማወቅ ተችሏል ፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የመምህራን ኢንዳክቲቭ ዘዴ በሰዋሰው ትምህረት ውስጥ አጠቃቀሙ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ የሃይለማሪያም ጥናት ኢንዳክቲቭ ዘዴ በሰዋሰው ትምህርት ያለውን አስተዋፅኦ ስለሚጠቁም ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ይሁን እንጂ የሃይለማሪያም ጥናት በዓይነታዊ የመረጃ አተናተን ስልት በእንግሊዘኛ ቋንቋ ሰዋሰው ትምህርት ውስጥ ኢንዳክቲቭ ዘዴን አስመልክቶ የመምህራንን አተገባበር የሚቃኝ በመሆኑ በጥናቱ ዓላማ በጥናቱተሳታፊ እና በጥናቱ አካባቢ ከዚህ ጥናት ጋር ይለያያል፡፡

ቲጃኒ (2007) "ኢንዳክቲቭና ዲዳክቲቭ ዘዴዎችን አዋህዶ ሰዋሰው ማስተማር በተማሪዎች የሰዋሰው ዕውቀት ላይ የሚኖረውን ሚና መመርመር በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ

ዓላማ ኢንዳክቲቭና ዲዳክቲቭ ዘዴዎችን አዋህዶ ሰዋሰው ማስተማር በተማሪዎች የሰዋሰው ዕውቀት ላይ የሚኖረውን ሚና መመርመር ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን በሻምቡ ከተማ አስተዳደር በሻምቡ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በእድል ሰጪ ንሞና ዘዴ የተመረጡ 35 ተማሪዎች ናቸው፡፡ የቲጃኒ ጥናቱ ፍትነታዊ ሲሆን ከተማሪዎች በፈተናና በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያመለክተው ኢንዳክቲቭና ዲዳክቲቭ ዘዴዎችን አዋህዶ መጠቀም የተመሪዎችን የሰዋስው ዕውቀት እንደሚያጎለብት አመላክተዋል፤፤ ይህ ጥናትም በኢንዳክቲቭ ዘቀራረብ ዘዴ ሰዋሰውን ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋሰው ዕውቀት በማነሳሳት ረገድ ያለውን ሚና የሚፈትሽ በመሆኑ ከቲጃኒ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ይሁን እንጂ የቲጃኒ ጥናት ኢንዳክቲቭና ዲዳክቲቭ ዘዴን አዋህዶ አንድ ተጠኝ ቡድን ላይ ብቻ ስለሚያተኩር ፡ ይህ ጥናት ደግሞ በኢንዳክቲቭና በተለመደው አቀራረብ ዘዴ ሰዋሰውን ማስተማር " በተማሪዎች የሰዋሰው ውጤት ላይ ልዩነት ይኖረው ይሆን ?የሚለውን ስለሚዳስስ በጥናቱ ዓላማ፣ በጥናቱ ተለዋጭ፣ በጥናቱ ተሳታፊ በጥናቱ አካባቢ ከዚህ ጥናት ጋር ይለያያል፡፡

መለሰ (2008) "Amharic second Language Teaching pedagogical Grammas approaches, the case of oromia" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዷል፡፡ የጥናቱ ዓላማ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ የአማርኛ መምህራን በሰዋሰው ትምህርት ሂደት በኢንዳክቲቭ ዘዴ ላይ ያላቸውን አመለካከት የአማርኛ መምህራን በሰዋሰው ትምህርት ሂደት በኢንዳክቲቭ ዘዴ ላይ ያላቸውን አመለካከት መመርመር ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በምሥራቅና በምዕራብ ሸዋ ዞን የሚገኙ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚያስተምሩ መምህራን ናቸው፡፡ የመለሰ (2008) ጥናት በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያመለክተው አብዛኛዎቹ የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን ለኢንዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ታይቷል፡፡ ይሁን እንጂ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ዘዴን አስመልክቶ የቋንቋ መምህራን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ላይ ያላቸውን አመለካከት መመርመር ብቻ የተማሪዎችን ሰዋሰው ዕውቀት ያጎለብታል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ይህ ጥናት ኢንዳክቲቭ ዘዴ የሰዋሰው ትምህርት ለማስተማር ያለውን አስተዋፅኦ ስለሚጠቁም ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ይሁን እንጂ የመለሰ (2008) ጥናት በዓይነታዊ የመረጃ አተናተን ስልት ተጠቅሞ በኢንዳክቲቭ ዘዴ መምህራን ያላቸውን አመለካከት መመርመር ላይ ብቻ ስለሚያተኩር በጥናቱ ዓላማ ፣ በጥናቱ ተሳታፊና በጥናቱ አካባቢ ከዚህ ጥናት ጋር ይለያያል፡፡ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢ ግንኙነት ያላቸው በውጭ ሀገር ከተሰሩ ጥናቶች ውስጥ Wang (2002), Herron and Tomasello (1992)እና Alkambi (2004) ጥናቶች ይጠቀሳሉ፡፡

Wang (1999) በታይዋን ሀገር መምህራንና ተማሪዎች በሰዋሰው ትምህርት ላይ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ ጥናት አድርገዋል፡፡ በጥናቱም ተማሪዎች በኢንዳክቲቭ ዘዴ መማር እንደሚፈልጉ ሲገልፁ መምህራን በመማሪያ ክፍል ውስጥ መተግበር የሚፈልጉት ዲዳክቲቭ ዘዴን እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ Borg እና Bomis (2008)ን ዋቢ በማድረግ Wang (1999) እንደሚያስረዱት በ176 የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ባደረጉት ጥናት መምህራን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ላይ ጠንካራ እምነት እንዳላቸውና ሰዋሰውን ነጣጥሎ ማስተማር ላይ ያላቸው አመለካከት አሉታዊ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

Herron and Tomasello (1992) ኢንዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ፈረንሳይኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ያለውን ሚና ለመፈተሽ ሃያስድስት የኮሌጅ ተማሪዎችን የጥናታቸው ተሳታፊ በማድረግ የጥናቱን ተሳታፊዎች በሁለት ቡድን በመመደብ አንደኛውን ቡድን ተጠኝ ቡድን ሁለተኛውን ቡድን ጥብቅ (የቁጥጥር) ቡድን አድርጎ ተጠኝ ቡድኑ በኢንዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ እንዲሁም ጥብቅ ቡድኑ በመደበኛው አቀራረብ ከተማሩ በኃላ ተጠኝ ቡድኑ በተሰጠው የድህረ ሙከራ ፈተና የቀረቡትን ጥያቄዎች ከጥብቅ ቡድኑ በተሻለ ሁኔታ መልሷል፡፡ እኚሁ ምሁራን እንደሚገልፁት የተወሰኑ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮችን ለማስተማር ኢንዳክቲቭ የሆነው ዘዴ ስለቋንቋው ገለፃ ከሚያደርገው ተመራጭ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ Alkal barni (2004) በኦማን ሀገር በተለያዩ ሶስት አካባቢዎች በሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት ያሉ 220 መምህራንና 1050 ተማሪዎች እንግሊዝኛን እንደ ውጭ ቋንቋ በመማርና በማስተማር ላይ በሚገኙ ላይ ጥናት አካሂደዋል፡፡ በዚህም ተማሪዎች ሰዋሰውን በኢንዳክቲቭ ዘዴ መማር እንደሚፈልጉ ሲገልፁ መምህራን ደግሞ በዲዳክቲቭ ዘዴ ተጠቅመው ሰዋሰው የሚያስተምሩበትን እንደሚያስበልጡ ያስረዳሉ፡፡ Mo culture (2006) በስድስት ትምህርት ቤቶች የእንግሊዝኛ መምህራን እምነትና ተግባር ላይ ጥናት አድርገዋል የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያሳየው ከሆነ የሰዋሰው ትምህርት በጣም አስፈላጊ እንደሆነና የተማሪዎችን የሰዋሰው ዕውቀት ለማጎልበት የኢንዳክቲቭ ዘዴን መገልገል ውጤታማ እንደሚያደርግ ያስረዳሉ፡፡ ከላይ ከተቃኙ የውጭ ሀገር ጥናቶች መረዳት እንደሚቻለው ኢንዳክቲቭ ዘዴን ተጠቅሞ ሰዋሰውን ማስተማር እንደሚቻል ያመለክታል ፡፡ ከዚህም ሁሉንም በጋራ የሚያስማማ ውጤት አለመገኘቱን ለመረዳት ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው የባለሙያዎች ገለፃ መረዳት እንደሚቻለው ኢንዳክቲቭ ዘዴን ተጠቅሞ በሰዋሰው ትምህርት ውስጥ ውጤታማ መሆን መቻሉን ያመለክታሉ፡፡ ነገርግን ዘዴውን አስቀድሞ በመጠቀሙ ሂደት ወጥ የሆነ አቋም የያዙ አይመስሉም፡፡ ይህ ጥናትም በኢንዳክቲቭ ዘዴ ሰዋሰውን ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋሰው ዕውቀት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና ላይ በማተኮር የተሰራ ነው፡፡

ከላይ የተቃኙ የውጭ ሀገር ጥናቶች መረዳት እንደሚቻለው በኢንዳክቲቭ ዘዴ የሰዋሰው ትምህርት ለማስተማር ያለውን አስተዋፅኦ ስለሚጠቁሙ ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላሉ፡፡ ይሁን እንጂ በኢንዳክቲቭ አቀራረብ ላይ መምህራን እና ተማሪዎች ያላቸውን አመለካከት መመርመር ላይ ብቻ ስለሚያተኩር በጥናቱ ዓላማ በጥናቱ አሳታፊና ፣ በጥናቱ አካባቢ ከዚህ ጥናት ጋር ይለያያል፡፡ በመሆኑም ይህጥናት ኢንዳክቲቭ ዘዴን ተጠቅሞ ሰዋሰውን በማስተማር ዙሪያ በ1ኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ የተሰራ ነው፡፡

## 2.3 የጥናቱ ጽንሰ ሃሳብና ማዕቀፍ

በቋንቋ  ውስጥ የሰዋሰው ትምህርት ወደ መሰረታዊው የቋንቋ ዕውቀት ግብ ለማድረስ እንደ ጠንካራ መሸጋገሪያ ሆኖ ያገለግለል፡፡ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ መለያየትን መሰረት በማድረግ የተለያዩ ምሁራን የሰዋሰው ስልቶችን በተለያየ ምድብ ያቀርባሉ፡፡ Hayder (2012:179) እንደሚያስ ረዱት የሰዋሰው ስልቶችን፡- ጥንታዊ ሰዋሰው (Traditiona Grammar): መደበኛ ሰዋሰው (Formal Gramemar እና ስልት ተኮር ተግባራት ሰዋሰው (systemic functional Grammar) በማለት በሦስት ይከፈላሉ፡፡ ይላል

Kope (1993)ን ዋቢ በማድረግ Hayder (2012:179) እንደሚያብራራው ጥንታዊ ሰዋሰው መሰረት የሚያደርገው የጥንታዊ ሮማውያንና ግሪካውያን ቋንቋዎችን ነው፡፡ የዚህ የሰዋሰው ክፍል ትኩረት የሚሰጠው የቋንቋውን የቃልክፍሎች ለማጥናት ሲሆን ስልቱም ያለምንም አውዳዊ መሰረትነት የቋንቋን ቅርፆች ያቀርባል፡፡ ሁለተኛው የሰዋሰው ስልት መደበኛ ሰዋሰው (Formal Grammar) ሲሆን እንደ ጥንታዊ ሰዋሰው ሁሉ በቃል ክፍሎች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ትኩረቱም የአንድን ዐረፍተ ነገር መዋቅር በመተንተን ላይ ያተኩራል፡፡ ይህ መደበኛ ሰዋሰው "ሰዋሰው የአንድን ዐረፍተ ነገር መዋቅራዊ አደረጃጀት ሊፈቅዱ ወይም ላይፈቅዱ የሚችሉ ህጎች ስብስብ ነው፡፡" ከሚለው የChomsiky ንድፈ ሃሳብ ጋር የሚደጋገፍ ነው፡፡ ሶስተኛው የሰዋሰው ዓይነት ስልት ተኮር ተግባራዊ ሰዋሰው ሲሆን ከጥንታዊ ሰዋሰው ፈፅሞ የተለየ ነው፡፡ የዚህ ሰዋሰው ትምህርት አራማጅ በሲውዲን ዩኒቨርሲቲ የስነ ልሳን ፕሮፌሰር Halliday (2004:46) እንደሚያስረዱት ቋንቋ መልዕክት ማስተላለፊያ ነው፡፡ ሰዋሰው ደግሞ በቃላት አማካይነት መልዕክትን ማስተለለፍ የሚያስችል መሰረት ነው፡፡ ቋንቋንም ከማህበራዊ ግንኙነት መፍጠሪያነቱ አንፃር የሚፈርጅ ነው፡፡ በመሆኑም በሰዋሰው ትምህርት ውስጥ ሰዋሰው በማህበረዊ ግንኙነት ውስጥ ካለው አገልግሎት አኳያ ሊታሰብ ይገባል የሚል አቋም አለው፡፡ Halliday (2004:46) እንደ ገለፁት ስልትተኮር ተግባራዊ የሰዋሰው ትምህርት ቃላትን በአውድ በምንጠቀምበት ጊዜ ሊከሰት የሚችልን ችግር ያስወግዳል፡፡ በአጠቃላይ ይህ የሰዋሰው ትምህርት ዓይነት የሰውልጆች ማህበራዊ

ግንኙነታቸውን ለማጠናከር ያስችላቸው ዘንድ ሊከተሉት የሚገባቸውን የቋንቋ አጠቃቀም በማመላከት ላይ ያተኩራል፡፡ኢንዳክቲቭ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ሰዋስዋዊ ህጋጋትን በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ተማሪዎች ለበርካታ ምሳሌዎችና ምልልሶች እንዲጋለጡ በማድረግ በትምህርትነት የሚቀርበውን ሰዋሰዋዊ ህግ እንዲያውቁ የሚያደርግ የሰዋስው የትምህርት አቀራረብ በመሆኑ ስልት ተኮር ተግባራዊ የሰዋስው ስልትን መሰረት በማድረግ የተጠና ምርምር እንዲሆን ተደርጓል፤፤

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ክለሣ ድርሳናት ሰዋሰው ለሚለው ፀንሰ ሃሳብ የተለያዩ ብያኔዎች የተሰጡ ቢሆንም ሰዋሰው ቋንቋን በአግባቡ እንዲጠቀሙበት ወሳኝ ሚና ያለውና ያለሰዋሰው ውጤታማ የሆነ ተግባቦት ለማከናወን አስቸጋሪ መሆኑን የተለያዩ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረቦች መኖራቸውን እንዲሁም  የተለያዩ የቋንቋ ምሁራን የሰዋሰው ዓይነቶች ከተለያዩ መመዘኛዎች አንፃር እንደሚመደቡ አመላክተዋል፡፡ ከእነዚህ የተለያዩ የሰዋሰውም ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች ውስጥም ኢንዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት ዘዴ ተማሪ አሳታፊ የሆነና የሰዋሰው ትምህርት ተማሪዎች ቋንቋውን በአግባቡ እንዲጠቀሙበት ማስቻል በመሆኑ ከስልት ተኮር ተግባራዊ ሰዋሰው ንድፈ ሃሳብ ጋር የሚዶጋገፉ በመሆኑ፡፡ ይህ ጥናትም በተለይም በ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ሰዋሰውን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋሰውዕውቀት በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና በተግባር እና በሙከራ በመፈተሽ ላይ ያተኮረ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# 3. የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት በዓይነቱ መጠናዊ ሆኖ ሙከራዊ /Experimental/ የምርምር ስልት ተከትሎ የተከናወነ በተተኳሪው ትምህርት ቤት ጥናቱ በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ነው፡፡ ጥናቱ ባለሁለት ቡድን ቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና ስልትን ተከትሎ የተከናወነ ነው፡፡ ተውላጦቻችን በተመለከተ ኢንዳክቲቭና በተለመደው የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ እንደ  ነፃ ተላውጠ ሲሆን የሰዋሰው ዕውቀትና እና የመማር ፍላጎት ጥገና ተላውጦዎች ናቸው፡፡ ጥናቱ ሁለት የጥናት ተሳታፊ ቡድኖች ማለትም የቁጥጥር እና የሙከራ /Control and Eyperimental/ ያሉት ሲሆን በጥናቱ ለሚሳተፉ (40) የቁጥጥር (40) የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት ፈተና እና የድህረ ትምህርት ፈተና (pre and post test) ተሰጥቶአቸዋል፡፡ በጥናቱ ተሳታፊ ለሆኑ ተማሪዎች የክፍል ደረጃው መማሪያ መፅሐፍ መሰረት ያደረገ የትምህርት ይዘት በኢንዳክቲቭ አቀራረብ ሳይማሩና በዘዴው ከተማሩ በኃላ በተማሪዎች ላይ የሚታየውን ለውጥ መርምሯል፡፡ እንዲሁም ዘዴው የሚኖረውን ሚና በተመለከተ የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት ሰዋሰው የመማር ፍላጎት ለማወቅ የፅሁፍ መጠይቅ እንዲምሉ ተደርጓል፡፡ የፈተናና የፅሁፍ መጠይቅ ውጤቱን በመተንተን የተደረሰበት ማጠቃለያም ደረጃ በደረጃ እንደየአግባቡ ለመስጠት የተሞከረ ሲሆን ለፈተና እና ለመጠይቁ ተማሪዎች በቅድሚያ አስፈላጊውን ዝግጅት አድርገው በሃላፊነት እንዲወጡ አስፈላጊ የሆኑ ማብራሪያዎችን ለመስጠት ተሞክሯል፡፡

## 2.2 የጥናቱ ተሳታፊዎችና የንሞና ዘዴ

ይህ ጥናት የተካሄደው በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በሊሙ ኮሣ ወረዳ በሊሙ ገነት 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ነው፡፡ ይኸውም አጥኚው በዚህ ትምህርት ቤት በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት እያገለገለ ስለነበረ ነው፡፡ በመሆኑም የምርምሩን ሂደት በቅርብ ለመከታተል  በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ (purposive sampling) ተመርጧል፡፡ በከተማው ዙሪያ ያሉ ሌሎች 1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች አጥኚው ከሚኖረው አካባቢ ርቀው ስለሚገኙ የምርምሩን ሂደት በቅርበት ለመከታተል አመቺ አይደሉም፡፡ በመሆኑም በዚህ ትምህርት ቤት በቅድሚያ ከተማሪዎች ቤቱ አስተዳደርና ለጥናቱ አስተዋፅኦ ለሚያደርጉ አካላት የምርምሩን ዓላማ በማስረዳት ይሁንታቸውን በማግኘት ወደሥራ ለመግባት ተሞክሯል፡፡

የጥናቱ ተሳታፊዎች በ2015 ዓ.ም በሊሙ ገነት 1ኛ ደረጃ ት/ቤት እየተማሩ ያሉ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ትምህርት ቤቱ አራት የ8ኛ ክፍል የመማሪያ ክፍሎች ያሉት ሲሆን በእነዚህ ክፍሎች 210 ተማሪዎች ትምህርታቸውን ይከተላሉ፡፡ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ያሉት የ 8ኛ ክፍል ተማሩዎች ጠቅላላ 4 ክፍሎች ሲሆኑ ሁለቱ ክፍል የአማርኛ ተማሪዎች ሁለቱ ክፍሎች ደግሞ የኦሮምኛ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በቀላል ዕጣ አወሳሰድ ማለትም ሁለቱ ክፍሎች የአማርኛ ተማሪዎችን በመውሰድ 8A (የቁጥጥር ቡድን) እና 8B (የሙከራ ቡድን) እንዲሆን ተደርጓል፡፡ የክፍሎቹን ቁጥር በዚህ መልኩ መወሰን ያስፈለገው ጥናቱ በሙከራ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በአግባቡ ጊዜን ለመጠቀም ታስቦ ነው፡፡

### 2.2.1 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በጥናቱ ተተኳሪ የሆነው ትምህርት ቤት ውስጥ አምስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ይገኛሉ፡፡ ከአምስቱ መምህራን ውስጥ አንዱ የዚሁ ጥናት አቅራቢ በመሆኑ የተገኘውን ውጤት እንዲያርም አልተደረገም፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ውጤቱ ተአማኒነት እንዲኖረው ታስቦ ነው፡፡ ካሉት መምህራን ውስጥ ሁለቱ የዲግሪ ምሩቅ እና ሁለቱ የዲፕሎማ ምሩቅ ናቸው በመሆኑም ካሉት አራት መምህራን ሁለቱን መምህራን በትምህርታቸው ደግሪ ያላቸው ፈተናውን እንዲያርሙ ተደርጓል፡፡

## 2.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

በዚህ ጥናት መሰረታዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ ያስችላሉ ተብለው በተግባር ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ፈተና እና የፅሑፍ መጠይቅ ናቸው፡፡

### 2.3.1 ፈተና

በዚህ ጥናት በዋናነት ለመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ያገለገለው ፈተና ነው፡፡ ለዚህ ይረዳ ዘንድ በጥናቱ ለሚሳተፉ ተማሪዎች አንድ ፈተና በቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት እንዲፈተኑ ተደርገዋል፡፡ ፈተናዎቹ የክፍል ደረጃውን መማሪያ መፅሐፍ መሰረት አድርገው በአጥኚው ከተዘጋጁ በኃላ ጥናቱ በሚካሄድበት ሊሙገነት 1ኛ ደረጃ ት/ቤት አማርኛ ቋንቋን በሚያስተምሩ ሁለት መምህራን እንዲገመገሙት ተደርጓል፡፡

#### 2.3.1.1 ቅድመ ትምህርት ፈተና

በትምህርት ቤቱ ውስጥ ለሚጠኑ ተማሪዎች የቀረበላቸው የቅድመ ትምህርት ፈተና (pre-test) ቅድሚያ የተሰጠው ነው፡፡ ይህ ፈተና ተጠኚ ተማሪዎች አስቀድሞ ያላቸውን የሰዋሰው

ዳራዊ ችሎታ ለመለካት በሰዋሰው ውጤት ችሎታቸው መሰረት በችሎታ አቻ ወይም ተመጣጣኝ የሆኑ የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ብሎ ለመመደብ ያስቻለ ፈተና ነው፡፡ ፈተናው የክፍል ደረጃውን መማሪያ መፅሐፍ መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ሲሆን አራት ክፍሎች ያሉትን 25 ጥያቄዎች እንዲይዙ ተደርጓል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል 15 የምርጫ ጥያቄዎን የያዘ ሲሆን ይህም ምዕላዶችንና የቃል ክፍሎችን እና ግሶን መሰረት አድርጎ የቀረበ ጥያቄ ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል አምስት የአዛምድ ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን ጥያቄዎቹም የቃል ክፍሎችን በተገቢው ክፍት ቦታ የማስገባት ችሎታን መለካት መሰረት ያደረጉሆነው የቃላትን ተቃራኒ በመፈለግ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ ሶስተኛው ክፍል ሦስት ክፍት ቦታን ማሟላት የሚጠይቁ ጥያቀዎችን የያዘ ነው፤፤እነርሱም አረፍተ ነገርንናሐረግን የሚመለከቱ ናቸው፤፤ አራተኛው ክፍል ሁለት ጥያቄዎችን የያዘ ነበር፤፤ ጥያቄዎቹም ተዘበራርቀው የተቀመጡ ቃላትን አስተካክሎ ዓረፍተነገር መገንባትን የሚጠይቁ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ ፈተናው ለተማሪዎች ከመቅረቡ በፊት አስተማማኝነቱን ለመጠበቅ ጥናቱ በሚካሄድበት ትምህርት ቤት አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ መምህራን እንዲገመግሙት ተደርጓል፡፡ ፈተናው ከተገመገመ በኋላ ማስተካከያ ተደርጎ ተማሪዎቹ እንዲፈተኑ ተደርጓል፤፤

ፈተናውን የፈተኑት አጥኚውና የየክፍሎቹ መምህራን ተጠሪ ሲሆኑ የተዘጋጀውን ፈተና አስተማማኝነቱን ለመጠበቅ የጥናቱ ተሳታፊዎች ሰፊ ክፍል ውስጥ ለፈተና አመቺ በሆነ አቀማመጥ ተቀምጠው የሁለቱም ክፍሎች ተማሪዎች ፈተናውን እንዲፈተኑ ተደርገዋል፡፡ ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ 50 ደቂቃ ነው፡፡ ተማሪዎች ፈተናውን ሰርተው እንደጨረሱ የፈተናው መልስ ወረቀት በአጥኚው እና በየክፍሉ መምህር ተጠሪ አማካይነት ተሰብስቧል፡፡ ፈተናው ከመታረሙ በፊት ኮፒ በማድረግ በሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አማካይነት እንደ ጥያቄዎቹ ባህሪ የጋራ መስፈርት በማውጣት ታርሟል፡፡ ሁለቱ አራሚዎች ለእያንዳንዱ ተማሪ የሰጡት ውጤት ከተደመረ በኋላ ለሁለት ተካፍሎ የተገኘው አማካይ ውጤት የጥናቱ ተሳፊዎች ውጠት ተደርጎ ተመዝግቧል፡፡ አስቀድሞ እንደተገለፀው የቅድመ ትምህርቱ የፈተና ውጤት ተጠኚ ተማሪዎች በተመጣጣኝ ችሎታ የቁጥጥርና የሙከራ ቡድን ብሎ ለመክፈል የራሱ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

### 2.3.1.2 ድህረ ትምህርት ፈተና

ተጠኚዎች በአግባቡ በተሰጠው የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ከተማሩ በኋላ የሚሰጠው የፈተና ዓይነት ሲሆን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀው የተሰጠውን ትምህርት ነው፡፡ አጥኚው ትምህርቱ ከሚጠናቀቅበት ቀን አስቀድሞ በሰጠው ትምህርት አቀራረብና አተገባበር መሰረት በማድረግ የድህረ ትምህርት የፈተና ጥያቄዎችን አዘጋጅቷል፡፡ የድህረ ትምህርት ፈተናው ከቅድመ

ትምህርት ፈተናው ጋር ተመሳሳይ ሆኖ የተዘጋጀ ሲሆን የድህረ ትምህርት ፈተና ዓላማ ተደርጎ የተዘጋጀው ተማሪዎች በኢንዳክቲቭ ዘዴ የቀረበላቸውን ትምህርት ለስድት ሳምንት (ከታህሣሥ 01/04/ 2015 - ጥር 15/05/2015) እንዲማሩ ከተደረገ በኋላ ዘዴው በተማሪዎች የሰዋሰው ውጤት ላይ ያለውን ሚና ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡ ፈተናው የክፍል ደረጃውን መማሪያ መፅሐፍ መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ሲሆን አራት ክፍሎች ያሉት 25 ጥያቄዎን እንዲይዝ ተደርጓል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል 15 የምርጫ ጥያቄዎን የያዘ ሲሆን ይህም የቃል ክፍሎችን እና ግሶችን መለየትን ለመለካት የቀረበ ጥያቄ ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል አምስት የአዛምድ ጥያቄዎን የያዘ ሲሆን ጥያቄዎም የቃል ክፍልችን በተገቢው ክፍል ተመሳሳያቸውን በመፈለግ የሚሰራነው፤፤ሶስተኛው ክፍልሶስት ክፍት ቦታን ማሟላት የሚጠይቁ ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን ጥያቄዎቹ ዐረፍተነገርን እና ዐረፍተነገር በውስጡ ከሚይዛቸው ዋና ተዋቃሪ አካላት ሁለቱን (ስማዊ ሀረግ እና ግሳዊ ሀረግ) የመለየት አቅም የሚከተሉ ናቸው፡፡ አራተኛው ክፍል ሁለት ጥያቄዎን የያዘ ነበር፡፡ ጥያቄዎቹም ተዘበራርቀው የተቀመጡ ቃላትን አስተካክሎ ዐረፍተነገር መገንባት የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ይህ በአጥኚው የተዘጋጀው ፈተና እንደ ቅድመ ትምህርቱ ፈተና አማርኛ ቋንቋ በሚያስተምሩ መምህራን ከተገመገመ በኋላ በተሰጠው አስተያየት መሰረት ማስተካከያ ተደርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡ ይህ ፈተና የካቲት 1/06/2015 ከቀኑ 8፡00 እስከ 8፡50 በሁለት የመፈተኛ ክፍሎች በአጥኚውና በየክፍሎቹ መምህር ተጠሪ አማካይነት ተሰጥቷል፡፡

የፈተናው አስተራረምና አመዘጋገብ እንደቅድመ ትምህርት ፈተናው ሲሆን በዚህ ፈተና ከጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የተገኘ ውጤትም ከቅድመትምህርቱ ፈተና አንፃር የጎላ ልዩነት መኖሩን ለማረጋገጥ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (t-test) እንዲተነተን ተደርጓል፡፡

### 2.3.2 የፅሑፍ መጠይቅ

በዚህ ጥናት ውስጥ የፅሑፍ መጠይቅ ዋና ዓላማ የነበረው በጥናቱ ለተሳተፉ ተማሪዎች በኢንዳክቲቭና በተለመደው አቀራረብ ሰዋሰው ማስተማሩ በተማሪዎች ሰዋሰው የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ልዩነት መመርመር ነው፡፡ የፅሁፍ መጠይቁ ባለአራት ስኬል ስምምነት መገለጫዎች እንዲኖረው ተደርጎ ተዘጋጅቷል፡፡ የፅሑፍ መጠይቁ ጥያቄ መልስ መወሰኛ ነጥብ አራት ብቻ እንዲሆኑ የተደረገበት ምክንያት ያለው (2004) እንደገለፁት ተጠኚዎቹ "እርግጠኛ አይደለሁም" የሚለውን ጨምሮ አምስት አማራጮች ቢቀርቡላቸው ኃላፊነት እና ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ መሃለኛውን (ሶስተኛውን) የመምረጥ አዝማሚያ እንደሚያሳዩ ይገመታል፡፡ ስለዚህ ይህ አማራጭ እንዲወገድ ተደርጓል፡፡ ጥያቄዎቹም በድርድር የጥያቄ አቀራረብ (matirix question) መሰረት ቀርቧል፡፡ መጠይቅ

በማዘጋጅበት ጊዜ መላሾቹ ወደ ተዛባ አቅጣጫ እንዳያመሩ ጥንቃቄ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ ስለዚህ የተስተካከሉና ደረጃቸውን የጠበቁ ጥያቄዎችን የያዘ መጠይቅ ምክንያታዊ ምላሽ ያስገኛል፡፡ መጠይቆቹም ግልፅ የማያሻማ እያንዳንዱም ጥያቄ ራሱንችሎ የሚቆም መሆን እንዳለበት Gray (2004፣ 189) እና Arksey and knight (1999)ን በመጥቀስ ያስረዳሉ፡፡ ስኬል ያላቸው ጥያቄዎች ተለዋዋጮችን ለመለካት የሚያስችሉ ናቸው፡፡ የተለመደው የስኬል አቀራረብ ጥያቄ ደግሞ "Likert scale" የተባለው ነው፡፡ ይህ እስኬል ባለ አራት ወይም ባለ አምስት ስኬል ሊሆን ይችላል፡፡ Gray (2004:197)::

የፅሑፍ መጠይቁ ቲጃኒ (2007) Beger እና Eterigten (2002) ጠቅሶ በጥናቱ የተጠቀመበትን ለጥናቱ እንዲስማማ ተደርጎበት 14 ጥያቄዎን እንዲይዝ ተደርጎ በአጥኚው ተዘጋጅቷል፡፡

የፅሁፍ መጠይቁ በጥናቱ ለሚሳተፉ ተማሪዎች ከመቅረቡ በፊት በቋንቋ መምህራን ተገምግሞ በተግባር ላይ እንዲውል ከማደረጉ በፊት በፓይለት ጥናት ተፈትሾ በክሮንባክ አልፋ ቀመር መሰረት አስተማማኝነቱ /0.748/ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ በመጠይቁም አምላል ሂደት በመጠይቁ ላይ በቀረበው ትዕዛዝ መሰረት በትክክል ያልተሞላ ካለማጣራት ተደርጎበት ትንታኔ እንዲካሄድበት ተደርጓል፡፡ የፅሁፍ መጠይቁ በተማሪዎች እንደሞላ የተደረገው በቅድመ ትምህርት እና ትምህርቱን ከተከታተሉ በኋላ ነው፤፤ በቅድመ ትምህርቱ መጠይቁን እንዲሞሉ የተደረጉበት ምክንያት ተማሪዎች በዘዴው ላይ ከመነሻው የነበራቸውን ፍላጎት ለማወቅ ታስቦ ነው፡፡ በድህረ ትምህርት መጠይቁን እንዲሞሉ የተደረገበት ምክንያት ተማሪዎቹ በተጠቀሰው አቀራረብ ሰዋሰውን ማስተማር የተማሪዎን ሰዋሰው የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ለመፈተሽ ነው፡፡ በመጠይቁ አሞላል ሂደት በመጠይቁ ላይ በቀረበው ትዕዛዝ መሰረት በትክክል ያልተሞላ ካለ ማጣራት ተደርጎበት በቅደመ ትምህርትና ድህረ ትምህርትፍላጎት መካከልየጎላ ልዩነት መኖሩን ለማረጋገጥም መጠይቁ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡

## 2.4 የጥናቱ ሂደት

ጥናቱን ለማካሄድ ለጥናት በተመረጠው ሊሙ ገነት አንደኛ ትምህርት ቤት ውስጥ ከተማሪዎች አትምህርት ቤቱ አስተዳደርና ለጥናቱ አስተዋፅኦ ለሚያደርጉ አካላት የምርምሩን አላማ በማስረዳት ይሁንታቸውን በማግኘት ወደሥራ መግባት ተችሏል፡፡ በዚሁ መሰረት የጥናቱ ተሳታፊዎች በአጥኚው የክፊል ደረጃውን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀውን የትምህርት ይዘት ከመማራቸው በፊት ቅድመ ትምህርት ፈተና ተፈትነዋል እንዲሁም ተማሪዎች የቅድመ ሙከራ ፈተና ተፈትነው ወደ ትምህርት እንዲገቡ በመጀመሪያው ክፍል

ጊዜ የፅሁፉ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ኢንዳክቲቭ አቀራረብን ከግምት በማስገባት ለክፍል ደረጃው ከቀረበው መማሪያ መፅሐፍ ላይ በመመስረት የቀረበውን የትምህርት ይዘት የሚያጎለብቱ ሃሳቦችንና የማስተማሪያ ሂደቶችን የመስኩ ባለሙያዎች ካቀረቧቸው መፃህፍት የተገኘውን ሃሳብ ከግምት በማስገባት በአጥኚው በተዘጋጀ የማስተማሪያ ቴክስት ለስድት ሳምንት እንዲማሩ ተደርጓል፡፡

ጥናቱን ከግብ ለማድረስም የጥናቱ ተሳታፊዎች ይማሩበት የነበረውን መደበኛውን ቴክስት ለማጠናቀቅ በሳምንት ሦስት ክፍለ ጊዜ በመስጠት በቀን ለ100 ደቂቃ (ለ1፡40) ለስድስት ሳምንት ያህል እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ በስተመጨረሻም ስድስቱ ሳምንታት ከተጠናቀቁ በኋላ የተዘጋጁት ጥያቄዎች ተገምግመው ለተጠኚዎቹ ፈተናው ከተሰጠ በኃላ በተመረጡ መምህራን እንዲታረም ተደርጓል፡፡

## 2.5 የማስተማሪያ ቴክስት አዘገጃጀት

አንድ የተማሪዎች የቋንቋ የማስተማሪያ ቴክስት ሲዘጋጅ የተማሪዎችን የክፍል ደረጃና የተማሪዎቹን የዕውቀት ደረጃ፣ ዕድሜ፣ ቋንቋዊ ዳራ ቀድሞ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች በአጥኚው በተቻለ መጠን ለመታየት ተሞክረዋል፡፡ ተማሪዎች የቅድመ ተምህርት ፈተናውን ከተፈተኑ በኋላ ለተሳታፊ ቡድኑ ኢንዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት ዘዴን ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋሰው ዕውቀት በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ቴክስት በአጥኚው ተዘጋጅቷል፡፡

ማረው (2003፡39) እንደሚያስረዱት ኢንዳክቲቭ የሰዋሰው ትምህርት ዘዴ በታወቀ ነገር አማካይነት ወይም ከታወቀ ነገር በመነሳት ያልታወቁ ሰዋሰዋዊ ህግጋትን ማስተማር ነው፡፡ ማረው (2003፡43) Hopkinson (2002) ዋቢ በማድረግ እንደሚገልፁት በኢንዳክቲቭ አቀራረብ የሚማሩ ተማሪዎች በመጀመሪያ እንዲገቡ የሚደረጉት መረጃ ውስጥ ነው፡፡ ከዚያም ተናጠላዊ መረጃዎችን በውል በማስተዋል እንደየተዛምዷቸው አይነት ያደራጇቸዋል፡፡ ዘዴው በነገሮች መካከል ያለን አንድነትና ልዩነት ለመረዳት ተግባራዊ የሆነ ዕውቀትን ለመገንባትና ስለነገሮች በስፋትና በጥልቀት ለማሰብ እንዲችሉ ጠንካራ መሰረት ይጥልላቸዋል፡፡ አጥኚው ለክፍል ደረጃው ከቀረበው መማሪያ መፅሐፍ ላጥ ተመስርቶ የቃል ክፍሎችን እንዲሁም ዐርፍተ ነገርን ለትምህርት ይዘትነት በመምረጥ በኢንዳክቲቭ አቀራረብ አቅርቧል፡፡

የተዘጋጁት ቴክስቶች ስድስት ክፍል ትምህርቶች ሲኖራቸው ሁሉም የሰዋሰው ችሎታን /ዕውቀትን/ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የተዘጋጁ መልመጃዎችንና ተግባራትን ይዘዋል፡፡ ቴክስቶቹ በሁለት የቋንቋ መምህራን ተገምግመው በተሰጡት አስተያየት መሰረት እንደገና ተሸሽለው ተዘጋጅተዋል፡፡ በመጨረሻም በተማሪዎች ቁጥር ልክ ተባዝተው ለእያንዳንዱ ተማሪ በግል ተሰጥተዋል፡፡ ጥናቱን ከግብ ለማድረስም የጥናቱ ተሳታፊዎች ይማሩበት የነበረውን መደበኛውን ቴክስት ለማጠናቀቅ በሳምንት ሦስት ጊዜ ለስድስት ሳምንት በቀን ለ100 ደቂቃ (1፡40) ያህል ተምረዋል፡፡

የመማሪያ ቴክስት ዝግጅቱን በተመለከተ አንድ ቃል በስም፣ በቅርፅ፣ በግስ፣ በተውሳከ ግስና በመስተዋድድ የቃል ክፍል ለመመደብ ማሟላት ያለበትን መስፈርትና እንዲሁም ዓረፍተነገር ማለት ምን ማለት እንደሆነ የዐረፍተ ነገር ተዋቃሪ አካላት ምንና ምን እንዲሆኑ ቀርቧል፡፡ የሚቀርቡትን ይዘቶች በተመለከተ መልመጃዎችን በማዘጋጀት ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ ከዚያም ተማሪዎች ከሚቀርብላቸው ምሳሌዎች በመነሳት የተለያዩ ምሳሌዎችን ለቃል ክፍሎችና ዐረፍተ ነገር በመስጠት የቃል ክፍሎችንና ዓረፍተነገርን በራሳቸው እንዲለዩና መምህሩም የመማሪያ ክፍሉን እንዲቆጣጠርና ሁኔታዎን እንዲያመቻች ተደርጓል፡፡

የማስተማሪያ ቴክስቱ የሚከተሉትን ሃሳቦች ከግምት ያስገባ ነው፡፡

1- ለቃል ክፍሎች ምሳሌዎን በመስጠት ከምሳሌዎቹ በመነሳት ተማሪዎቹ የራሳቸውን ምሳሌዎች በመስጠት የቃል ክፍሎችን እንዲለዩ ተደርጓል፡፡ ዓረፍተነገርን በተመለከተ ስለዐረፍተ ነገር ምሳሌዎችን በማቅረብ ተማሪዎች ከምሳሌው በመነሳት ሌሎች ምሳሌዎችን እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ ተዘበራርቀው የተሰጡትን ቃላት አስተካክለው ዐረፍተነገር እንዲመሰርቱም ተደርጓል፡፡
2- ትምህርቱ ሲቀርብ ለተማሪዎች ልምምድ የተመደበው ሰዓት ለመምህሩ ንግግር ከተመደበው ሰዓት እንዲበልጥ ተደርጓል፡፡ ይህ የሚሆንበትም ምክንያት ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ሰዋሰዋዊ ህግጋት ለራሳቸው ፈልገው እንዲያገኙ ለማስቻል ነው፡፡
3- ተማሪዎቹ የሚቀርቡላቸውን ሰዋሰዋዊ ይዘቶች በቡድንና በጥንድ በመሆን እንዲለማመዱ ተደርጓል፡፡
4- መምህሩና ተማሪዎች የሚቀርበው ትምህርት ሂደት በተፈለገው መጠን እንዲቀርብ ለማስቻል ሁኔታዎችን የማመቻቸት ተግባር ፈፅመዋል፡፡

5- መምህሩ ተማሪዎች በመግባባት ሂደት የሚፈፅሙትን ስህተት እንዲታገሱ ተደርጓል፡፡

6- መምህሩ በሚያመቻቹት ሁኔታ ተማሪዎች የሚና ጫወታ ተጫውተዋል፡፡

## 2.6 የመረጃ አተናተን ዘዴ

በዚህ ጥናት ውስጥ የተነሱ ጥያቄዎችን ለመመለስና የጥናቱ ዓላማ ከግብ ለማድረስ ተፈላጊው መረጃ ከተሳታፊዎች (በኢንዳክቲቭና በተለመደው አቀራረብ) ከሚማሩ ተማሪዎች በፈተና እና በፅሁፍ መጠይቅ ከተሰበሰበ በኋላ በሥርዓት ተደራጅቶ አማካይ ውጤትን፣ መደበኛ ልይይትንና የተለያዩ ቲ-ቴስቶችን መሰረት በማድረግ ትርጎም ሊሰጥ በሚችል ሁኔታ ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ በኢንዳክቲቭ እና በተለመደው የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ሰዋሰው መማር በተማሪዎች የሰዋሰው ዕውቀት ላይ የሚታየውን አንድምታ በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት ፈተና ከጥናቱ ተሳታፊዎች የተሰበሰበው መረጃ በሥርዓት ከተደራጀ በኋላ የየቡድኖቹ አማካይና መደበኛ ልይይት ውጤት ልዩነት ይኑረው እንደሆነ ለማረጋገጥ ውጤቱ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent sample t-test) አማካይነት ተሳልቶ ተቀምጧል፡፡ ትንታኔም ተሰጥቶበታል፡፡ በዚህም መሰረት በቅድመና በድህረ ፈተና የተገኙትን የተማሪዎች ውጤት የነፃነት ደረጃውንና የጉልህነት ደረጃውን እንዲሁም የቲ-ዋጋን ጨምሮ የተገኘውን ውጤት በማወዳደር የተደረሰበት ማጠቃለያ ቀርቧል፡፡ ለዚህም ለምናልባት ስህተት /Simple-error/ ከፍ እና ዝቅ ተብሎ p= 0.05 ተወስዷል፡፡

ከፈተና በተጨማሪም ለመረጃ መሰብሰቢያነት የዋለው የፅሑፍ መጠይቅ ሲሆን የፅሁፍ መጠይቁ በኢንዳክቲቭና በተለመደው አቀራረብ በቅድመ ትምህርት ድህረ ትምህርት በጥናቱ ተሳታፊዎች ከተሞላ በኋላ በሥርዓት ተደራጅቷል፡፡ በቅድመ ትምህርትና ድህረትምህርት የፅሁፍ መጠይቅ ከጥናቱ ተሳታፊዎች የተሰበሰበው መረጃ በሥርዓት ከተደራጀ በኋላ የየቡድኖቹ አማካይና መደበኛ ልይይት ውጤት ልዩነት ይኖረው እንደሆነ ለማረጋገጥ ውጤቱ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (Independet-t-test) አማካይነት ተሰልቶ በምዕራፍ አራት ውስጥ ትንታኔ ተሰጥጦበታል፡፡ በዚህም መሰረት በፅሑፍ መጠይቁ የተገኙት የተማሪዎች ምላሽ የነፃነት ደረጃውንና የጉልህነት ደረጃውን ጨምሮ በገላጭና ድምዳሚያዊ ስታትቲክስ ተተንትኗል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 3የጥናቱ ውጤት ትንተና ማብራሪያ

### 3.1 የጥናቱ ውጤት ትንተና

ይህ ጥናት ሲደረግ ዋና ዓላማ ተደርጎ የተወሰደው በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሰዋሰው ትምህርትን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋሰው ዕውቀት በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና መፈተሽ/መመርመር/ ነው፡፡ ይህንን ጥናት ውጤታማ ለማድረግ፣ በፈተናና፣ በቃለመጠይቅ የተሰባሰቡትን መረጃዎች በኢንዳክቲቭ እና በመደበኛው የትምህርት አቀራረብ ሰዋሰውን ማስተማር በተማሪዎች ሰውሰውን የመረዳት ችሎታ ላይ ልዩነት መኖር አለመኖሩን እና በ ኢንዳክቲቭ እና በዘልማዳዊው አቀራረብ ሰዋሰውን ማስተማር በተማሪዎች የሰዋሰው ዕውቀት ላይ ምን ያህል ልዩነት ሊኖረው ይችላል? የሚሉት መሰረታዊ የምርምሩ ጥያቄዎችን ቅደም ተከተሉን በመጠበቅ ተተንትነዋል፡፡

በክፍል ውስጥ በቅድመ ሙከራ እና ድህረ ሙከራ ፈተናዎች አጠቃላይ መረጃዎችን በመሰብሰብ እንደ አገባባቸው ተደራጅተው ቅደም ተከተላቸውን በጠበቀ መልኩ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ይኸውም የሙከራ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን ተጠኚዎች ከልምምዱ በፊት ያላቸውን የሰዋሰው ችሎታ መረጃ መለየት አስፈላጊ በመሆኑ በተሰጣቸው የሰዋሰው ችሎታ ፈተና የሙከራ ቡድኑና የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ሰዋስው ፈተና ከ50 ያስመዘገቡት ችሎታ ውጤት ንፅፅር በ ሰንጠረዥ 4.1 ላይ ተገልፃል፡፡ የሙከራ ቡድኑና የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ የሰዋሰው ችሎታ ያስመዘገቡት ችሎታ ውጤት ንፅፅር ደግሞ በሰንጠረዥ 4.2 ላይ በሂሳባዊ ቀመር ተሰልቶ ተቀምጧል፡፡ በዚሁ መሰረት የቁጥጥር ቡድን ቅድመ እና ድህረ ችሎታ ፈተና እንዲሁም የሙከራ ቡድኑ ቅድመና ድህረ ችሎታ ፈተና ውጤት ንፅፅር በሰንጠረዥ 4.3 ላይ ተሰልቶ ተቀምጧል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ሊመለስ የተፈለገው የመጀመሪያው ጥያቄ በክፍል ውስጥ የሰዋሰው ትምህርትን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር በተማሪዎች የሰዋሰው ትምህርት ላይ ዕውቀት ላይ የሚኖረው አንድምታ ምንድነው? የሚለው ሲሆን ይህንን ጥያቄ ለመመለስ በኢንዳክቲቭ እና በመደበኛው አቀራረብ ቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት ፈተና የተሰበሰበውን መረጃ አማካይ ውጤት፡ መደበኛ ልይይትና ስታትቲክስ ተተንትኗል፡፡ ውጤቱም በሰንጠረዥ 4.1 እና 4.2 ተመልክቷል፡፡

ሰንጠረዥ 4.1 የሙከራ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርት ፈተና የሰዋሰው ችሎታ ንፅፅር (በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት)

| ቡድን | ናሙና | ማካይ ውጤ | መደበኛ ልይይት | የቲ-ዋጋ | ነፃነት ደረ | የጉልህነት ደረጃ (ባለ ሁለት ጫፍ) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሙከራ | 40 | 23 | 8.84 | 0.052 | 78 | 0.123 |
| የቁጥጥር | 40 | 22.9 | 8.49 | | | |

p>0.05

ከሠንጠረዥ 4.1 መረዳት እንደሚቻለው የሙከራ ቡድን የሰዋሰው ውጤት አማካይ ውጤት 23 ሲሆን የቁጥጥር ቡድን የሰዋሰው ውጤት 22.9 ነው፡፡ የሁለቱም ቡድኖች የሰዋሰው ውጤት አማካይ ውጤት ተመሳሳይነት ያላቸው ይመስላሉ እንዲሁም የሙከራ ቡድን የመደበኛ ልይይት 8.84 ሲሆን የቁጥጥሩ ቡድኑ የመደበኛ ልይይት ደግሞ 8.49 ነው፡፡ ይህም የሁለቱ ቡድኖች የመደበኛ ልይይት ውጤት ተቀራራቢነት እንዳላቸው ያሳያል፡፡ በመሆኑም ሁለቱ ቡድኖች ውስጥ የተመዘገቡት የፈተና ውጤቶች ከአማካያቸው ተቀራራቢ መሆኑ እንዲሁም በክሪንባች የውጤት መመዘኛ መሰረት ከ0.7 በላይ በመሆኑ እውነትነት እና ተገቢነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል፤፤በተጨማሪም በቅድመ ፈተና ውጤት ምዘና የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኖች መካከል የጎላ ልዩነት አለመኖሩን ጥናቱ ያሳያል፤፤

ነገር ግን የአማካይ ውጤትን ብቻ በማየት በመካከላቸው ያለው ልዩነት አስተማማኝ መሆኑን ማረጋገጥ አዳጋች ይሆናል፡፡ ስለዚህ ውጤቱ በስታትቲክስ መረጋገጥ አለበት፡፡ ይህም በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተፈትሾ የ"ቲ" ስሌት ዋጋ 0.0052 ሲገኝ የpስሌት ዋጋ/tab/ 0.123 ሲሆን በ0.05 የጉልህነት ደረጃ /signification level/ በ 78 የነፃነት ደረጃ /degree of freedom/ ባለሁለት ጫፍ ፍተሻ የ"ቲ" ሰንጠረዥ ዋጋ ወይም /t-cri/ 2.000 ሆኗል፡፡ በዚህም መሰረት የ "ቲ" ዋጋ /0.052) ከሠንጠረዥ ዋጋ /t-cri/ 2.000 አንሶ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በፈተና አማካይነት የተሰበሰበው መረጃ የድህረ ሰዋሰው የፈተና ውጤት ነው፡፡ የቁጥጥር ቡድን በመደበኛው መንገድ የሙከራ ቡድኑ ደግሞ አጥኚው ባዘጋጀው የቃል ክፍሎችንና ዓረፍተ ነገርን ከቴክስት ከተማሩ በኋላ ሁለቱም ቡድኖች አንድዓይነት የሰዋሰው ችሎታ ፈተና ተፈትነው ያስመዘገቡት ውጤት የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ የድህረ

የሰዋሰው ፈተና ውጤት በሰንጠረዥ 4.2 ላይ በንፅፅር ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 4.2 በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድን ድህረ ትምህርት ፈተና የሰዋሰው ችሎታ ንፅፅር (በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት)

| ድን | ሙና | ማካይ ጤት | ደበኛ ይይት | ቲ-ዋጋ | ነፃነት ደረ | ጉልህነት ደረጃ(ባለ ሁለ ጌፍ) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሙከራ | 40 | 31.4 | 6.95 | 4.79 | 78 | 0.001 |
| ቁጥጥር | 40 | 24 | 6.88 | | | |

P<0.05

ሠንጠረዥ 4.1 እንደሚያሳየው በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድኑ ሰዋሰው መማር በሰዋሰው ውጤት ላይ የታየው ለውጥ በሙከራ ቡድን የተማሩ ተማሪዎች አማካይ ውጤት 31.4 ከቁጥጥር ቡድን አማካይ ውጤት 24 በ7.4 ብልጫ አሳይቷል፡፡ በመደበኛ ልይይት የቁጥጥር ቡድን መደበኛ ልይይት 6.88 ከሙከራ ቡድን መደበኛ ልልይት 6.95 ያነሰ ይመስላል፡፡ይህም ልዩነት በመደበኛ ልይይት 0.07 ነው፤፤

ይሁን እንጂ አማካይ ውጤትን እንዲሁ በማየት ብቻ ልዩነት እንዳለውና እንደሌለው ማረጋገጥ ስለማይቻል በቲ-ቴስት ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም የባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በስታት ስቲክስ ስሌቱም የpስሌት ዋጋ /tab/ 0.000 ሲሆን 0.05 የጉልህነት ደረጃ በ78 የነፃነት ደረጃ /ቲ=4.79 df=78, p=<0.05 መሆኑን ውጤት አሳይቷል፡፡ ይህ የሚያመለክተው የሙከራ ቡድኑ በኢንዳክቲቭ አቀራረብ መማራቸው ከተለመደው አቀራረብ በላይ የተማሪዎቹን የሰዋሰው ችሎታ ማሻሻሉን ያመለክታል፡፡ ይህንን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ የሁለቱን ቡድኖች ቅድመ ፈተናና ድህረ ፈተና በማነፃፀር በሰንጠረዥ 4.3 ላይ የተቀመጠውን ማየት ይቻላል፡፡

ሠንጠረዥ-4.3 የቡድኖቹ የቅድመና የድህረ ሰዋሰው ትምህርት የሰዋሰው ችሎታ ተናጠላዊ ንፅፅር (በዳግም ልኬት ናሙና "ቲ"-ቴስት")

| ተጠኚ ቡድን | የፈተና ዓይነት | የሰዋሰው ፈተና ውጤት | | | ተቀንሶ የተገኘ አማካይ ውጤት ልዩነት | ተቀንሶ የተገኘ መደበኛ ልይይት ልዩነት | የፃነት ደረጃ (df) | የተሰላ የ"ቲ" ዋጋ | የጉልህነት ደረጃ (ባለሁለት ጫፍ) | ጉልህ ልዩ ነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛ ት | አማካይ ውጤት | በደበኛ ልይይት | | | | | | |
| የቁጥ ጥር ቡድን | ቅድመ ትምህርት | 40 | 22.9 | 8.49 | 1.1 | 1.61 | 39 | 1.73 | 0.092 | የለም |
| | ድህረ ትምህርት | | 24 | 6.88 | | | | | | |
| የሙከ ራ ቡድን | ቅድመ ትምህርት | 40 | 23 | 8.84 | 8.4 | 14.51 | 39 | 14.52 | 0.001 | አለ |
| | ድህረ ትምህርት | | 31.4 | 6.95 | | | | | | |

- ✓ የቁጥጥር ቡድን ፡- /p>0.05/ ሲሆን
- ✓ የሙከራ ቡድን ፡- /p<0.05/

ሠንጠረዥ 4.3 እንዲሚያሳየው የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ትምህርት የሰዋሰው ፈተና አማካይነት ውጤት 24 ከከቅድመ የሰዋሰው ትምህርት ፈተና አማካይነት ውጤት 22.9 ጋር ሲነፃፀር በልጦ የታየው በ1.1 ብቻ ነው፡፡ ይህም ልዩነት ጉልህነት እንዳለው እና እንደሌለው በዳግም ልኬት ናሙና "ቲ-ቴስት" (repeadted measure sample t-test) ተፈትሻል፡፡ በፍተሻውም የ"ቲ" ስኬት ዋጋ /tab/ 1.72 ሲሆን በ0.05 የጉልህነት ደረጃ በ39 የነፃነት ደረጃ ባለሁለት ጫፍ ፍተሻ የ"ቲ" ሠንጠረዥ ዋጋ /tort/ 2.021 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት የ"ቲ" ስሌት ዋጋ 1.72 ከሰንጠረዥ የ"ቲ" ዋጋ 2.021 ሲነፃፀር አንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም ቡድኑ በድህረ ትምህርትና ከቅድመ ትምህርት የሰዋሰው ውጤት ጉልህ ልዩነት አለማሳየቱን ሊያመለክት ይችላል፡፡ ይህም የቁጥጥር ቡድኑ ተጠኚዎች በተለመደው አቀራረብ መማራቸው የሰዋሰው ችሎታቸውን በማሻሻል ረገድ የጎላ አስዋፅኦ እንደሌለው የሚያሳይ ፍንጭ አለው፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ ሲታይ የሙከራ ቡድኑ የድህረ ትምህርት የሰዋሰው ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት 31.4 ከቅድመ ትምህርት የሰዋሰው ችሎታ አማካይ ውጤት 23 ጋር ሲነፃፀር በ8.4 ልቆ ይታያል፡፡ ልዩነቱም ጎላ ያለ እንደሆነና ብልጫ ያለው መሆኑንም ያሳያል፡፡ ስለዚህም የሙከራ ቡድኑ ከትምህርት በፊትና ከትምህርት በኋላ የሰዋሰው ፈተና ውጤት ልዩነት አሳይቷል፡፡ ሙከራ ቡድኑ በኢንዳክቲቭ አቀራረብ አማካይነነት የሰዋሰው ትምህርት

በመማሩ በሰዋሰው ችሎታ ላይ ደግሞ ከነበረው የተሻለ ችሎታ ማምጣት ችሏል ማለት ይቻላል፡፡ በሁለቱም አማካዮች መካከል ልዩነት የመጣው የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ በላይ የተማሪዎችን የሰዋሰው ችሎታ ያሻሽላል ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ ነው ማለት ይቻላል፡፡ አይታይም በሚል የቀረበው የጥናቱ አልቦ መላምት /Ho/ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይህ ማለት በኢንዳክቲቭ እና በተለመደው አቀራረብ ሰዋሰውን ማስተማር በተማሪዎች የሰዋሰው ችሎታ ላይ ልዩነት አይኖርም/የለም የሚለው መላምት ውድቅ ይሆንና ተለዋጩ መላምት/ በኢንዳክቲቭ እና በተለመደው አቀራረብ ሰዋሰውን ማስተማር በተማሪዎች የሰዋሰው ችሎታ ላይ ልዩነት አለ? የሚለው መላምት በተጨባጭ ሙከራ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ ለመመለስ የተፈለገው ሁለተኛ መሰረታዊ ጥያቄ በኢንዳክቲቭ እና በተለመደው አቀራረብ በተማሪዎች ሰዋሰው የመማር ፍልጎት በማጎልበት ረገድ ልዩነት ይኖረው ይሆን? የሚል ነው፡፡ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ተግባራዊ የተደረገው የፅሁፍ መጠይቅ ሲሆን የፅሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ የተደረገው በቅድመ ትምህርትና በድህረ ሰዋሰው ትምህርት ነው፡፡ ለዚህም በፅሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ትንተና የሙከራ ቡድንንና የቁጥጥር ቡድን ተጠኚዎች ከልልምዱ በፊት ያላቸውን ሰዋሰው የመማር ፍላጎት መረጃ መለየት አስፈላጊ በመሆኑ በተሞላው የፅሁፍ መጠይቅ የሙከራ ቡድኑና የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ሰዋሰው የመማር ፍላጎት ንፅፅር እንደሚከተለው በሰንጠረዥ 4.4ይመልከቱ፤፤የሙከራ ቡድኑና የቁጥጥር ቡድኑድህረ ሰዋስው የመማር ፍላጎት ንጽጽር እንደሚከተለው በሰንጠረዠ 4.5 ተሰልቶ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሰረት የቁጥጥር ቡድን ቅድመና ድህረ ሰዋሰው የመማር ፍላጎት እንዲሁም የሙከራ ቡድኑ ቅድመና ድህረ ሰዋሰው የመማር ፍላጎት ንፅፅር በሰንጠረዥ 4.6 ተሰልቶ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 4.4 የሙከራ ቡድን እና የቁጥጥር ቡድን ቅድመመ ሰዋሰው የመማር ፍላጎት (በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት)

| ቡድን | ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ-ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ (ባለ ሁለት ጫፍ) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ | 40 | 28.4 | 2.41 | 1.56 | 78 | 0.123 |
| የቁጥጥር | 40 | 27.6 | 2.18 | | | |

$p>0.05$

በሰንጠረዥ 4.4 የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ የመማር ፍላጎት የፅሁፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ ውጤት 27.6 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ቅድመ የመማር ፍላጎት ምላሽ የተገኘው አማካይ ውጤት ደግሞ 28.4 ነው፡፡ ይህም የቁጥጥር ቡድኑም ሆነ የሙከራ ቡድኑ ከትምህርት በፊት ተመሳሳይ ሰዋሰው የመማር ፍላጎት እንደነበራቸው ያሳያል፡፡ በሰንጠረዥ 4.4 የተመዘገቡት የመደበኛ ልይይት ውጤቶች ከአማካይ ውጤት ያላቸው ርቀት የተቀራረበ እንደሆነ ያሳያል፡፡ የተገኘው "ቲ- ዋጋ 1.56 ከቲ ሰንጠረዥ ዋጋ 2.000 ያነሰ በመሆኑ ተጠኚ ተማሪዎች ያላቸው ቅድመ ትምህርት ሰዋሰው የመማር ፍላጎታቸው ተቀራራቢ እንደሆነ ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በፅሁፍ መጠይቅ አማካይነት የተሰበሰበው መረጃ የድህረ የፅሁፍ መጠይቅ ነው፡፡ የቁጥጥር ቡድኑ በመደበኛው መንገድ የሙከራ ቡድኑን ደግሞ አጥኚው ባዘጋጀው የቃል ክፍሎችንና አረፍተነገር ከቴክስት ከተማሩ በኋላ ሁለቱም ቡድኖች የሞሉት ሰዋሰው የመማር ፍላጎት ንፅፅር በሰንጠረዥ 4.5 በንፅፅር ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 4.5 የሙከራ ቡድን እና የቁጥጥር ቡድን የተማሪዎች ድህረ ሰዋሰው የመማር ፍላጎት ንፅፅር (በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት)

| ቡድን | ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ-ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ (ባለ ሁለት ጫፍ) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ | 40 | 35 | 3.74 | 10.10 | 78 | 0.001 |
| የቁጥጥር | 40 | 28.3 | 1.91 | | | |

P<0.05

ሠንጠረዥ 4.5 እንደሚያሳየው የሙከራ ቡድኑ የመማር ፍላጎት አማካይ ውጤት 35 ከቁጥጥር ቡድን የመማር ፍላጎት አማካይ ውጤት 28.3 በ6.7 ብልጫ አሳይቷል፡፡ በመደበኛ ልይይት የቁጥጥር ቡድን መደበኛ ልይይት (1.91) ከሙከራ ቡድን መደበኛ ልይይት 3.74 ያነሰ መሆኑን ከሰንጠረዥ 4.5 መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሰንጠረዥ 4.5 እንደተመለከተው በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድን የመማር ፍላጎት አማካይ ውጤት መካከል ያለውን ልዩነት በስታትስቲክስ ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በሰንጠረዥ 4.5 እንደተመለከተው በ78 የነፃነት ደረጃ የp-ዋጋ 0.000 (ቲ = 10.10 p<0.05 ሲሆን የቲ ዋጋ 10.10 ከ t-cri 2.000 ጉልህ ሆኖ መገኘቱን ውጤቱ አሳይቷል፡፡ በሁለቱ አማካዮች መካከል ልዩነት የመጣው የሙከራ ቡድኑ በኢንዳክቲቭ አቀራረብ መማራቸው ከተለመደው አቀራረብ በላይ የተማሪዎችን ሰዋሰው የመማር ፍላጎት ማጎልበት ይቻላል የሚል ተጨማሪ መረጃ ይሰጣል፡፡ ይህንንም ይበልጥ

ግልፅ ለማድረግ የሁለቱን ቡድኖች ቅድመ የፅሁፍ መጠይቅና ድህረ ፅሁፍ መጠይቅ ለንፅፅር በሰንጠረዥ 4.6 ላይ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 4.6 የቡድኖቹ የቅድመና የድህረ የሰዋሰው የመማር ፍላጎት የፅሁፍ መጠይቅ ተናጠላዊ ንፅፅር (በዳግም ልኬት ናሙና "ቲ-ቴስት")

| ተጠኚ ቡድን | የፅሁፍ መጠይቅ | የፅሁፍ መጠይቅ | | | ተቀንሶ የተገኘ አማካይ ውጤት ልዩነት | ተቀንሶ የተገኘ መደበኛ ልይይት ልዩነት | የነፃነት ደረጃ (df) | "ቲ" ቴስት | የጉልህነት ደረጃ (ባለሁለት ጫፍ) | ጉልህ ልዩ ነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | | | | | | |
| የቁጥጥር ቡድን | ቅድመ ፍላጎት | 40 | 27.6 | 2.18 | 0.7 | 0.27 | 39 | 1.87 | 0.092 | የለም |
| | ድህረ ፍላጎት | | 28.3 | 1.91 | | | | | | |
| የሙከራ ቡድን | ቅድመ ፍላጎት | 40 | 28.4 | 2.41 | 6.6 | 1.33 | 39 | 10.96 | 0.001 | አለ |
| | ድህረ ፍላጎት | | 35 | 3.74 | | | | | | |

- ✓ የቁጥጥር ቡድን ፡- /p>0.05/ ሲሆን
- ✓ የሙከራ ቡድን ፡- /p<0.05/

ሰንጠረዥ 4.6 እንደሚያሳየው የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ትምህርት የፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት 28.3 ከቅድመ ትምህርት የፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት 27.6 ጋር ሲነፃፀር በልጦ የታየው በ0.7 ብቻ ነው፡፡ ይህም ልዩነት እንዳለው እንደሌለው በደግሞ ልኬት ናሙና "ቲ-ቴስት" /repeated measure sample t-test/ ተፈትሿል፡፡ በፍተሻውም የ"ቲ" ቴስት ስሌት ዋጋ /tab/ 1.87 ሲሆን በ0.05 የጉልህነት ደረጃ በ39 የነፃነት ደረጃ ባለሁለት ፍተሻ "ቲ" ሠንጠረዥ ዋጋ /tort 2.021 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት የ"ቲ" ስሌት ዋጋ 1.87 ከሠንጠረዥ የ"ቲ" 2.021 ሲነፃፀር አንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም ቡድኑ በድህረ ትምህርትና በቅድመ ትምህርት ሰዋሰው የመማር ፍላጎት ጉልህ ልዩነት አለማሳየቱን ሊያመለክት ይችላል፡፡ ይህም የቁጥጥር ቡድኑ ተጠኚዎች በተለመደው አቀራረብ መማራቸው ሰዋሰው የመማር ፍላጎታቸውን በማሻሻል ረገድ የጎላ አስተዋፅኦ እንደሌለው የሚያሳይ ነው፡፡

በሌላ መልኩ ሲታይ የሙከራ ቡድኑ የድህረ ትምህርት የሰዋሰው የፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት 35 ከቅድመ ትምህርት የፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት 28.4 ጋር ሲነፃፀር በ6.6 ልቆ ይታያል፡፡ ልዩነቱ የጎላ መሆኑን ብሎም ብልጫ እንዳለው የሚያሳይ ነው፡፤ ስለዚህ የሙከራ ቡድኑ ከትምርት በፊትና ከትምህርት በኋላ ሰዋሰው የመማር ፍላጎት ልዩነት አሳይቷል፡፡ ሙከራ ቡድኑ በኢንዳክቲቭ ዘዴ አማካይነት የሰዋሰው ትምህርት በመማራቸው ምክንያት የሰዋስውን ትምህርት በክፍል ውስጥ የመማር ፍላጎታቸው

በመሻሻሉ ተማሪዎች ቀድሞ ከነበራቸው የተሻለ ግንዛቤ አግኝተዋል ማለት ይቻላል፡፡ በሁለቱም አማካዮች መካከል ልዩነት የመጣው የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ በላይ የተማሪዎችን ሰዋሰው የመማር ፍላጎት ማጎልበት ይቻላል፤ ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ ነው ለማለት ያስደፍራል፡፡ ይታይም በሚል የቀረበው የጥናቱ አልቦ መላምት /Ho/ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይህ ማለት በኢንዳክቲቭ እና በተለመደው አቀራረብ ሰዋሰውን ማስተማር በተማሪዎች ሰዋሰው የመማር ፍላጎት ላይ ልዩነት አይኖርም/ የለም የሚለው መላምት ውድቅ ይሆንና ተለዋጩ መላምት በኢንዳክቲቭ እና በተለመደው አቀራረብ ሰዋሰውን ማስተማር በተማሪዎች ሰዋሰው የመማር ፍላጎት ላይ ልዩነት አለ? የሚለው መላምት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

ይህ ጥናት ሲካሄድ በአጠቃላይ ትኩረት ያደረገው ሰዋሰውን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋሰው ዕውቀት በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም በፈተናና በፅሁፍ መጠይቅ በተሰበሰቡት መረጃዎች በኢንዳክቲቭና በተለመደው /በመደበኛው/ አቀራረብ ምክንያት ሰዋሰው ማስተማር በተማሪዎች የሰዋሰው ችሎታ ላይ ያለው ለውጥ ልዩነት ይኑረው አይኑረው እንደሆነ በኢንዳክቲቭና በተለመደው አቀራረብ ምክንያት ሰዋሰው የመማር ፍላጎት ላይ ያለውንለውጥ ልዩነት ይኑረው አይኑረው እንደሆነ ለመፈተሽ መረጃዎች በገላጭና በድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ በሰፊው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

በውጤት ትንተናው በቅድሚያ ምላሽ የተሰጠው የጥናቱ ሌላው ትኩረት በኢንዳክቲቭና በተለመደው አቀራረብ ምክንያት ሰዋሰው ማስተማር በተማሪዎች የሰዋሰው ዕውቀት ላይ ያለው ለውጥ ልዩነት መኖር አለመኖር የሚመለከት ነው በሰንጠረዥ 4.1፣ 4.2 እና 4.3 እንደቀረበው የሙከራ ብድኑ አማካይ ፈተና ውጤት በስታትስቲክስ ጉልህ ($p>0.05$) ሆኖ ባለመገኘቱ በኢንዳክቲቭና በተለመደው አቀራረብ ምክንያት ሰዋሰው ማስተማር በተማሪዎች የሰዋሰው ችሎታ ላይ ያለው ለውጥ ልዩነት መኖሩን የዚህ ጥናት ውጤት አረጋግጧል፡፡ ይህም ውጤት ከ(wang -2012)፣ (swafer and wudruf 1978) ጥናቶች ውጤት ጋር ይደጋገፋል፡፡ በተመሳሳይ ከ(shafer 1989) ድምዳሜ ሃሳብ ጋር የተስማማ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በጥናቱ ውጤት መሰረት በሰዋሰው ችሎታ ላይ መሻሻል የታየው የጥናቱ ተሳታፊዎች የቃል ክፍልን፣ ዐረፍተነገርን፣ ግሶችንና ቅፅሎችል በኢንዳክቲቭ አቀራረብ መማራቸው የሰዋሰው ፈተና ውጤታቸውን አሻሽሎላቸዋል፡፡

ከዚህ ጥናት መሰረታዊ ጥያቄዎች አንፃር በውጤት ትንተናው ሌላው ትኩረት የተደረገበት ጉዳይ በኢንዳክቲቭ በተለመደው አቀራረብ ምክንያት ሰዋሰው የመማር ፍላጎት ላይ ያለው ልዩነት መኖር አለመኖሩን የሚመለከት ነው፡፡ በሠንጠረዥ 4.4 4.5 እና 4.6 እንደሚታየው ከቁጥጥር ቡድን የተማሪዎች የመማር ፍላጎት አማካይ ውጤት በስታትስቲክስ ጉልህ ($p<0.05$) ሆኖ በመገኘቱ እና የቁጥጥር ቡድን አማካይ ውጤት በስታትስቲክ ጉልህ ($p>0.05$) ሆኖ ባለመገኘቱ በኢንዳክቲቭና በተለመደው አቀራረብ ምክንያት ሰዋሰው የመማር ፍላጎት ላይ ያለው ለውጥ ልዩነት መኖሩን ያመላከተው የዚህ ጥናት ውጤት አብርሃም (2008) እንደገለፁት "ለቋንቋ ቅርፅ የሚሰጠው ትኩረት ተግባቦታዊ ብቃትን ሊያዳብር አይችልም በመሆኑም ተማሪዎች ሰዋሰዋዊ ስህተት እንፈፅማለን የሚል ፍራቻ በሚያስወግድላቸውና ነፃ ሆነው እንዲሰሩ የሚያደርጋቸው አቀራረብ መማር አለባቸው" ከሚለው ሃሳብ ጋር ተደጋጋፊነት አለው፡፡

## 3.2የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ውጤት በኢንዳክቲቭና በተለመደው አቀራረብ ምክንያት ሰዋሰውን ማስተማር በተማሪዎች የሰዋሰው ችሎታ ላይ ያለው ለውጥ ልዩነት መኖር እንዲሁም በኢንዳክቲቭ በተለመደው አቀራረብ ምክንያት ሰዋሰውን የመማር ፍላጎት ላይ ያለው ለውጥ ልዩነት መኖር የሚል አንድምታ ይኖረዋል፡፡ ይህም የድህረ ትምህርት አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት አማካይ ውጤት በስታስቲክስ ጉልህ ሆኖ መገኘቱ አንድ አስረጂ ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪ በኢንዳክቲቭ አቀራረብ የሰዋሰው ፈተና ውጤት አማካይ ውጤትና በተለመደው አቀራረብ የሰዋሰው ፈተና ውጤት አማካይ ውጤት በስታስቲክስ ጉልህ ሆኖ መታየቱ ተጨማሪ አስረጂ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት በኢንዳክቲቭ አቀራረብ ሰዋሰው የመማር ፍላጎት አማካይ ውጤትና በተለመደው አቀራረብ ሰዋሰውን የመማር ፍላጎት አማካይ ውጤት እስታስቲክስ ጉልህ ሆኖ መታየቱ ተጨማሪ አስረጂ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ በኢንዳክቲቭ አቀራረብ ሰዋሰውን የመማር ፍላጎት ከተለመደው አቀራረብ ሰዋሰውን የመማር ፍላጎት በላይ በመጎልበቱ በኢንዳክቲቭ አቀራረብ ሰዋሰው ፈተና ውጤት ከተለመደው አቀራረብ ሰዋሰው ፈተና ውጤት በላይ እንደሚሻል አስተዋፅኦ አድርጓል ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በተጨማሪም ተጠኚ ተማሪዎቹ (የሊሙ ገነት አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ በዕድሜም በ14-15 ውስጥ ያሉ ወንድና ሴት ተማሪዎች ናቸው እነዚህ ተማሪዎች ሰዋሰውን በኢንዳክቲቭ ዘዴ በተግባራዊ መልኩ እንዲማሩ መደረጉ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡ ይህም ማለት ለምሳሌ፡- አበበ በሩን ዝጋ፣ ከበደ መስኮቱን ክፈት ፣

ጫልቱ መፅሐፉን ጠረጴዛ ላይ አስቀምጭው ወዘተ የሚሉት ተማሪዎች በተግባር እየሞከሩት መሂዳቸው የበለጠ ለትምህርቱ ትኩረት እንዲሰጡ አነሳስቷቸዋል፡፡

የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች በዕድሜም ልጆች ስለሆኑ በተግባር የሚሰሩትን ቶሎ የመያዝ ችሎታቸው ከፍተኛ በመሆኑ ሰዋሰውን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ሲማሩ ይህ ተግባር እየተተኮረ መማራቸው ትምህርቱን የበለጠ እንዲጓጉና ያለመሰልቸት እንዲከታተሉትና በቀላሉ ግንዛቤ እንዲያገኙ አድርጓቸዋል ለዚህም ነው የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች መመረጣቸው ምክንያቱ በመሆኑም ተማሪዎች በኢንዳክቲቭ ዘዴ በድህረ ፈተና የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸው የአቀራረቡ ስልት ሳቢ እና ምቹ በመሆኑ ለወደፊት በት/ቤት ሰዋሰውን ከሥር ላሉት ተማሪዎች ሳቢ በሆነ መልኩ ለማስተማር እንዲሁም ተመሳሳይ ጥናት ለሚያደርጉ አካላት ትንሽ ፍንጭ ያለ ይመስላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 4 ማጠቃለያ ፣ መደምደሚያና የመፍትሔ ሃሳብ

በዚህ "ሰዋሰውን" በበኢንዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር የተማሪዎች የሰዋሰው ዕውቀት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና "በሚል ጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥ ባፉት አራት ምዕራፎች ውስጥ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ጥያቄዎች የጥናቱ ስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰን፣ ተዛምዶ ፅሁፎች፣ ተዛጅ ጥናቶች፣ የጥናቱ አጠናን ዘዴዎች፣ የጥናቱ ትንተና ገለፃዎችና የመፍትሄ ሃሳቦች በጥናቱ ውጤት የተመሰረቱ አስተያየቶች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

### 4.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት እና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ መሰረታዊ የሆነውን የሰዋሰውን ትምህርት የሚዳስስ ነው፡፡ ጥናቱም ሰዋሰውን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋሰው ዕውቀት በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ይመረምራል፡፡ ብሎም የሰዋሰውን ትምህርት በኢንዳክቲቭ ዘዴ ሲማሩ ያላቸውን ግንዛቤ ፈትሿል፡፡ በዚሁ መሰረት በጥናቱ ምላሽ ሊሰጥባቸው የጣለሙት መሠረታዊ ጥያቄዎች በቅደም ተከተል የሚከተሉት ጥያቄዎች ነበሩ፡፡

1- በክፍል ውስጥ የሰዋሰው ትምህርት በኢንዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር በተማሪዎቹ የሰዋስው ዕውቀት ላይ ምን አንድምታ ይኖረው ይሆን?

2- የሰዋሰው ትምህርት በኢንዳክቲቭ ዘዴ በክፍል ውስጥ ሲማሩ ምን ያህል ተሳትፎ ይኖራቸው ይሆን?

3- በኢንዳክቲቭና በተለመደው አቀራረብ ሰዋሰውን ማስተማር በተማሪዎች ሰዋሰው የመማር ፍላጎት ላይ ልዩነት ይኑረው ይሆን? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመተንተን ተሞክሯል።

የጥናቱ ተሳታፊዎች በጅማ ዞን በሊሙ ኮሣ ወረዳ በሊሙ ገነት 1ኛደረጃ ት/ቤት በ2015 ዓ.ም በ8ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ያሉ ተማሪዎች ናቸው። ትምህርት ቤቱ 210 ተማሪዎች በአራት የመማሪያ ተመድበው ከሚማሩ ክፍሎች ሁለቱን "8A" እና

"8B" የአማርኛ ተመሪዎችን በቀላል ዕድል ሰጪ ናሙና ዘዴ ተሳታፊ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ዋነኛው የመረጃ መሰብሰቢያ ፈተና ሲሆን የክፍል ደረጃውን መርጦ ትምህርትና መማሪያ መፅሐፉን መሰረት በማድረግ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

የጥናቱ ተሳታፊዎች ከቃል በመነሳት እስከ ዐረፍተነገር እና አንቀፅ ድረስ በቴክስት በማዘጋጀት በኢንዳክቲቭ እና በተለመደው አቀራረብ ከመማራቸው በፊት የቅድመ ትምህርት ሰዋሰው ፈተና በጥናቱ አማካይና አጥኚው በሚሰራበት ትምህርት ቤት በሚያስተምሩት መምህራን ታይቶ ማስተካከያ ታክሎበት በሙከራ ጥናት ተፈትሾ አስተማማኝ ሆኖ በመገኘቱ የተማሪዎቹን ሰዋሰው ችሎታ ለመለካት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በመቀጠልም ለማስተማሪያነት የተዘጋጁትን ቴክስቶች ለስድስት ሳምንት ሲማሩ ቆይተዋል በመጨረሻም ከቅድመ ትምህርት ፈተና ጋር አቻ የሆነየድህረ ትምህርት ፈተና እንደቅድመ ትምህርት ፈተና ታይቶና ተፈትሾ ተግባራዊ በማድረግ ለጥናቱ የሚፈለገው መረጃ እንዲሰባሰብ ተደርጓል፡፡

ይህም ጥናት በሚካሄድበት ጊዜ በክፍሉ ውስጥ የሚደረገው ትምህርት በናሙና መጠን በፎቶ እና በቪዲዮ የተደገፈ መረጃ እንዲኖረው አስፈላጊው ጥረት ተደርጓል፡፡

ተማሪዎች በሁለቱ አቀራረብ ሰዋሰው ለመማር ያላቸው ፍላጎትና እና አመለካከት ልዩነት መኖርና አለመኖር ለማወቅ የፅሁፍ መጠይቅ ሌላው መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡ መጠይቁ 14 ጥያቄዎች የተካተቱበት ሲሆን ቲጃኒ (2007) የሰዋሰው ፍላጎትን ለመለካት የተጠቀመበትን ለጥናቱ በሚመች መልኩ በመታየትና በመፈተሽ ተማሪዎቹ ለሰዋሰው ያላቸውን ፍላጎትና አመለካከት እንዲለካ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ውሏል፡፡ በአጠቃላይ በፈተና እና በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተተንትነዋል፡፡ በፈተና አማካይነት የተሰበሰበውን መረጃ መሰረት በማድረግ በቅድሚያ የተያዘው መሪ ጥያቄ በክፍል ውስጥ የሰዋሰው ትምህርትን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር በተማሪዎቹ የሰዋሰው ትምህር ዕውቀት ላይ የሚኖረውን አንድምታ ምንድነው የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ተሚክሯል፡፡ ለዚህም የባዕድ ናሙና ቲ- ቴስት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በትንተናው መሰረትም የሙከራ ቡድን አማካይ ፈተና ውጤት በስታትስቲክ ጉልህ (p>0.05) ሆኖ በመገኘቱ እና የቁጥጥር ቡድን አማካይ ውጤት በስታትስቲክ ጉልህ (p>0.05) ሆኖ ባለመገኘቱ ኢንዳክቲቭ አቀራረብ ከተለመደው አቀራረብ በላይ የተማሪዎችን የሰዋሰው ችሎታ ማሻሻል መቻሉን ለመረዳት ተችሏል፡፡

በመቀጠልም በኢንዳክቲቭ እና በተለመደው አቀራረብ ሰዋሰውን መማር የተማሪዎችን ሰዋሰው መማር የተማሪዎችን ሰዋሰው የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ የሚታየው ለውጥ ልዩነት ይኖረዋል ይሆን? የሚለው ጥያቄ ለመመስ ተሞክሯል፡፡ ለዚህም የባዕድ ናሙና ቲ- ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በትንተናው መሰረትም በሙከራ ቡድን ሰዋሰው የመማር ፍላጎት አማካይ ውጤት በስታትስቲክስ ጉልህ (p>0.05) ሆኖ በመገኘቱ እና በቁጥጥር ቡድን ሰዋሰው የመማር ፍላጎት አማካይ ውጤት መካከል በስታስቲክስ ጉልህ (p>0.05) ሆኖ ባለመገኘቱ

በኢንዳክቲቭና በተለመደው አቀራረብ ምክንያት ሰዋሰው ማስተማር በተማሪዎች ሰዋሰው የመማር ፍላጎት ላይ ልዩነት እንደሚየሳይ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ኢንዳክቲቭ አቀራረብን መሰረት በማድረግ የቀረበው የቃል ክፍልና አረፍተ ነገር ቴክስት ትምህርት በተማሪዎች ሰዋሰው የመማር ፍላጎት ላይ ለውጥ እንዳመጣ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ጥንተና ውጤት እንደሚያሳየው የተማሪዎችን የሰዋሰው ዕውቀት ለማሻሻልና የሰዋሰው ፍላጎት ለማሳደግ ለተማሪዎች የቀረቡት ቴክስቶች ሰዋሰውን ለማስተማር የኢንዳክቲቭ ዘዴ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብን መሰረት ያደረጉ ቢሆን የተሸለችሎታ ሊገኝ እንደሚችል አመልክቷል ትምህርቱም ኢንዳክቲቭ ዘዴን መሰረት አድርጎ ሰዋሰው የመማር ፍላጎትን በሚያነሳሳ መልኩ ቢቀርብ የሰዋሰው ችሎታን እንደሚያጎለብት ውጤቱ ይጠቁማል፡፡ በተጨማሪም ተጠኚዎቹ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች እንደመሆናቸው መጠን አሳታፊ የሆነውን የኢንዳክቲቭ ዘዴ ሰዋሰውን በተግባሪዊ መልኩ እንዲማሩ መደረጉ ወይም በሙከራው ውስጥ መካተቱ ተጠኚዎቹ የለምንን ፍርሃት በግልፅነት ለሰዋሰው ትምህርት ያላቸውን ቀረቤታ አሳይቷል፡፡ ለውደፊትም በተማሪዎች ላይ አሳታፊ በሆነ መልክ መምህራን የኢንዳክቲቭ ዘዴን ተጠቅመው ቢያስተምሩ ተማሪዎች በሰዋሰው ትምህርት እንዲቀርቡ እና ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ይህ የኢንዳክቲቭ ዘዴ ጥናት የተወሰነ ጥቆማ ይሰጣል፡፡

## 4.2መደምደሚያ

በአጠቃላይ የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ መሰረት በማድረግ የሚከተሉት መደምደሚያ ላይ መድረስ ተችሏል፡፡

1- አጠቃላይ የውጤት ትንተና እንደሚያመለክተው በክፍል ውስጥ የሰዋሰው ትምህርትን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር በተማሪዎቹ የሰዋሰው ትምህርት ዕውቀት ላይ በጎ የሆነ አንድምታ ያለው መሆኑን

2- የሰዋሰው ትምህርትን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ሲማሩ ከተለመደው አቀራረብ እና በኢንዳክቲቭ አቀራረብ ፈተናዎች መካከል ያለውን ልዩነት ለማወቅ በተሰራው የባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት መሰረት በኢንዳክቲቭ አቀራረብ የተማሩት የፈተና ውጤት የቲ-ቴስት መሰረት በኢንዳክቲቭ አቀራረብ የተማሩት የፈተና ውጤት የቲ-ዋጋ ከt-cri ዋጋ ልቆ በመገኘቱና በተለመደው አቀራረብ የተማሩት የፈተና ውጤት የt-ዋጋ ከt-cri ዋጋ አንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም ከተለመደው አቀራረብ ይልቅ በኢንዳክቲቭ ዘዴ መማራቸው ለተማሪዎች የተሻለ ግን ዛቤን እንዲሰጣቸው ያረጋግጣል፡፡

3- በተለመደው የክፍል ውስጥ አቀራረብና በኢንዳክቲቭ ዘዴ ሰዋሰውን መማር የተማሪዎቹን ሰዋሰው የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ ልዩነት ይታያል፡፡ ይህም ኢንዳክቲቭ ዘዴ ከተለመደው አቀራረብ በተሻለ ሁኔታ የተማሪዎችን ሰዋሰው የመማር ፍላጎት በማነሳሳት ረገድ የተሻለ ሚና እንዳለው አቅጣጫ ያሳያል፡፡

## 4.3የመፍትሔ ሃሳቦች

በዚህ በኢንዳክቲቭ ዘዴ ጥናት ውስጥ የተገኙትን ውጤቶችና ማብራሪያዎች ተግባራዊ ለማድረግ እንዲሁም የተማሪዎችን የሰዋሰው ዕውቀት የመማር ፍላጎት ከፍ ለማድረግ እንዲሁም ከሰዋሰው ትምህርት ጋር የበለጠ ትስስር እንዲኖረውቸው ለማድረግ የሚከተሉት የመፍትሔ ሃሳቦች ተምጠዋል፡፡

1- የሰዋሰው ትምህርት በቋንቋ ውስጥ መሰረታዊ መሆኑን መምህራን ተገንዝበው ሰዋሰውን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ተጠቅመው ተማሪዎችን ቢያስተምሩ የተማሪዎች የሰዋሰው ችሎታ የበለጠ እየተሻሻለ ሊሄድ ይችላል፡፡ እንዲሁም በራስ መተማመናቸው ሊጨምር ይችላል፡፡
2- ተማሪዎች ከተለመደው የክፍል ውስጥ የሰዋሰው ትምህርት ውጪ በኢንዳክቲቭ ዘዴ ቢማሩ የመማር ፍላጎታቸው በተሻለ ሁኔታ እየጨመረ እንደሚሄድ በመገንዘብ መምህራን ይህን ዘዴ በየጊዜው ቢጠቀሙ የተሻ ለ ውጤት ሊመዘገብ ይችላል፡፡

# ዋቢ መፃህፍት

ማረው ዓለሙ፡፡ (2003)፡፡ ዘመናዊ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ፡፡ (2ኛ ዕትም)፡፡ አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ባዬ ይማም፡፡ (2000)፡፡ የአማርኛ ሰዋሰው፡፡ አዲስ አበባ ካልቸው ኤንድ አርት ሶስይቲ ኦፍ ኢትዮጵያ (ኬዝ) የተሻሻለ ሁለተኛ ዕትም፡፡

ትጃኒ ምትኩ፡፡ (2007)፡፡ "ኢንዳክቲቭና ዲዳክቲቭ ዘዴዎችን አዋህዶ ሰዋሰውን ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋሰው ዕውቀትና ሰዋሰው የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና" ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)

አለም እሸቱ፡፡ (1992)፡፡ መሰረታዊ የምርምር ዘገባ አፃፃፍ፡፡ አዲ አበባ ንግድ ማተሚያ ቤት

ያለው እንዳወቅ፡፡ (2004)፡፡ የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር፡፡ (ሶስተኛ ዕትም)፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፡ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ጌታሁን አማረ፡፡ (1995)፡፡ ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋሰው በቀላል አቀራረብ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ንግድ ማተሚያ ቤት

Al Ghazali,F, (2006) The presentation-practice-production Vs Cobciousness-Raising: Which is Efficient in Teaching Grammer? The University of Birrn-ibham Upu blished

Alkalbani, N. (2004). "Oman English Teachers and students perceptions of the role of Grammer instruction EFL teaching and learing : Sultan Qabous Univesity

Akinbote. (2010). Effective of deductive Approach on Teaching Grammar in the writing course Thailand. Sonngkla University

Anne, S. (2007). Basic English Grammar for English Language Learnners. USA: Saddle back Education Publish

Azar.B.(1989). Understanding and using English Grammer. New Jersey; Prentice Hall, Inc.

Brown, H.D. (1980) Principles of learning and theaching . Newjeresey : prentice HallInce ,

Brown H.D (1994). Peiciples of language learning and Teaching ,Engle wood cliffs , NJ : prentice Hall Regents ,

Brown's (1999). the uses of gramatical teminology in the second language class room ; aqualitive stady of theachers' practices and congnitions . Applied linguistics, (20(11)),- 126.

Celce- Murica M. (1999) .Teaching English as A second or forein language. (2nd Edition). Losanjeles: Heinleand publisher .

Derebssa Dufera. (n.a). Quality of Teaching and learning in Ethiopian primery schools: Tension between Traditional and Innovative teaching learning.

Ellis, R (1993), The strutureal syllabus and second language acquistion. TESOL, Quarterly 27,1,91-113.

Fortune, A. (1992). Self-study grammer practical: learners ‘viwes and preferences. English language Teaching jornal 46(2), 160-171.

Fotos, S. (1994). Integrating grammer instructuction and communicative language use through grammer consciousness-raising tasks. TESO Quarterly, 28,323-35/.

Gray, D. (2004) .Doing Resarch in the Real worled.SAGE publications London.

Green, P,(1988), ”implicit and explicit grammer” an emprical study. Applied lingustics 134:168-84.

Hilemaryam Yimenu. (2011). “Investigating Teachers Application of the Indactive Approach to Grammer Teaching” Bahirdar University. (unpublished MA Thesis)

Halliday. M. (2004).An Introduction to function Grammer.London Edward Arold.

Hppt://www.google.com/search? site: and sourse: hp and q= halliday.M.(2004)tan.

Harmer,J, (1987), Teahing and learnig Grammer.London publisher

Hayder.A.(2012) The usefullness of systematic Functional Grammer and its impact on students communicative skill.Europan scientific journal Vol.18 No.http://www.google.com/search?q=The ussefulness + of + systemic + functional.

Herron, C,and Tomasello, M. (1992). Acquiring Grammatical stractures by Guided induction.65(5)708-718.

Kate,P.(2005).Literacy Texts and Grammer Instruction Rivising The inductive presentation.Michipan:Wayne state University,foreing language Vol,38(1).

Krashen,S.(1982).principles and practice in second language acquisition.Engle wood cliffs,NJ:prenticehall.

Krashen,S.(1985).The Inpuct Hypothesis:Issues and Implications.Newyork;longman.larson Freemaan,D.(1997) Grammer. Diamnession.(2nd Ed).Henile:publisher.

Lin.M.H.(19860 the effects of the educative and dedish Grammer acquistion.Taiwan:Chaoyang University of technology.

Lightbown,M.and spead.nina(2006). How languages are learned (3rd Edition).China Oxford Universit press.

MC culture,E.S(2006). Six middle school English language arts Teaching Bliefs about Grammer and theilr teaching of grammer while participting in a professional learning community.Geogria : college of education. Georgia state University [etd-11122006-225340]

Mellese Gelanch.(2008).”Amharic second language Teaching pedagogical grammer approaches.The case of oromia.”Addis Abeba University.(unpublished MA Thesis).

Nuna,D.(1999).second language teaching and learning Boaston: Heinle and Heinle.

Pennon,E.(2006).From theoretical to pedagogical Grammer:Raintering the role of grammer in English language Teacheing.Hunggary.

Parichat,C.(2009).Effectiveness of an indactive Approach on the Teaching of Grammer in the writing course,lecturer:faculty of International studies: Thailand prince of songkla Univesity. Mailto: paric hart.c@phuket.pus.ac.t .

Richardes,J.U and Rogers,TS.(1986), Approach and method in language Teaching: Adescription and analysis, cambrange: cup

Roper,P.C(1956). Teaching colleg Grammer by Induction and education: The Modern language Jornal, Vol, 40, No.2fed,1956,pp.76-79.

Ruther Forde,W. (1984) second language Grammer learning and Teaching. London, New york longman.

Stern,H (1983). Fundamental concepts of language Teachimg. Oxford: Oxforde Univesity press.

Terrell,T. (1977).A National Approach to second language Acquistion and learning. Modern languaage Journal 61,325-336.

Thornbury,S.(1999).How to teach Grammer.Harlow:longman.

Ur,P.(1988).Grammer practice activities : A practical guide for teachers Attitueds: (UMI9960674).

Wang,P.(2012),Teaching and learning english verb Tenses in Taiwanese University:Applied foring language Departments,National Kaohsivng,807, Taiwan Vol,1,No:1:2012 URL:

http://dx.doi.org/10.5430/elr, Vlnlp 18 Acceted : April 5 ,2016,

Widdowson,H. (1978).Teaching language as a communication. Oxford: Oxford University press.

Wilkins,D. (1978). National syllabuses. Oxford: Oxford University press.

# አባሪዎች

## አባሪ “ሀ”

ሰዋሰውን በኢንዳክቲቭ ዘዴ ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ለመመርመር ለተሰራ ጥናት የቃል ክፍሎችን እና ዐረፍተ ነገሮችን ተጠቅሞ ለማስተማር የተዘጋጀ የማስተማሪያ ቴክስት፡፡

ይህ የመማር /ማስተማሪያ ቴክስት ማረው (2003፡43) Hopkinson (2002) ዋቢ. በማድረግ እንደገለፁት በኢንዳክቲቭ ዘዴ የሚማሩ ተማሪዎች በመጀመሪያ እንዲገቡ የሚደረጉት መረጃ ውስጥ ነው፡፡ በተባለው መሰረት ይዘቱ ከስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መፃፍ እና መርሀ ትምህርት መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡ የቃል ክፍሎችን እንዲሁም አረፍተ ነገርን በትምህርት ይዘትነት በመምረጥ ትምህርቱ የቀረበ ሲሆን ለተመረጡ የትምህርት ይዘቶች ማለትም የቃል ክፍሎችን እና አረፍተ ነገሮችን ተማሪዎች ከአካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት የተለያዩ ምሳሌዎችን እንዲያቀርቡ ለማድረግ ተሞክሯል ፡፡

**መምህር ታረቀኝ አብርሃም**

**የትምህርት ክፍለጊዜያት** ሰኞ፣ ረቡዕ እና ዓርብ በቀን ለሀምሳ (50) ደቂቃ

**የመማሪያ ክፍል** :-መደበኛ የመማሪያ ክፍሎች

### ክፍለ ትምህርት አንድ፡-ስም

በዚህ ክፍለ ትምህርት የስም ምንነት አንድ ቃል በስም የቃል ክፍል ለመመደብ ማሟላት ያለበት መስፈርት ከተለያዩ ምሳሌዎች ውይይቶችና ምልልሶች አንፃር እንዲለዩ ይቀርብበታል፡፡

**ለትምህርቱ የተመደበው ሰዓት**፡-1፡40 (ሁለት ክፍለጊዜ)

**ተግባር አንድ** ፡- መምህሩ ከተማሪዎች መካከል አራት ተማሪዎችን ተራ በተራ በማስነሳት ስሞችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ ከተማሪዎች የሚገኘውን ምላሽ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ማለማመድ፡፡

ለምሳሌ፡-መምህር (የአቤልን ስም በመጥራት) ታዋቂ የሆኑ አትሌቶችን ስም ጥራ?

**አቤል** ፡-

ደራርቱ   ፖልቱርጋት     ሀይሌ               ቀነኒሳ

መምህር (የአቤኔዘርን ስም በመጥራት) ከአዕዋፍ መካከል አራቱን ጥቀስ?

- ጅራ     -ጉጉት      -እርግብ       -ጩሉሌ

መምህር (የዲቦራን ስም  በመጥራት ) ከተሰባሪ እቃዎች  መካከል አራቱን ጥቀሺ?

**ዲቦራ**፡- ሲኒ                ቡሽ

ብርጭቆ                ጀበና

መምህር (የፈጠነን ስም በመጥራት )  ከግዙፍ እንስሳት ውስጥ ሶስቱን ጥቀስ?

**ፈጠነ**፡- ዝሆን              አውራሪስ

ጉማሬ

መምህር (የገነትን ስም በመጥራት) የወል ስም ከሆኑት መካከል  አምስቱን ጥቀሺ?

**ገነት**፡- ትምህርት ቤት

ሰራዊት              ሀገር

እስር ቤት             አረጋውያን

**ተግባር ሁለት**

ሶስት ተማሪዎች በፍቃደኝነት በማስነሳት የወል ስሞች ለምን እንደሚጠቅሙ በመጠየቅ ተማሪዎቹ የሚሰጡትን መልስ በሰሌዳ ላይ በመፃፍ ሌሎቹ  እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሁለት፡- ግስ**

በዚህ ክፍል የግስ ምንነት የግስ ተግባር እና አንድ ቃል ግስ  ለመባል የሚያሚላውን መስፈርት ከተለያዩ  ምልልሶችና ከተለያዩ ምሳሌዎች  አንፃር እንዲገነዘቡ የሚቀርብበት ክልፍል ነው፡፡

### ለትምህርቱ የተመደበ ሰዓት፡- 1፡40 (ሁለት ክፍለ ጊዜ)

### ተግባር አንድ

አንድ ወንድ እና አንድ ሴት ተማሪ በማስነሳት አጭር ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ በማድረግ ግስነብ ማለማመድ ፡፡ ተግባራዊ እንቅስቃሴውም፡፡

ለምሳሌ፡- ኪሩቤል ሻይ ሲጠጣ የሚመለክት እና ሒሩት ኪሩቤል ሻይውን ጠጥቶ ቶሎ ወደ ትምህርት ቤት እንዲሄድ ስትነግረው የሚያመላክት እንዲሆን ማድረግ ከዚያም ሁለቱ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ ፡፡ ሌላ አንድ ተማሪ በመነሳት ኪሩቤል ምን አደረገ? ብሎ ተማሪዎችን እንዲጠይቅ በማድረግ ከተማሪዎቹ የሚገኘውን መልስ መምህሩ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ከዚያም ተማሪዎች በግስ የቃል ክፍል የሚመደበውን እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡ ከዚያም ሌሎቹንም ተማሪዎች በዚሁ መልክ እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

### ተግባር ሁለት

ተማሪዎች ከቤተሰባቸው ወይም ከሚያውቁት ሰው ከሚከተሉት በየትኛው ሞያ እንደሚሳተፉ እንዲናገሩ ማደውረግ፡፡ ቃላቱም፡- ፓይለት ፤ ኢንጂነር ፤ገበሬ ፤ ዳኛ ፤ከየትኛው እንደሆነ የተናገሩትን በጥቁር ሰሌዳ ለይ በመፃፍ ግሶችን ማለማመድ ይቻላል፡፡

ዘላለም ፓይሌት ሆነ፡፡

ሲትራ እንጂነር ሆነች፡፡

በላይ ገበሬ ሆነ፡፡

ኤርሚያስ ዳኛ ሆነ፡፡

ከዚህ በመነሳት ተማሪዎቹ ከተዘረዘሩት ምሳሌዎች በተጨማሪ መሰል ምሳሌዎችን ተወያይተው በመስጠት ተማሪዎቹ ከሰጡት የተወሰኑትን በጥቅር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ግስን እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

በሌላ መንገድ በሁለት ተማሪዎች መካከል ምልልስ እንዲቀርብ በማዘዝ የተማሪዎችን ንግግር በጥቅር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ግስን እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

የተማሪዎቹ ምልልስ እንደሚከተለው ነው፡፡

ገመችስ ፡- የአማርኛ መፅሐፍ አለህ?

ዳግም ፡-የአማርኛ መፅሐፌ ክፍል ውስጥ ጠፋብኝ፡፡

ከላይ የቀረቡ ምሳሌዎችን መሰረት ባማድረግ ተማሪዎች ግሶችን እንዲለማመዱ ማድረግ በመጨረሻም አንድ ቃል በግስ የቃል ክፍል ለመመደብ  የመሆን ፤ የመኖር ፤ሌሎች ተግባራትን የሚያመለክት እንዲሁም በዓረፍተ ነገር ውስጥ በስተመጨረሻ በመግባት ዓረፍተ ነገሩ የተሟላ ሀሳብ እንዲሰጥ የሚያደርጉ መሆናቸውን ከምልልሳቸው እንዲገነዘቡ ማድረግ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሶስት ፡- ቅፅል**

በዚህ ክፍለ ትምህርት ከቃል ክፍሎች ቅፅልን በመውሰድ  የሚቀርብ ይሆናል፡፡በክፍለ ትምህርቱም የቅፅል ምንነት አንድ ቃል በቅፅል ለመመደብ ማሟላት ያለበትን መስፈርቶች እና ቅፅሎች ተግባራቸው ምን እንደሆነ  የሚቀርብበት ይሆናል፡፡

**ለትምህርት የተመደበው ጊዜ 1፡40 (ሁለት ክፍለ ጊዜ)**

**ተግባር አንድ ፡-**

ሁለት አይነት ጠመኔዎችን ወደመማሪያ ክፍል ይዞ በመምጣት ጠመኔዎቹን ለተማሪዎቹ ተራ በተራ በማሳየት ጠመኔዎቹ ያሉበትን ደረጃ እንዲገልፁ  ማድረግ ከተማሪዎቹ የሚገኘው መልስ የሚከተለውን እንዲመስል በማድረግ ማለማመድ፡፡

ነጭ ጠመኔ

ቢጫ ጠመኔ

የተገኘውንም መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ  በቅፅል የቃል ክፍል የሚመደቡትን ከላይ በቀረበው መንገድ እንዲያመለክቱ በማድረግ ማለማመድ፡፡

ሁለት የተለያየ መጠን ያላቸውን እርሳሶች በማሳየት የእርሳሶቹን መጠን እንዲናገሩ ማድረግ፡፡

ከተማሪዎቹ የተገኘውን መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ቅፅሎችን እንዲለዩ ማድረግ፡፡

### ተግባር ሁለት ፡-

በአካባቢያቸው የተለያዩ በህሪ ያላቸውን የቤት እንስሳት በአዕምሯቸው እንዲያስቡ ማዘዝ ከዚያም ያስታወሱትን እንስሳ ባህሪ እንዲናገሩ ማድረግ፡፡ ከተማሪዎቹ የተገኘውን መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ቅፅሎችን በሚከተለው መልኩ እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

ቁጡ እንስሳ

ተዋጊ እንስሳ

ተናካሽ እንስሳ

በተማሪዎች ፊት የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ በማሳየት ከላይ ወደታች ምን አይነት መልክ እንዳለው እንዲገልፁ በማድረግ ቅፅሎችን ማለማመድ፡፡

የተለያዩ ነገሮችን የያዘ ምስል ፖስተር ወደ ክፍል በማምጣት ተማሪዎች ከፖስተሩ ላይ እያዩ ከለሮችን እንዲናገሩ ማድረግ፡፡

| ዓይነት | የተማሪዎች መልስ |
|---|---|
| ወረቀት | ነጭ |
| ጠጅ | ቢጫ |
| ወተት | ነጭ |
| ሳር | አረንጓዴ |

ተማሪዎች ከዚህ ልምምድ በመነሳት ቅፅሎችን እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አራት፡- መስተዋድድ

በዚህ ክፍል የመስተዋድድን ምንነት፤ መስተዋድዶች በዓረፍተ ነገር ውስጥ የሚኖራቸውን ተግባር ከተለያዩ ምልልሶች እና ውይይቶች አንፃር እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

**ለትምህርቱ የተመደበው ግዜ፡- 50 ደቂቃ (አንድ ክፍለ ጊዜ)**

### ተግባር አንድ ፡-

አንድ ተማሪ ወደ ሌላ ጎረቤት ትምህርት ቤት በመላክ እና ደርሶ እንዲመጣ በማድረግ ቤት በኩል ደርሶ እንደመጣ እንዲናገር በማዘዝ ከተማሪው የተገኘውን መልስ በጥቁር ሰሌዳ በመፃ ፍ ከተማሪው ከቀረበው ሀሳብ በመነሳት ሌሎች ተማሪዎች መስተዋድዶችን ለይተው እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

### ተግባር ሁለት፡-

መምህሩ ለተማሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማቅረብ ከተማሪዎች የተገኘውን መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ መስተዋድዶችን ማለማመድ፡፡

**መምህር**፡-ወደትምህርት ቤት ከማን ጋር ሄደህ ታውቃለህ?

**ተማሪ**፡- ከእህቴ ጋር

ከጓደኞቼ ጋር

**መምህር**፡-ክረምትን ከማን ጋር ተሳልፊያለሽ?

-ከቤተሰቦቼ ጋር

-ከጓደኞቼ ጋር

ከዚህ በተጨማሪ አንድ ትልቅ ጠረጴዛ አምጥቶ አንድ ተማሪ በተለያየ የጠረጴዛው ክፍሎች ጋር እየተገኘ ተማሪዎቹ እንዲያዩ በማድረግ መስተዋድዶችን እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

ለምሳሌ፡- ሞገስ ምኑ ላይ ነው?

-ጠረጴዛ ላይ

-ጠረጴዛ ስር

-ከጠረጴዛ ፊትለፊት

## ክፍለ ትምህርት አምስት፡- ተውሳከ ግስ

በዚህ ክፍለ ትምህርት ተውሳከ ግስ ከቃል ክፍል አንዱ እንደሆነና ተውሳከ ግስ በዓረፍተ ነገር ውስጥ የሚኖረውን ተግባር ለማቅረብ እንዲሞክሩ ማድረግ፡፡

**ለትምህርቱ የተመደበ ግዜ፡- 50 ደቂቃ (አንድ ክፍለ ጊዜ)**

**ተግባር አንድ፡-**

የሚከተሉትን ተግባራት ተማሪዎች እንዲፈፅሙ በማድረግ ተውሳከ ግስ ማለማመድ፡፡ ሶስት ተማሪዎች በሚከተለው መልኩ ጭውውት እንዲያቀርቡ በማድረግ ተማሪዎች ጭውውቱን ሲያቀርቡ እያንድ አንዳቸው የተናገሩትን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ከንግግራቸው ተውሳከ ግስን እንዲለዩ ማድረግ፡፡

**ተማሪ አንድ፡-** ልደት ወዴት ሄደች?

**ተማሪ ሁለት፡-** አሁን ቶሎቶሎ እየተራመደች ሄደች፡፡

**ተማሪ አንድ፡-** ኸረ! ምንኛ ድብቅ ልጅ ናት!

**ተግባር ሁለት፡-**

ሁለት ተማሪዎች ስለጓደኛቸው የትምህርት ሁኔታ እየተነጋገሩ ተውሳከ ግስን እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

**ተማሪ አንድ፡-** ዘካሪያስ ዡንድሮ ደረጃ የሚያገኝ ይመስልሀል?

**ተማሪ ሁለት፡-** አይ ዘንድሮ ከአምና የተሻለ አይመስለኝም ፡፡

በዚህ መልኩ ተማሪዎች ተውሳከ ግሶችን እንዲለዩ ማድረግ፡፡ ቀፅሎች ስምን እንደሚገልጹ ሁሉ ተውሳከ ግሶችም ግስን ከቦታ፤ ከሁኔታዎች እና ከመሳሰሉት አንፃር ከምሳሌው ሊገልፁ እንዲችሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**ክፍለ ትምህርት ስድስት፡- ጠቋሚ መስተአምር እና መስተፃምር**

**ለትምህርቱ የተመደበው ግዜ 50 ደቂቃ**

ተማሪዎች በቡድን ሆነው ጠቋሚ መስተአምሮችን እንዲለማመዱ ማድረግ ፡፡

ለምሳሌ፡- ያቺ ልጅ በትምህርቷ ጎበዝ ናት፡፡

እነዚያ ተማሪዎች አርፋጆች ናቸው፡፡

ምሳሌ በመስጠት ተማሪዎች ጠቋሚ መስተ አምርን እንዲለማመዱ ማድረግ እና እነርሱ የሚሞክሩትን ጥያቄ በሰሌዳ ላይ መፃፍ፡፡

**ተግባር ሁለት፡-** ተማሪዎች በቡድን በቡድን ሆነው መስተፃምሮችን በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡ ተማሪዎች የሰሩትን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ተጨማሪ የመስተአምር ሙከራ እንዲያደርጉ ማለማመድ፡፡

ለምሳሌ፡- አበበ ከትምህርት ቤት መጣና እናቱን ስራ አገዘ፡፡

- ልጁ በደንብ ያጠና ነበር ነገር ግን ፈተናውን ማለፍ አልቻለም፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሰባት ፡- አረፍተ ነገር**

በዚህ ክፍል የዓረፍተ ነገር ምንነት ፤ ዓረፍተ ነገር ከሁለት ዋና ዋና አካላት እንደሚመ ሰረት እነሱም ምንና ምን እንደሆኑ በውስጡም ሙሉ ሀሳብ የሚተላለፍበት መሆኑን ከተለያዩ ምልልሶችና ክስተቶች አንፃር ለማቅረብ መሞከር፡፡

**ተግባር አንድ፡-**

**ለትምህርቱ የተመደበው ግዜ 150 ደቂቃ (ሶስት ክፍለ ጊዜ)**

በመምህራንና በተማሪ መካከል የተለያዩ ክስተቶችን በተመለከተ ተማሪዎች ዓረፍተ ነገርን እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

**ለምሳሌ፡- *መምህር*፡-** በሶስተኛው ክፍለግዜ ምን ተምራችኃል?

***ተማሪዎች*፡-**ምንም አልተማርንም፡፡

***መምህር*** ፡-ክፍለጊዜው የምን ትምህርት ነበር?

***ተማሪዎች*፡-** የአማርኛ ትምህርት ነበር፡፡

***መምህር*፡-** በምን ምክንያት ሳትማሩ ቀራችሁ?

***ተማሪዎች*** ፡-የአማርኛ መምህር ታመው ስለቀሩ ነው፡፡

**ተግባር ሁለት ፡-**

ተማሪዎች ከተሰጡ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ስማዊ ሐረጎችን እንዲለዩ ማድረግ፡፡

ለምሳሌ ፡- ትብለጥ ሰነፍ ተማሪ ናት ፡፡

-አሰገደች ታታሪ ሴት ናት፡፡

**ተግባር ሶስት ፡-**

ተማሪዎች ከሚሰጡ ዓረፍተ ነገሮች ጥገኛ ሀረጎችን እንዲለዩ በማድረግ ማለማመድ፡፡

ለምሳሌ ፡- <u>**አለምነሽ ስትመጣ**</u> ፤እኔ ወደ ትምህርት ቤት ሄድኩ፡፡

<u>**-እኔ ቡና ስጠጣ፤**</u> እነሱ ምሳ እየበሉ ናቸው

## ተግባር አራት፡-

ተማሪዎች አሉታዊ አረፍተ ነገሮችን እየሰሩ እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

ለምሳሌ፡-ልጁ ወደትምህርት ቤት አልሄደም፡፡

-አየለ በሬ ገዛ፡፡

-ልጅቷ የቤት ስራውን አልሰራችም፡፡

-ፀጋ ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡

-መቅደስ ወደትምህርት ቤት ስትሄድ ቁርሷን አልበላችም ፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ አሉታዊ ዓረፍተ ነገርን እየጠቀሱ እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

## ተግባር ስድስት፡-

ተማሪዎች መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገርን እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

ለምሳሌ፡-ልጁ ወዴት ሄደ?

-የልጅቷ ውጤት ዝቅተኛ ሆነ እንዴ?

-አበበ! ለምን ትምርትህን አታጠናም?

## ተግባር ሰባት፡-

ቃላትን አዘበራርቆ ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ተማሪዎች አስተካክለው በአገባቡ ዓረፍተ ነገርን እንዲመሰርቱ ማድረግ፡፡

ለምሳሌ፡-መቅደስ ሄደች ወደ ገበያ (መቅደስ ወደ ገበያ ሄደች)

-ቃልኪዳን ተማሪ ናት ሰነፍ (ቃልኪዳን ሰነፍ ተማሪ ናት)

-ኢክራም ጥላ ተገረፈች መፅሐፏን ( ኢክራም መፅሐፏን ጥላ ተገረፈች)

በመጨረሻም ተጨማሪ ምሳሌ በመስጠት ተማሪዎች ዓረፍተ ነገር እያስተካከሉ በመፃፍ እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

## አባሪ ( ለ ) -ቅድመ ትምህርት ፈተና

እንዳክቲቭ ዘዴን ተጠቅሞ ሰዋስውን ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት በማጎልበት ረገድ የሚኖረው ሚና በሚል ርዕስ ለሚካሄደው ጥናት የተማሪዎች ቅድመ ችሎታ ውጤት መረጃ እንዲያስገኝ ለማወቅ ለስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና፡፡

**ስም --------------------ክፍል-------ተራ ቁጥር (ኮድ)--------ጾታ----------**

***ፈተናው የተጀመረበት ሰዓት፡- 4፡00***

***ለፈተናው የተፈቀደው ሰዓት፡-50 ደቂቃ***

***አጠቃላይ መመሪያ*** *፡-ይህ ፈተና በሊሙ ገነት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኢንዳክቲቭ የሰዋስው ትምህርት ዘዴ የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለመፈተሽ እየተካሄደ ላለው ጥናት የተጠኚ ተማሪዎችን ቅድመ ትምህርት ውጤት ለማወቅ ታስቦ ለመረጃ መሰብሰቢያ ነት የተዘጋጀ ፈተና ነው፡፡*

*ፈተናው አራት ዋና ዋና ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል አስራ አምስት የምርጫ ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ አምስት ያዛምድ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ ሶስተኛው ክፍል ሶስት የባዶ ቦታ ሙላ ጥያቄዎችን ሲይዝ አራተኛው ክፍል ደግሞ ተዘበራርቀው ያሉ ቃላትን አስተካክሎ ዓረፍተ ነገር መመስረትን የያዘ ነው፡፡*

*የጥያቄውም ብዛት ሁለት ነው ፡፡በአጠቃላይ የጥያቄዎቹ ብዛት ሃያ አምስት ሲሆን ከ* 50% *የሚያዝ ነው፡፡ በየክፍሉ ለቀረቡ ጥያቄዎች ሌሎች ንዑሳን መመሪዎች የተዘጋጁ ስለሆነ እንደየ ንዑሳን ክፍሎች መመሪያ አጠያየቅ ተገቢውን መልስ ስጥ/ጪ፡፡*

***ማሳሰቢያ፡- ፈተናውን እንድትገልፅ/ጪ መምህሩ ሳያዝህ /ሽ ፈተናውን ገልፆ መስራት የተከለከለ ነው፡፡***

## ***ክፍል አንድ፡- የምርጫ ጥያቄዎች***

***መመሪያ አንድ*** *፡- የሚከተሉት ጥያቄዎች የቃል ክፍሎችን ምህላዶችንና ዓረፍተ ነገሮችን መሰረት በማድረግ የቀረቡ ናቸው፡፡ ከቀረቡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ ፊት ለፊት በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ላይ ሙላ/ይ* (30%)

---1) *"ተማሪዎቻችን" በሚለው ቃል ውስጥ ነጻ ምዕላድ የሆነው የቱ ነው?*

*ሀ) ተማሪ ለ) -ኣችን ሐ)-ነታችን መ) ዎቻችን*

---2) *አየለ በሬ <u>ገዛ</u>፡፡ የተሰመረበት ቃል_የቃል ክፍል ምን ይባላል?*

*ሀ) ቅፅል ለ) ግስ ሐ) ተውሳከ ግስ መ) ስም*

---3) ***<u>ያቺ</u>*** *ልጅ ወዴት እየሄደች ነው፡፡ በሚለው ዓረፍተ ነገር ስር የተሰመረበት ቃል፡-*

*ሀ) መስተፃምር ለ) ቅፅል ሐ) ጠቋሚ መስተ አምር መ) የመሆን ግስ*

---4) *ሲጠብቅም ሆነ ሲላላ ትርጉም የሚሰጠው የቱ ነው?*

ሀ)ጠራ ለ)ሊጋ ሐ)ፈራ መ)ደመና

---5) ሲጋው ጮማ ነው በሚለው በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ቅፅል የሆነው የቱ ነው?

ሀ) ሲጋው ለ) ነው ሐ) ጮማ መ) መልስ የለም

----6) አያንቱ <u>**ታታሪ ሴት**</u> ናት፡፡ የተሰመረበት ቃል፡-

ሀ) ግሳዊ ሐረግ ለ) ስማዊ ሐረግ ሐ) ተውሳከ ግሳዊ ሐረግ መ) መስተዋድዳዊ ሐረግ

---7) <u>**"እኔ ላይ ሲዘንብብኝ፤**</u> አንቺ ላይ ያካፋል" በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ፡፡

ሀ) ጥገኛ ዓረፍተ ነገር ለ) ሙሉ ዓረፍተ ነገር ሐ) ቅፅል መ) መልስ የለም

----8) ‹‹ አለሚቱ ከስራ መጣችና ምግብዋን አዘጋጀች ›› በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ አያያዥ መስተፃምር የቱ ነው?

ሀ) አዘጋጀች ለ) ከስራ ሐ) ምግቧን መ) ና

---9) ከሚከተሉት ውስጥ ጠቋሚ መስተአምር የሆነው የቱ ነው?

ሀ) ነገር ግን ለ) ቶሎ ቶሎ ሐ) እነዚያ መ) ወይም

--- 10) ግጥም <u>**ረጅም እድሜ**</u> አለው፡፡ የተሰመረበት ቃል ፡-

ሀ) ግሳዊ ሀረግ ለ) ቅፅላዊ ሀረግ ሐ) ስማዊ ሀረግ መ) ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ

------11)ልጁን <u>**ፀሐይ**</u> አቃጠለው፡፡የተሰመረበት ቃል፡-

ሀ)ቅፅል ለ)ተውሳከ ግስ ሐ)ግስ መ)ስም

-------12)ከሚከተሉት ውስጥ መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገር የሆነው የቱ ነው?

ሀ)ዳቦ ለምን ይጠቅማል፡፡ ለ)በጥገኝነት መኖር አያዋጣም፡፡ ሐ)ስራ መስራት ምርታማ ያደርጋል መ)ሁሉም፡፡

---------13)‹‹መሰረት ወደ ጎንደር እየሄደች ነው››በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ጊዜ አመልካች ቅርፅ የሆነው የቱ ነው?

ሀ)እየሄደች ነው   ለ)ወደ ጎንደር   ሐ)መሰረት   መ)መልስ የለም

-----14) ማንም ሰው ስለ ሀገሩ መቆርቆር አለበት፡፡የተሰመረበት ቃል ፡፡

ሀ) ግስ   ለ) ስም   ሐ ) ተውሳከ ግስ   መ) መስተዋድድ

----15) ‹‹ቶሎቶሎ ምሳውን በልቶ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ›› በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ተውሳከ ግስ የሆነው የቱ ነው?

ሀ) ምሳውን   ለ) በልቶ   ሐ) ቶሎቶሎ   መ) ትምህርት ቤት

**ክፍል ሁለት፡-የአዛምድ ጥያቄዎች**

***መመሪያ ሁለት፡-***ከታች የተዘረዘሩትን ቃላት ተቃራኒያቸውን በመፈለግ አዛምድ፡፡ (10 ፐርሰንት)

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| -1) ረጅም | ሀ) ቆንጆ |
| -2)ወላዋይ | ለ) አጭር |
| -3) ጣፋጭ | ሐ) በጋ |
| -4) አስቀያሚ | መ) መራራ |
| - 5) ክረምት | ሠ) የፀና |

**ክፍል ሶስት ፡- ባዶ ቦታ ሙላ**

***መመሪያ ሶስት፡-***የሚከተሉት ጥያቄዎች ስማዊ ሀረግ እና ግሳዊ ሀረግ እንዲሁም ዓረፍተ ነገርን መሰረት በማድረግ የቀረቡ ናቸው፡፡ ከቀረቡት ምልልሶች ከስራቸው የተሰመረባቸው ሀረጋት በየትኛው የሀረግ ክፍል እንደሚመደቡ በቀረው ባዶ ቦታ ላይ መልስ /ሽ (6 ፐርሰንት)

---1) **<u>ትልቅ ቤት</u>** አላት፡፡ ከቀረበው አረፍተ ነገር ከስሩ የተሰመረበት ሀረግ ---------ሀረግ ይባላል፡፡

---2) ወይዘሮ ሐያት <u>ባለሞያ ሴት</u> ናቸው፡፡ የተሰመረበት ሀረግ --------ሀረግ የባላል፡፡

----3) **<u>ሌባው በር ሲሰብር፤</u>** ፖሊሱ ደርሶ ያዘው፡፡ የተሰመረበት አረፍተ ነገር -------ይባላል፡፡

**<u>ክፍል አራት፡-</u>**ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ቃላት አስተካክሎ መፃፍ፡፡

<u>***መመሪያ አራት፡***ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ቃላት አስተካክላችሁ ዐረፍተ ነገር መስርቱ፡፡(4ፐርሰንት)</u>

---1)መብላት የለበትም ሰው የማይሰራ ስራ፡፡-------------------------------------------

---2)ይዛ ሄደች ወደ እህል ወፍጮ ቤት፡፡ ---------------------------------------------------

# <u>አባሪ‹‹ሐ›› ድህረ ትምህርት ፈተና</u>

-ኢንዳክቲቭ ዘዴን ተጠቅሞ ሰዋስውን ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው ዕውቀት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና በሚል ርዕስ ለሚካሄደው ጥናት ድህረ ትምህርት መረጃ እንዲያስገኝለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና፡፡

**ስም------------------------ክፍል-----ተራ ቁጥር(ኮድ)-------ፆታ-------**

**ፈተናው የተጀመረበት ሰዓት፡-4፡00**

**ለፈተናው የተፈቀደው ሰዓት፡-50 ደቂቃ**

አጠቃላይ *መመሪያ፤* ይህ ፈተና በሊሙ ገነት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኢንዳክቲቭ የሰዋስው ትምህርት ዘዴ የተማሪዎችን የስዋስው እውቀት በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለመፈተሽ እየተካሄደ ላለው ጥናት ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተዘጋጀ ነው፡፡ፈተናው አራት ዋና ዋና ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል አስራ አምስት የምርጫ ጥያቄዎቸን ያካተተ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ አምስት የአዘምድ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ሶስተኛው ክፍል ሶስት ክፍት ቦታ ሙላ ሲይዝ አራተኛው ክፍል ተዘበራርቀው ያሉ ቃላትን አስተካክሎ ዐረፍተ ነገር መመስረትነው፡፡ብዛቱም ሁለት ሲሆን፤-በአጠቃላይ ሃያ አምስት ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ በየክፍሎቹ ለቀረቡት ጥያቄዎች ሌሎች ንዑሳን *መመሪያዎች* የተዘጋጁ ሲሆን እንደየንዑሳን ክፍሎች *መመሪያ* አጠያየቅ ተገቢውን መልስ ስጥ/ጭ፡፡

<u>*ማሳሰቢያ፡-ፈተናውን እንድትገልጽ /ጭ መምህሩ ሳያዝህ /ሽ ፈተናውን ገልፆ መስራት የተከለከለ ነው፡፡*</u>

## ክፍል አንድ ፡-የምርጫ ጥያቄዎች

***መመሪያ* አንድ ፡-** *የሚከተሉት ጥያቄዎች የቃል ክፍሎችን መሰረት በማድረግ የቀረቡ ናቸው፡፡*

*ከቀረቡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ ከጥያቄዎቹ ፊትለፊት በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ሙላ/ይ* (30 ፐርሰንት )

--1) ‹‹ከፊት›› የሚለው ቃል በሁለተኛ መደብ ሲፃፍ ምን ይሆናል?

ሀ) ከፊትን ለ) ከፊተ ሐ ) ከፊቶች መ) ከፊታችሁ

--2) ከሚከተሉት ውስጥ የአሁን ግዜን የሚያመለክተው የቱ ነው?

ሀ) እየሰበረ ነው ለ) ሰብሯል ሐ) ሰብሮ ነበር መ) ሰብረዋል

--3) ‹‹ መሐመድ ሁለት መፅሐፍ ገዝቷል›› በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ግዜ አመልካች ቅርፅ የሆነው የቱ ነው?

ሀ) መሐመድ ለ) መፃሕፍት ሐ) ገዝቷል መ) ሁለት

--4) አንተ ወይም እሷ ጥያቄውን መመለስ ትችላላችሁ በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ አያያዝ መስተፃምር የሆነው የቱ ነው?

ሀ) አንተ ለ) ወይም ሐ) መመለስ መ) እሷ

--5) ከሚከተሉት ቃላት መካከል አንዱ በስም የቃል ክፍል ይመደባል፡፡

ሀ) ክፉ ለ) መታ ሐ) ደረሰ መ) አንበሳ

--6) ሁለቱ ልጆች ከቤት **እንደ**ወጡ ቀሩ፡፡ የተሰመረበት ቃል፡-

ሀ) ተውሳከ ግስ ለ) ስም ሐ) ቅፅል መ) መስተዋድድ

--7) ኤርሚያስ **ነጭ** ፈረስ ገዛ ፡፡ የተሰመረበት ቃል፡-

ሀ) ግስ ለ) ቅፅል ሐ) ስም መ) ስማዊ ሀረግ

--8) በቀለ **አምና** ሰባተኛ ክፍል ነበር፡፡ የተሰመረበት ቃል፡-

ሀ) ተውሳከ ግስ ለ) ስም ሐ) ተውላጠ ስም መ) ስማዊ ሀረግ

--9) ‹‹ተማሪዎች ለምን አርፍዳችሁ መጣችሁ››፡፡ የሚለው አረፍተ ነገር ምን አይነት ነው?

ሀ) ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ለ)ተራ አረፍተ ነገር

ሐ) መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገር መ) አሉታዊ ዓረፍተ ነገር

--10) ወይዘሮ አየለች ጠንካራ ሴት **ናቸው**፡፡ የተሰመረበት ቃል፡-

ሀ) ቅፅል ለ) ተውላጠ ስም ሐ) የመሆን ግስ መ) ስማዊ ሐረግ

--11) ምት፣ ዜማና አንጓ **የግጥም ቃላት** ናቸው ፡፡ በሚለው ስር የተሰመረበት ቃል፡-

ሀ) ግሳዊ ሐረግ ለ) ተውሳከ ግሳዊ ሐረግ ሐ) ግስ መ) ስማዊ ሐረግ

--12) ልጅቷ **<u>ከፉኛ</u>** ታማለች፡-የተሰመረበት ቃል፡-

ሀ) ቅፅል ለ) ስም ሐ) ተውሳከ ግስ መ) ስማዊ ሐረግ

--13) ቁልቁለቱን **<u>ወደ</u>**ታች ስትወርጂ ተጠንቀቂ! የተሰመረበት ቃል፡-

ሀ) ስም ለ) መስተዋድድ ሐ) መስተፃምር መ) ስማዊ ሐረግ

--14) ከሚከተሉት ውስጥ በሳድስ ፊደል ያለቀው ቃል የቱ ነው?

ሀ)ሀገር ለ) ጫማ ሐ) መርፌ መ) በሶ

--15) ቡና መጠጣት ፈልጌ ነበር፤ **<u>ነገር ግን</u>** ገንዘብ የለኝም ፡፡የተሰመረበት ቃል፡-

ሀ) መስተ አምር ለ) ግስ ሐ) መስተፃምር መ ) መስተዋድዳዊ ሐረግ

**ከፍል ሁለት፡- የአዛምድ ጥያቄዎች**

***መመሪያ ሁለት፡-*** ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን ፈልገህ /ሽ አዛምድ/ጂ(10ፐርሰንት)

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1) ጥሩ | ሀ) የማይረባ |
| 2) ብልህ | ለ) መልካም |
| 3) ሆደ ባሻ | ሐ) ቶሎ የሚከፋው |
| 4) መናኛ | መ) አስተዋይ |
| 5) መሬት | ሠ) ምድር |

## ክፍል ሶስት፡-ባዶ ቦታ ሙላ

**መመሪያ ሶስት፡-** የሚከተሉትን ጥያቄዎች ስማዊ ሐረግ እና ግሳዊ ሐረግ እንዲሁም ዓረፍተ ነገርን መሰረት በማድረግ የቀረቡ ናቸው፡፡ ከቀረቡት ምልልሶች ከስራቸው የተሰመረባቸው ሐረጋት በየትኛው የሐረግ ክፍል እንደሚመደቡ በቀረበው ባዶ ቦታ ላይ መልስ/ሺ (6 ፐርሰንት)

1) አየለ ጎሽ አደነ፡፡ የተሰመረበት ቃል -------ይባላል፡፡
2) ማሞ ትልቅ መኪና ገዛ፡፡ የተሰመረበት ቃል ----------ይባላል፡፡
3) ሁለት ሐረጋት በአንድ ላይ ተጣምረው ---------ይሰጣሉ፡፡

**ክፍል አራት፡- ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ቃላት አስተካክሎ መፃፍ**

1) ጣሉት ደብተሬን መምህሩ ቀደው፡፡-------------------------------------------.
2) ሁሌም ይተያያሉ አንበሳና በጎሪጥ ነብር ፡፡-----------------------------------.

## አባሪ (መ)

**በቅድመ ትምህርት እና በድህረ ትምህርት የሚሞላ የፅሑፍ መጠይቅ**

**ውድ ተማሪዎች፡-** የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው መማር /ማስተማር ሒደት ላይ ጥናት ለማድረግ ነው፡፡ ጥናቱ በተለይ ከዝርዝር ወደ ጥቅል አቀራረብ እና ከጥቅል ወደ ዝርዝር ሰዋስውን ማስተማር በተማሪዎች ሰዋስው የመማር ፍላጎት ማጎልበት ላይ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ ለሚካሄድ ጥናት መረጃ ለማግኘት ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ዝተርዝር ጥያቄዎች ለያንድ አንዳቸው አራት አራት አማራጭ መልሶች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ አማራጭ መልሶች በቁጥር የተሰየሙ ሲሆኑ ቁጥሮቹም የሚከተሉትን የመስማማት ደረጃ ይወክላሉ፡፡ ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ሲደረደሩ በሚከተለው መልኩ ቀርበዋል፡፡

4=በጣም እስማማለሁ

3=እስማማለሁ

2=አልስማማም

1=በጭራሽ አልስማማም

ስለዚህ ከዚህ በታች የቀረቡትን ዝርዝር ጥያቄዎች በማንበብ ያንተን/ችን ሀሳብ ወይም እምነት ያንፀባርቃል የምትለውን /ይውን ከተሰጡት አማራጮች መካከል አንድ ምርጫ

በመምረጥ ከያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር ፊትለፊት ይህን ( ) ምልክት በማድረግ ስምምነትህን/ሽን አመልክት/ቺ፡፡

አንተ /ቺ የምትሰጠው /ጪው መልስ ለጥናቱ መሳካት ከፍተኛ ድርሻ ያለው በመሆኑ በተቻለ መጠን የምትሰጣቸው /ጫቸው መልሶች በትክክል ያንተን /ቺን ስሜትና እምነት የሚያንፀባርቁ እንዲሆኑ አደራ እላለሁ፡፡ በዚህ የመልስ ወረቀት ላይ ስምህን /ሽን መፃፍ አያስፈልግም የምትሰጠው /ጪው መልስ በሚስጥር የሚያዝ ሲሆን ይህንን መልስ በምትሰጥበት/ጪበት ግዜ በተረጋጋ አዕምሮ ግዜ ሰጥተህ /ተሽ መሆን ይገባዋል ይህም ለጥናቱን ጥራት የራሱ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡

**ስለቀና ትብብርህ /ርሽ ስለታማኝነትህ /ትሽ ከልብ አመሰግናለሁ፡**

| ተራ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| 1 | መምህሬ ፍፁም የሰዋስው ትክክለኛነት ላይ ባያተኩሩ እመርጣለሁ | | | | |
| 2 | ሰዋስው ለመማር እና ለማወቅ ከመምህር ተኮር ተማሪ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ያስደስተኛል | | | | |
| 3 | መምህሬ ሰዋስው ሲያስተምሩ በቃል ከማስረዳት በተጨማሪ በአውድ እንድጠቀም ሲያደርጉ ያስደስተኛል | | | | |
| 4 | ከምሳሌዎቹ በመነሳት የራሴን ምሳሌ በመስጠት ህግጋት ላይ በመድረስ ሰዋስው የመማር ሂደት በራስ መተማመኔን ከፍ ያደርግልኛል | | | | |
| 5 | የአማርኛ መምህራችን የሰዋስው ህጎችን በራሴ እንድደርስበት ሲያደርጉ ደስ ይለኛል | | | | |
| 6 | ቋንቋዬን ለማሻሻል መምህሬ የሰዋስው ህጎችን እያሰብኩ ቋንቋ ውን እንድጠቀም ከማድረግየራሴን ምሳሌ እየሰጠሁ በቋንቋው እንድጠቀም ቢያደርጉ ደስ ይለኛል | | | | |
| 7 | በቃል ልምምድ ግዜ የሰዋስው ስተቶችን ሁልግዜ በራሴ እያረምኩ ስማር ደስ ይለኛል | | | | |
| 8 | መምህሬ ሰዋስው ሲያስተምሩ ምሳሌዎችን እየሰጡ ከምሳሌዎቹ መዋቅራዊ ህግጋትን እየለዩ ሲያስተምሩ ደስ ይለኛል | | | | |
| 9 | መምህሬ ለመግባባት የሚያስችል የሰዋስው ዕውቀት ለማስጨበጥ ከሚሰጡኝ ምሳሌ በመነሳት የራሴን ምሳሌ እየሰጠሁ እንድማር የሚያግዙ የግንዛቤ ማሳደጊያ መልመጃዎችን በማቅረብ ቢያስተምሩ መርጣለሁ | | | | |
| 10 | ሰዋስው ሁል ግዜ ህግጋትን በመተንተን ከመማር ከቀረቡ ምሳሌዎች በመነሳት በራሴ ምሳሌ በመስጠት ህግጋት እያወጣሁ መማር የሰዋስው ዕውቀቴን ያሳድግልኛል | | | | |
| 11 | ሰዋስው ስማር መምህሬ የዓፍተነገርና የቃል ክፍሎችን ሲያስተምሩ ከሚሰጡኝ ምሳሌ በመነሳት የራሴን ምሳሌ በማዋቀር ህግጋትን እንድለይ ሲያደርጉ የሰዋስው ዕውቀቴን ከፍ ያደርግልኛል | | | | |
| 12 | መምህሬ ሰዋስውን ሲያስተምሩ ሂደቱን ሳይሆን ግቡን መሰረት አድርገው ቢያስተምሩ እመርጣለሁ | | | | |
| 13 | መምህሬ ሰዋስውን ሲያስተምሩ ከዝርዝር ተነስተው ወደአጠቃላይ ቢደርሱ እመርጣለሁ | | | | |
| 14 | መምህሬ ሰዋስውን ሲያስተምሩ የሚነገሩ ዓረፍተ ነገሮችን በተግባር እያሳየሁ እንድረዳ ቢያደርጉ እመርጣለሁ | | | | |

አባሪ( ሠ)

የቅድመ ትምህርት እና ደህረረ ትምህርት ፈተና ውጤት

የሙከራ ቡድን (8 ለ)

| ተማሪ | | የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት | የደህረ ትምህርት ፈተና ውጤት |
|---|---|---|---|
| ኮድ | ፆታ | ከ (50 ፐርሰንት) | ከ (50 ፐርሰንት) |
| 1 | ሴ | 18 | 26 |
| 2 | ሴ | 18 | 26 |
| 3 | ወ | 30 | 34 |
| 4 | ሴ | 28 | 36 |
| 5 | ወ | 12 | 28 |
| 6 | ወ | 18 | 28 |
| 7 | ወ | 40 | 46 |
| 8 | ሴ | 20 | 28 |
| 9 | ወ | 14 | 20 |
| 10 | ወ | 26 | 32 |
| 11 | ሴ | 26 | 34 |
| 12 | ሴ | 30 | 36 |
| 13 | ሴ | 24 | 30 |
| 14 | ሴ | 22 | 28 |
| 15 | ሴ | 20 | 28 |
| 16 | ሴ | 18 | 26 |
| 17 | ሴ | 12 | 22 |
| 18 | ሴ | 20 | 28 |
| 19 | ሴ | 14 | 20 |
| 20 | ሴ | 28 | 36 |
| 21 | ሴ | 46 | 48 |
| 22 | ሴ | 26 | 32 |
| 23 | ወ | 24 | 30 |
| 24 | ሴ | 38 | 44 |
| 25 | ሴ | 8 | 24 |
| 26 | ሴ | 12 | 20 |
| 27 | ሴ | 18 | 26 |
| 28 | ሴ | 10 | 22 |
| 29 | ሴ | 24 | 28 |
| 30 | ሴ | 28 | 36 |
| 31 | ወ | 24 | 34 |
| 32 | ሴ | 10 | 26 |
| 33 | ወ | 26 | 32 |
| 34 | ሴ | 20 | 34 |
| 35 | ወ | 26 | 34 |
| 36 | ወ | 18 | 28 |
| 37 | ወ | 28 | 38 |
| 38 | ወ | 30 | 38 |
| 39 | ወ | 14 | 26 |
| 40 | ሴ | 20 | 24 |

አባሪ ‹‹ረ››

የቅድመ ትምህርት እና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት

የቁጥጥር ቡድን(8 ሀ)

| ተማሪ | | የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት | የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት |
|---|---|---|---|
| ኮድ | ፆታ | ከ(50ፐርሰንት) | ከ(50 ፐርሰንት) |
| 1 | ወ | 12 | 16 |
| 2 | ወ | 16 | 20 |
| 3 | ወ | 26 | 26 |
| 4 | ሴ | 16 | 20 |
| 5 | ወ | 16 | 20 |
| 6 | ወ | 22 | 20 |
| 7 | ሴ | 24 | 24 |
| 8 | ሴ | 16 | 20 |
| 9 | ሴ | 12 | 18 |
| 10 | ሴ | 30 | 26 |
| 11 | ወ | 30 | 30 |
| 12 | ሴ | 18 | 20 |
| 13 | ወ | 14 | 16 |
| 14 | ሴ | 12 | 16 |
| 15 | ሴ | 20 | 20 |
| 16 | ሴ | 20 | 24 |
| 17 | ሴ | 22 | 18 |
| 18 | ሴ | 26 | 22 |
| 19 | ወ | 16 | 18 |
| 20 | ሴ | 12 | 16 |
| 21 | ወ | 38 | 38 |
| 22 | ሴ | 22 | 26 |
| 23 | ሴ | 22 | 26 |
| 24 | ሴ | 18 | 20 |
| 25 | ወ | 26 | 26 |
| 26 | ሴ | 10 | 18 |
| 27 | ወ | 26 | 12 |
| 28 | ወ | 22 | 22 |
| 29 | ወ | 46 | 38 |
| 30 | ሴ | 38 | 40 |
| 31 | ወ | 28 | 22 |
| 32 | ሴ | 32 | 32 |
| 33 | ሴ | 36 | 34 |
| 34 | ወ | 24 | 32 |
| 35 | ሴ | 18 | 16 |
| 36 | ወ | 32 | 32 |
| 37 | ሴ | 20 | 22 |
| 38 | ወ | 22 | 22 |
| 39 | ሴ | 18 | 32 |
| 40 | ወ | 38 | 32 |

በዳግም ልኬትና ቲ-ቴስት (independent sample test) እና በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት

(repeated measure/paired samples test/ የተሰሩ የፈተና እና የጽሁፍ መጠይቆች ውጤቶች

PRE-EXPERMENTAL AND PRE –CONTROL TEST

| | RESP | N | Mean | STD.devation | Std.Error mean |
|---|---|---|---|---|---|
| Pretest .exp.group<br>Control.group | | 40<br>40 | 23.00<br>22.90 | 8.840<br>8.485 | 1.398<br>1.342 |

Independent samples test

| | Levene's test for equality of variances | | t-test for quality of means | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | F | Sig | T | Df | Sig(2-tailed | Mean differnce | STD.error difference |
| Equal variances assumed Post test | 134 | 715 | 0.52 | 78 | 959 | 100 | 1.937 |
| Equal variances not assumed | | | 0.52 | 77.869 | 959 | 100 | 1.937 |

Post expermental and post control

Group statistics

| | Respondent | N | Mean | STD.DEV | STD .Error mean |
|---|---|---|---|---|---|
| Post exp exp.Group<br>And control control group | | 40<br>40 | 31.40<br>24.00 | 6.946<br>6.884 | 1.098<br>1.088 |

Indpendent samples test.

| | Levene's test for equality of variances | t-test for equality of means | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | F | sig | T | df | Sig-(2-tailed | Mean diff |
| Post.exp equal var assumed and post | 001 | 973 | 4.786 | 78 | 0.000 | 7.400 |
| control equal var not assumed | | | 4.786 | 77.994 | 0.000 | 7.400 |

Pre and post control test

Paried samples statistics

| | Mean | N | Std.devation | Std .error mean |
|---|---|---|---|---|
| Pair.1 pre .control<br>Post control | 22.90<br>24.00 | 40<br>40 | 8.485<br>6.884 | 1.342<br>1.088 |

Paired samples correlation

| | N | Correlation | Sig |
|---|---|---|---|
| Pair 1.pre control<br>& post control | 40 | 0.883 | 0.000 |

Paired samples test

| | Paired differences | | | | | T | DF | Sig.(2-tailed |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | mean | Std.devation | Std.error mean | 95% confidence interval of the difference | | | | |
| | | | | lower | upper | | | |
| Pair.1pre&post Control | -1.100 | 4.024 | 0.636 | -2.387 | .187 | -1.729 | 39 | 0.092 |

Pre & post experimental test

Paired samples statistics

| | Mean | N | Std.devation | Std.error mean |
|---|---|---|---|---|
| Pair.1 pre-exper<br>- Post- exper | 23.00<br>31.40 | 40<br>40 | 8.840<br>6.946 | 1.398<br>1.098 |

Paired samples correlations

| | N | Correlation | Sig |
|---|---|---|---|
| Pair.1 pre –exp &post -exp | 40 | 0.920 | 0.000 |

Paired samples test

| | Paired differences | | | | | T | DF | Sig.(2-tailed |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | mean | Std.devation | Std.error mean | 95% confidence interval of the difference | | | | |
| | | | | lower | upper | | | |
| Pair.1pre&post Control | -8.400 | 3.657 | 0.578 | -9.570 | -7.230 | -14.527 | 39 | 0.001 |

Pre -expermental &pre –control questionnaire.

Group statistics

| | Resp. | N | Mean | Std.devation | Std.error mean |
|---|---|---|---|---|---|
| Pre-exp&<br>Pre-control | pre –exp<br>post-control | 40<br>40 | 28.40<br>28.60 | 2.405<br>2.182 | 0.380<br>0.345 |

Independent samples test

| | Levene's test for quality of varinces | | t.test for equality of means | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | F | sig | T | dif | Sig.(2-tailed |
| -Pre-exp & equal varinces assumed<br>-Pre –cont equal variances not assumed | 435 | 512 | 1.558<br>1.558 | 78<br>77.269 | 123<br>123 |

Post -expermental &post –control questionnaire.

Group statistics

| | Resp. | N | Mean | Std.devation | Std.error mean |
|---|---|---|---|---|---|
| post-exp& Post-control | post –exp<br>post-control | 40<br>40 | 35.00<br>28.30 | 3.735<br>1.911 | 0.591<br>0.302 |

Independent samples test

| | Levene's test for quality of varinces | | t.test for equality of means | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | F | sig | T | dif | Sig.(2-tailed |
| -Post-exp & equal varinces assumed | 9.013 | 0.004 | 10.101 | 78 | 0.000 |
| -Post –cont equal variances not assumed | | | 10.101 | 58.108 | 0.000 |

Pre & post experimental questionnaire

Paired samples statistics

| | Mean | N | Std-deviation | Std.error mean |
|---|---|---|---|---|
| Pair 1 pre –exp<br>& post-exp | 28.40<br>35.00 | 40<br>40 | 2.405<br>3.735 | 0.380<br>0.591 |

Paired samples correlations

| | N | Correlations | Sig |
|---|---|---|---|
| Pair 1 pre-exp & post -exp | 40 | 0.291 | 0.068 |

Paired samples test

| | Paired differnces | | | | | T | dif | Sig(2-tailed |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | mean | Std.deviation | Std.error mean | 95% confidence interval of the difference | | | | |
| | | | | lower | upper | | | |
| Pair-1 pre.exp & post.exp | -6.600 | 3.808 | 0.602 | -7.818 | -5.382 | -10.961 | 39 | 0.000 |

Pre & post experimental questionnaire

Paired samples statistics

| | Mean | N | Std-deviation | Std.error mean |
|---|---|---|---|---|
| Pair 1 pre –ontrol<br>& post-control | 27.60<br>28.30 | 40<br>40 | 2.182<br>1.911 | 0.345<br>0.302 |

Paired samples correlations

| | N | Correlations | Sig |
|---|---|---|---|
| Pair 1 pre-control & post -control | 40 | 0.337 | 0.033 |

Paired samples test

| | Paired differnces | | | | | T | dif | Sig(2-tailed |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | mean | Std.deviation | Std.error mean | 95% confidence interval of the difference | | | | |
| | | | | lower | upper | | | |
| Pair-1 pre.exp & post.exp | -700 | 2.366 | 0.374 | -1.457 | 0.057 | -1.871 | 39 | 0.000 |